200 ማስረጃዎች ምድር የምትሽከረከር ኳስ እንዳልሆነች

By Eric Dubay

AtlanteanConspiracy.com
IFERS.boards.net

ትርጉም በትንሳኤ ዘኢትዮጵያ

1) በማንኛውም ከፍታ ላይ ባለ እይታ ውስጥ የምድር አድማስ 360 ዲግሪ ዝርግ ሁኖ መታየት፤ በሁሉም አማተር ባሉን፣ ሮኬት፣ አውሮፕላን እና ድሮውን ቀረፃ አድማሱ ሙሉበሙሉ ዝርግ ሁኖ ከ20+ ማየል ከፍታ ላይ ይታያል። ናሳና የሌሎች አስተዳደር ህዋ ሳይንስ ተቋማት ብቻ ናቸው ፈክ በሆኑ የኮምፒውተር ፎቶዎቻቸው የምድርን የተጠመዘዘ /curve ያደረገ አድማስ የሚያሳዩት።

2) ከፍታ በጨመርን ቁጥር የምድር አድማስ ከእይታችን ከፍታ ጋር እኩል እየጨመረ መታየት፤ በዚህም ምክንያት ምድርን ለማየት ማጎንበስ አይጠበቅብንም። ምድር ሉል ብትሆን ኑሮ ምንም ያህል እርቀት ወደ ላይ ብንወጣ አድማሱ ውስን ሁኖ መቆም ነበረበት፤ ካሜራ ወይም ተመልካች ከፍታ በጨመረ ቁጥር ምድርን ለማየት ወደታች እያቀረቀረ መሄድ ነበረበት።



3) በተፈጥሮ የውሃ ጸባይ ባገኘበት መፍሰስና ወለል ብሎ መቀመጥ ነው፤ ምድር ትልቅ ኳስ ከነበረችና ዘንበል ብላ እየተሽከረከረች ከፀሐይ ጋር ወደማያልቀው ህዋ የምትሮጥ ከሆነ፤ እንደዚህ በቋሚነት ቀጥ ብሎ የተዘረጋ ባህር ሊኖር አይገባም ነበር። ነገር ግን ምድር የተለጠጠች ዝርግ ጠለል በመሆኗ ይህ መሰረታዊ የፈሳሾች ባገኙት ቀዳዳ የመፍሰስና ወለል ብሎ ውሃልክን ጠብቆ የመቀመጥ ጸባይ በደንብ ከልምዳችን እና ከስሜት ህዋሳችን የምንረዳው እውነት ነው።

4) ወንዞች በተመሳሳይ ጊዜ ከተለያዩ ከሰሜን፣ ከደቡብ፣ ከምስራቅና ከምዕራብ አቅጣጫ ቁልቁለትን ተከትለው ወደታች ወደ ባህር ጠለል ይፈሳሉ። ምድር የምትሽከረከር ኳስ ከነበረች፤ ብዙዎቹ እነዚህ ወንዞች በማይታሰብ ሁኔታ ወደ ላይ ወደ ዳገትም እየፈሰሱ መሆን ነበረበት። ለምሳሌ የ3000 ማየሉ የሚሲሲፒ ወንዝ ከሜክሲኮ ባህረ ሰላጤ ከመግባቱ በፊት ወደላይ 11 ማየል መውጣት ነበረበት።

5) አንዱ የናየል ወንዝ አካል፤ ለሺህ ማየሎች በአንድ ጫማ ዝቅታ ምክንያት ብቻ ይፈሳል፤ የምዕራቡ አፍሪካ ክፍል ኮንጎ ማለት ነው። በሚባለው ያጋደለ የኳስ ዓለም እንቅስቃሴ ምክንያት ወንዞቹ አንዳንዴ ወደታችና አንዳንዴ ወደላይ ዳገትም መሮጥ ነበረባቸው። እንዲሁ ለፓራና፣ ፓራጉዋ እና ለሌሎች ትልቅ ወንዞችም የዚህ አይነቱ ክስተት ሊፈጠር ይገባ ነበር።



6) ልክ ናሳና የዘመኑ ጠፈርተኞች እንደሚሉት ምድር ኳስ ከነበረችና 25,000 ማየል ዙሪያ ካላት፤ በሉል ትሪጎኖሜትሪ መሰረት ሁሉም የባህር ጠለል የተጠመዘዘ/curve ያደረገ ሁኖ 8 ኢንች በአንድ ማየል ውስጥ ሲባዛ እርቀቱን በማል እርቢ ሁለት (8inch/mile (distance)^2) አድርገን በቀላሉ በዛ እርቀት ውስጥ ያለውን ጉብታ(curvature) ማወቅ እንችላለን ማለት ነው። ይህም ማለት፤ በምድር የ6 ማየል እርቀት የቦይ ውሃ ውስጥ ከመሀከለኛው ቦታ በግራና ቀኝ ወይም በሁለቱም ጫፍ በኩል የስድስት ጫማ ዝቅታ ይኖራል ማለት ነው። ብዙጊዜ የዚህ አይነቱ ምርመራ ቢካሄድም የቆመ ውሃ በስነስርአት ዝርግ መሆኑ ነው የተረጋገጠው።

7) ሰርቬየሮች ኢንጅነሮች እና አርክቴክቸሮች ይህንን የተጠመዘዘ የምድር ቅርጽ በፕሮጀክቶቻቸው ውስጥ ግምት ውስጥ ለማስገባት አልተገደዱም። ለምሳሌ ቦዮች፣ የባቡር ሀዲዶች፣ ድልድዮች እና ዋሻወች ከመቶ ማየል በላይ በሆነ እርቀትም ያለምንም ጉብታ አግድም ቀጥብሎ በተዘረጋ ጠለል ላይ ነው የሚገነቡት።

8) ሜዲትራኒያንን ከቀይ ባህር ጋር የሚያገናኘው የግብፁ ሲውዝ ካናል፤ የ100 ማየል እርዝመት ሲኖረው፤ ውሃው ያለምንም መረበሽ ቀጥ ብሎ ሁለቱን ባህር እንዲያገናኝ፤ በመካከሉ ምንም አይነት ቁልፍ ቦታ ወይም በር የለውም። ሲገነባም ምድር ይኖራታል የሚባለው ጉብታ(curve) ግምት ውስጥ አልገባም። አግድም ከባህር ጠለል በታች 26 ጫማ በሆነ ጥልቀት በተቆፈረ መሰረት ላይ የቆመ ነው፤ ለመቶ ማየል እርቀት የቦዩ መሰረት እና የውሃው ጠለል ትይዩ(parallel) ሁነው ያልፋሉ።

9) ኢንጅነር ደብልዩ. ዊንክለር በኧርዝ ሪቪው ጋዜጣ ላይ የሚባለውን የምድር መጠምዘዝ(curvature) በተመለከተ በሰጠው መግለጫ ‹‹ኢንጅነር ሁኜ ስብዙ ስመት እንደማገልገሌ ደህ የምድር ጉብታ(curve) የሚባለው በትምህርት ቤት መፅሐፎች ብቻ ነው ሲፈቀድ ያየሁት፤ ማንም ኢንጅነር የዚህ ስደነቱን ነገር ግምት ውስጥ ስማስገባት ስያልምም፤ እኔ ብዙ ማየል እርቀት ያሳቸውን የባቡር ሀዲዶች እንዲሁም የተስያዩ ብዙ ቦዮች ሰርቻስሁ፤ ስመስሬት ከምንጠቀምባቸው ስሌቶች ውጭ ግምት ውስጥ መግባት ነበረበት የሚባለው የምድር ከርቭ ግን በፍፁም ስደታስብም። ስጉብታው መታሰብ ስስበት የሚባለው ደህ ነው፤ 8 ኢንች ከርቭ ስመጀመሬያው የስንድ ማየል ቦደ፤ በሙሉ እርቀቱ እርቢ ሁስት ሲባዛ በስምንት ኢንች ደህም ማስት፤ ስስጭሯ የ30 ማየል መርከብ መተሳስፌያ ቦደ በሳደኛው ህግ መሰረት የ600 ጫማ ከርቭ ደኖረዋል ማስት ነው። ስስሁትና ኢንጅነሮች ሞኝ ሁነው እንዳልሆነ የዚህስደነቱን ህግ የማደጠቀሙት ተረዱልኝ፤ ስ30 ማየል የባቡር ሃዲድ የ600 ጫማ ከርቭ ደኖረዋል ብስን ስናስብም፤ ክቡንም ስማዎቅ እርቢ ሁስት በማድረግ ጊዜያችንን ስሳጠፋንም።››

10) የለንደን እና የሰሜን ምዕራቡ የባቡር ሃዲድ ከለንደን እስከ ሊቨርፑል ሁኖ 180 ማየል ቀጥተኛ መስመር ይሰራል። በሀዲዱ አጋማሽ ቦታ በርሚንግሀም ላይ በሚገኘው ጣቢያ ያለው ከፍታ ከባህር ጠለል በላይ 240 ጫማ ነው፤ ምድር ሉል ብትሆን እና 8 ኢንች ጉብታ በአንድ ማየል ውስጥ ቢኖራት፤ ለ180 ማየል የተዘረጋው ሀዲድ በቀመሩ መሰረት መሀል ቦታ በርሚንግሀም ላይ በሚፈጠረው የ5,400 ጫማ ከርቭ ምክንያት ከለንደን እስከ ሊቨርፑል በትልቁ የተጠመዘዘ arc/ጉብታ ይሆን ነበር።



11) በ በርሚንግሃም ዊክሊ ሜርኩሪ ጋዜጣ እትም ላይ ለስላሳ ዓመት ቀያሽና ምሃንዲስ ሁኖ ያገለገለው ሰው እንደተናገረው ‹‹ስኔ በሲቪል ምህንድስና ንድፌ ዘሳብ እና ተግባር ስፌ ላይ ስስዚህ ጉዳዩ በደንብ መረዳት ችያስሁ፤ ነገርግን ስንዳንድ ስክፊፊ ፕሮፌሰሮች ስሁንም መቀየሳ ንድፌ ዘሳብ ላይ በተገስፀው ደንብ ውስጥ ሲሆኑ ደችሳሉ፤ ደህ ንድፌ ዘሳባዊ ልኬታ በተግባር ስፌዎች ላይ የማደመጣጠን መሆን ግን በስኛ ዘንድ የታወቀ ነው። ሁሱም የስኛ ፌጣን ባቡሮች ዲዛይን የሚደርጉት በስውነተኛ መሰረት ወይም በዝርግ መሰረት ላይ እንዲርሙ ተደርጎ ነው፤ በእርግጥ መፌት ላይ ብዙ ዳገቶች እና ንድንዳ ስፍፌዎች ደኖፌሉ፤ እነዚህ ሁሱ ግን በሃዲዱ ተዋኖ እንዳያደርጉ በጥንቃቄ እንዲስተካከሱ ተደርጎና ቦታ ተመርጦ ነው የሚሰፌሙ። ነገር ግን በስንድ ማየል ውስጥ ወደ 8 ኢንች መጠምዘዝ እና በእርቀቱ እርቢ ሁስት እየተባዛ ጉብታው መጨመሬ፤ በማጎኛውም የተገነባ ማሽን ላይ ሲሰፌ ስደችልም፤ በሁሱም ስስኮትላንድ እና ኢንግላንድ ያሉ ጣቢያዎችን ስንዱን ከስንዱ ብናስተያደ የሁሱም መድረክ በተንዳዘፌ ከፍታ ላይ መገኘት ደችሳል፤ በምስፌቅ ኢንግላንድ እና በምስፌብ ኢንግላድ ባህር ዳርቻዎች መካከል ያለው እርቀት 300 ማየል ነው፤ የተባለው የምድር መጠምዘዝ እንደተገስፀው ከሆነ፤ በፌገቢ ወደም በዋርዊኪ የሚገኘው መካከለኛው ጣቢያ ቀጥተኛ መስመር ሁኖ ሁስቱን ጫፎች ከማገናኘት ደሳቅ ከሁስቱ ጫፎች በስዩ ሁኔታ ወደ ሳደ 3 ማየል ከፍ ብሎ ደገኛል ማስት ነው፤ ሁኔታው እንደዛ ከሆነ ደግሞ በዛ ግዛት የባቡሪን ኃሳፌነት የሚወስድ ምንም ስደነት ሹፌር ወደም ሰፌተኛ ሲኖር ስደችልም ነበር። እኛ ግን እንዴት ደህን ኃሳፌነት ወስዶ የሚሰፌ ተቀጣሪ ደጠፋል ብለው በቁምነገር በሚናገሪ ስንባቢዎች ልንስቅ እንችሳለን፤ እንደው በሱል ዙሪያ ስሚሮጥ ባቡር፤ በቀጥታ ስግድም መስመር ሳደ ያስ መጠምዘዝ እንኳን በጣም ስደገኛ ነው በቁልቁል የሚደረግ መጠምዘዝ ደግሞ በጣም በእጅጉ የከፋ ደሆናል፤ ስሁን ስተሰሪት ባቡሮች ደግሞ የማደታስብ ነው።››

12) በኧርዝ ሪቪው ጋዜጣ ላይ የማንችስተር መርከብ ቦይ(canal) ኩባንያ እንዲህ ሲል ተናግሯል፡- ‹‹በዘዲድ እና ቦደ ግንባታዎች ሁሱም መሰረቶች ቀጥተኛ ብቻ ተደርገው መታሰብ መደበኛ ስርዓት ነው፤ ማስትም መፌቱ ቀጥተኛ ስግድም ተደርጎ ደመሰዳል፤ ደህም በሁሱም ክፍሎች የሚታደ ነው፤ በደፌ በተግባር ስፌዎቻችን ላይ የምድርን መጠምዘዝ ግምት ውስጥ ስማስገባት የዚህ ስደነት ህግ ስንጠቀምም።››

13) በ 19ኛው ክፍለ ዘመን በኤም ኤም ቢዮት እና አራጎ የፊረንሳውያን ኢክስፐርመንት፤ ትልቅ ጉልበት ያለው አምፖል ከትልቅ ማንጸባረቂያ ጋር ሁኖ በዲሳርቶ ላስ ፓልማስ ከተማ ጫፍ እስፔን ውስጥ ተቀመጠ፤ በአይቪዛ ደሴት ላይ ኬፕሬ ከተማ ድረስ ማየት ተችሏል። በሁለቱም ቦታዎች ላይ የነበረው ከፍታ ተመሳሳይ በመሆኑ እና በመካከላቸው የነበረው እርቀት ወደ 100 ማየል በመጠጋቱ፤ ምድር ካስ ከነበረችና 25,000 ማየል ዙሪያ

ካላት፤ አምፖሉ 6,600 ጫማ ወይም አንድ ማየል ከሩብ ከእይታ መስመር በታች መሆን ነበረበት።።

14) የምክትል ኮሎኔል ፖርትሎክ መኩራ፤ ኦክሲ ሃይድሮጅን ድራመንድ ብርሃንን ወስዶ የፀሐይን ጨረር ለማንጸባረቅ ሄሊዮ እስታትን በመጠቀም፤ በሴንት ጆርጅ ወንዝ ሁኖ በ108 ማየል እርቀት ላይ ለሚገኘው ጣቢያ ማንጸባረቅ ችሏል።። ምድር ኳስ ከነበረች እና 25,000 ማየል ዙሪያ ካላት፤ የፖርትሎክ ብርሃን አንድ ማየል ከሩብ በላይ በሆነ ዝቅታ ከእይታ በታች መሆን ነበረበት።።



15) በእውነት ምድር ሉል ከነበረችና 25,000 ማየል ዙሪያ ካላት፤ የአውሮፕላን አብራሪዎች ወደ ውጭ ወደ ህዋ ላለመብረር፤ ሁልጊዜ ከፍታቸውን ወደታች ዝቅ እያደረጉ መብረር ነበረባቸው።። አውሮፕላን ባለው በሰዓት 500 ማየል የሆነ ፍጥነት፤ አብራሪው በእያንዳንዷ ደቂቃ የአየሩን አፍንጫ ቁልቁል 277 ጫማ(ከግማሽ ማየል በላይ) ታች ዝቅ እያደረገ መብረር ነበረበት፤ አለበለዚያማ ያለምንም ማስተካከያ በአንድ ሰዓት ጊዜ ውስጥ አብራሪዎች ከሚጠበቀው ከፍታ ውጭ በተጨማሪ የ31.5 ማየል ከፍታ ላይ እራሳቸውን ያገኛሉ።።

16) ‹‹የኤሪ ውድቀት›› በመባል የሚታወቀው ኢክስፐርመንት ከዋክብቶች በማትንቀሳቀሰው ምድር ሰማይ ልይ እንደሚዞሩ እንጅ በሌላ እንዳልሆነ ያረጋገጠ ነበር።። በመጀመሪያ የብርሃን ፍጥነትን ለመቀነስ ቴሌስኮፕ በውሃ ተሞላ፤ የኮከቡ ብርሃን በቀጥታ ቱቦ ውስጥ እንዲገባ የሚያስፈልገውን ዝንባሌ ካሰላ በኋላ፤ ኤሪ የተንቀሳቃሿን ዓለም ቲወሪ ለማረጋገጥ ተስኖታል፤ ምክንያቱም የኮከቡ ብርሃን ያለ ምንም መቀያየር በትክክለኛ ማዕዘን ይመጣ ስለነበር።። በተዘዋዋሪ ግን ቋሚ የማትንቀሳቀሰውን ዓለም ንድፈሃሳብ ያረጋገጠ መኩራ ነበር።።



17) ‹‹የአልበር ተቃውሞ›› እንደሚለው፡- በቢሊየኖች ከዋክብት ኑረው ፀሐይ ከነበሩ፤ የምሽቱ ሰማይ ሙሉበሙሉ በብርሃን መሞላት ነበረበት።። አድጋር አለንፖም እንዳለው ‹‹የኮከቦች ተከታታይነት ማስቂያ ከሌለው የሰማዩ ዳራ ወጥ የሆነ ብሏህነት ማሳየት ነበረበት፤ ምክንያቱም በዚያ ሁሉ ዳራ ኮከብ የሌለበት ምንም ስንነት ክፍት ቦታ ሲገኝ ስለማይችል።።› የሚገርመው ግን የአልበር ተቃውሞ ያው ተቃውሞ ብቻ ነበር የተባለው፤ ልክ የጆርጅ ኤሪ መኩራ ውድቀት እንደተባለው፤ ሁለቱም ግን ፀሐይን ማዕከል አድርጎ የሚሽከረከረውን ኳስ ዓለም ንድፈ ሃሳብ ትክክለኛ ድክመት ነበር ያወጡት።።



18) የሚቸልሰን ሞርሊ እና የሳግናክ ኢክስፐርመንት፤ የሚታሰበው የምድር ህዋ ላይ እንቅስቃሴ የሚኖረውን የብርሃን ፍጥነት ልዩነት ለመለካት ባደረጉት መኩራ፤ ከተለያዩ ቦታዎች በሁሉም የተገኘ አቅጣጫ መለካት ከቻሉ በኋላ፤ ምንም አይነት ሊታይ የሚችል ለውጥ ማግኘት ተስኗቸዋል።። አሁንም ቋሚ የማትንቀሳቀሰውን ምድር ያሳያል።።



19) በወቅቱ ፀሐይን ማዕከል አድረጎ የሚንቀሳቀሰውን ዓለም ንድፈሃሳብ እንደተቀበለ የሚታወቀው ቴኮብራሂ፤ እንዲህ ሲል ግራመጋባቱን ገልጾ ነበር፡- ከ6 ወር ምህዋራዊ እንቅስቃሴ በኋላ

የኮከቦቹ አንጻራዊ አቀማመጥ መቀየር፤ ሳይታይ መቅረት አልነበረበትም፤ ወደ ኮከቦቹ ስንጠጋ ተለያይተውና፤ እየራቅን ስንሄድ ደግሞ አንድላይ የሆኑ መስለው መታየት ነበረባቸው፤ ብሎ ተከራክሯል። በእውነታው ግን 190,000,000 ማየል በሚታሰበው ፀሐይን ዙሪት፤ የአንድ ኢንች ልዩነት እንኳን በከዋክብቶቹ ላይ ማየት አይቻልም ምንም እንዳልተንቀሳቀስን ያስረዳል።



20) በእውነት ምድር በሰዓት ከ1000 ማየል በላይ ከምስራቅ በኩል ያለማቋረጥ የምትሽከረከር ከሆነ፤ ወደ ላይ የተተኮሰ የመድፍ ኳስ እና ሌሎችም ወደ ሰማይ የተወረወሩ ነገሮች በጎላ ሁኔታ ወደ ምዕራብ መውደቅ ነበረባቸው። በእውነታው ግን ምንም እነዚህ ነገሮች ቢሞከሩም፤ ወደ ላይ የተተኮሰው የመድፍ ኳስ በአማካኝ የ14 ሴኮንድ ወደላይ ጉዞ እና የ14 ሴኮንድ ወደታች የመመለስ ጉዞ በኋላ እዛው ተመልሶ ከመድፉ ሁለት ጫማ ጎን ላይ አርፏል፤ ቀጥታ ተመልሶ ወደ አፈሙዙ ማለት ነው።



21) በእውነት ምድር ያለማቋረጥ በሰዓት ከ1000 ማየል በላይ ከምስራቅ በኩል የምትሽከረከር ከነበረ፤ ሄሊኮፕተሮች እና የሙቅ አየር ባሉኖች፤ በቀላሉ አየር ላይ ተንሳፈው በመቆም የሚፈልጉት መዳረሻ እስከሚመጣ ድረስ መጠበቅ ይችሉ ነበር።

22) በእውነት ምድር ያለማቋረጥ በሰዓት ከ1000 ማየል በላይ ከምስራቅ በኩል የምትሽከረከር ከሆነ፤ በሬድቦል የፍሊክስ ባምጋርትነር የእስትራቶስፌር ዝላይ፤ ወደ ኒው ሜክሲኮ ሰማይ ላይ በወሰደበት የ3 ሰዓት ጊዜ፤ ሲያርፍ ደግሞ 2,500 ማየል ወደ ምዕራብ ፓስፊክ ውቅያኖስ መሆን ነበረበት፤ እሱ ግን ከተነሳበት ቦታ በ12 ማየሎች እርቀት ብቻ አርፏል።

23) የኳሷ አማኞች እንደሚሉት ከሆነ፤ የምድር ስበት አስማታዊ ሁኖ ያለምንም ችግር በሙሉ የታችኛዉን ከባቢ አየር ጎትቶ እስካልተገለጸ ከፍታ ድረስ ከምድር ጋር በተመሳሳይ ፍጥነት ማድረግ እንደቻለና፤ ይህ በተከታታይ እየፈጠነ የሚሽከረከረዉ ከባቢ አየር ለማይሽከረከረዉ፤ ስበት ለሌለዉ፤ አየር ለሌለዉ የማያልቅ ባዶ ህዋም የተመቻቸ እንደነበር ነዉ። እንደዚህ ምንም ስሜት የማይሰጥ ንድፈሃሳብ ግን በዝናብ፤ በእርችቶች፤ በወፎች፤ በትንኞች፤ በደመናዎች፤ በጭሶች፤ በአዉሮፕላኖች፤ በነፋሶች እና በተወረወሩ ነገሮች መጋለጥ የቻለ ንድፈሀሳብ ነበር። ምድርና የአየር ንብረቱ 1000 ማየል በሰዓት ወደ ምስራቅ በኩል የሚሽከረከሩ ከነበረ፤ እነዚህ ሁሉ ሁነቶች በጣም በተለየ ጸባይ መከሰት ነበረባቸው።



24) ምድርና ከባቢ አየሯ በቋሚነት 1000 ማየል ከምስራቅ በኩል እየተሽከረከሩ ከሆነ፤ ወደ ሰሜን/ደቡብ ፊቱን ያዞረ መድፍ ሲተኮስ የሚያርፍበት ቦታ መወሰን ይችል ነበር፤ ወደ ምስራቅ የተተኮሰው መድፍ ወደ ምዕራብ ከተተኮሰው መድፍ ይልቅ በጉልህ ሁኔታ እራቅ ብሎ መውደቅ ነበረበት፤ ወደ ምዕራብ የተተኮሰው መድፍ ደግሞ በተቃራኒው ቀረብ ባለ ቦታ ላይ ማረፍ ነበረበት፤ በእውነታው ግን በየትኛዉም አቅጣጫ የተተኮሰ መድፍ የሚሸፍነው እርቀት አንድአይነት ነው።

25) ምድር እና ከባቢ አየሯ በቋሚነት በሰዓት 1000 ማየል ከምስራቅ በኩል እየተሽከረከሩ ከሆነ፤ የንግድ አውሮፕላኖች አማካኝ 500 ማየል በሰዓት እየተጓዙ፤ ከምስራቅ በኩል ወደ ምዕራብ ለሚያደርጉት በረራ ፊዕሞ መድረስ ባልቻሉ ነበር። ከኋላ የተለየ ፍጥነት ጨምረው ምድርን መቅደም ካልቻሉ በስተቀር። በተቃራኒው ከምዕራብ ወደ ምስራቅ የሚደረግ በረራ ደግሞ ከፍጥነቱ በሶስት እጥፍ ቅርብ ሁኖለት ይደርስ ነበር፤ እውነታው ግን ይሄ አይደለም።

26) ‹‹Heaven and Earth›› ከጋብሬል ሄንሪት አባባል ‹‹የስየር በፈፌ በኮፐርኒከስ ዘመን ተፈጥሮ ቢሆን ኑሮ፤ እንደምትሽከረከር የነበረው ስስተያየት ስህተት መሆኑን እንደሚፈዳ ምንም ጥርጥር የስውም፤ የስውሮፕላን ፍጥነትና የምድር ስሽክርክፈት በምንም መልኩ ስደዛመድም። እንደተባለው ምድር በሰዓት 1000 ማየል የምትሽከረከር ከሆነ፤ ስየሏም በተመሳሳይ ስቀጣጫ በሰዓት 500 ማየል ብቻ ስየበረረ፤ በየደቂቃው የስየሏ መዳረሻ ስየራቀ እንደሚሄድ ግልጽ ነው፤ በስሽክርክፈቱ ተቃራኒ ስቀጣጫ የሚደረግ በፈፌ ግን፤ የ1,500 ማየሱን እርቀት በስንድ ሰዓት መድረስ ደኖርበታል ማስት ነው፤ 1000 ማየል በሰዓት ስየበረረ ነው የሚባል የምድርን ስሽክርክፈት ስናነሳ፤ በተመሳሳይ ስቀጣጫ በዚሁ በጠን የሚበር ስውሮፕላን ቢኖር እንኳን ወደየትም እርቆ መሄድ ስደችልም

ነበር፤ እዛው ከተነሳበት ቦታ አየር ላይ ተንሳፎ ይቀር ነበር፤ ምክንያቱም የሁለቱም ፍጥነት እኩል ስለሆነ፡፡››

27) ምድርና የአየር ንብረቷ ዘወትር በሰዓት ከ1000 ማየል በላይ ከምስራቅ በኩል እየተሽከረከሩ ከሆነ፤ እንደዚህ በሚሮጥ ምድር ላይ አውሮፕላንን በሁሉም በሰሜን፣ በደቡብ፣ በምስራቅ፣ በምዕራብ እና በተለያዩ አቅጣጫዎች ማሳረፍ መቻል የማይተሰብ ተግባር ይሆን ነበር፡፡ ነገር ግን በእውነታው እንደዚህ አይነቱ ልብወለዳዊ ጭንቀት ሙሉበሙሉ የማያሳስብ ነው፡፡



28) ምድርና የአየር ንብረቷ ያለማቋረጥ በሰዓት ከ1000 ማየል በላይ ከምስራቅ በኩል የሚሽከረከሩ ከሆነ፤ ዳመናዎች ነፋሳት እና የአየሩ ሁኔታ በተናጥል ባልታሰበ መልኩ በየትኛውም ተቃራኒ አቅጣጫ መሄድ እና ዳመናዎች ደግሞ በየትኛውም ከፍታ ላይ እንደፈለጉ መጓዝ አልነበረባቸውም፡፡

29) ምድርና የአየር ንብረቷ ያለማቋረጥ በሰዓት ከ1000 ማየል በላይ ከምስራቅ በኩል የሚሽከረከሩ ከነበረ፤ ይህ ሁሉ ግን በአንድ ቦታ ወይም በአንድ ሰው እንኳን ታይቶ፣ ተሰምቶ ወይም ተለክቶ የነበረ ጉዳይ እንዲሆን ያስፈልግ ነበር፤ ይህንን ከምስራቅ በኩል የማያልቅ እንቅስቃሴ ግን፤ በታሪክ ውስጥ ማንም ሰው አልተለማመደውም፡፡ ነገር ግን እኛ ትንሿን ከምዕራብ በኩል የምትነሳ ነፋስ እንኳን መስማትም መለካትም እንችላለን፡፡

30) ‹‹South Sea Voyages›› በሚለው መጽሐፉ፤ የአርክቲክ እና የአንታርክቲክ አሳሽ የሆነው ክቡር ጀምስ ክላርክ ሮስ፤ በህዳር 27 ማታ 1839 ከተሞክሮው ምድር የማትንቀሳቀስ መሆን አለባት ያስባለውን መደምደሚያ ገልጿል፤ ‹‹ሰማዩ በጣም የጠሬ ሁኖ የተደሬሬቡት ደመናዎች ከንፋሱ በተቃሬኒ ሲጓዙ አሳየን፤ ይህም ሁኔታ በሁለቱም ሰሜን-ምስሬቅና ደቡብ-ምስሬቅ ጉዟችን በተደጋጋሚ የሜትሮሎጂያዊ መጽሔታችን ላይ ስንመዝገብው የነበረ ነው፤ ብዙ ጊዜ በቀድሞ ተጓዦችም ሲስተዋል የነበረው ማለት ነው፤ ካፒቴን ባዝል ሀል ከጫፍ ከፍታ ቴኔሪፍ ጫፍ ላይ እና በካውንት እስትረዝለች ሁኖ ምስክርነት ሰጥቷል፤ በኦውሄይ ሀገር ወደላይ እሳተ ገሞሬማውን የኬርንያ ተሬሬ ከወጣ በኋላ ባህሩ ላይ ካለው ነፋስ 400 ጫማ ከፍታ ላይ ሁኖ ተቃሬኒ ተጽኖ ያለውና የተለያየ ሃይግሮሜትሬዊ እና ቴርሞሜትሬዊ ሁኔታዎች ያሉት አየር ነበር የገጠመው፡፡ በካውንት እስትረዝለች በተጨማሪም ተከታዩን ያልተለመደ የሚመስል ሁኔታ አሳውቆኛል፤ ከ600 ጫማ ከፍታ አየሩ ከቀጥተኛ ማዕዘን እየተወረወረ ለሁለቱም የታችኛው የድንጋይ ደረጃዎች ሁሉ ሲሆን፤ እንዲሁ የተለያየ ሃይግሮሜትሬዊ እና ቴርሞሜትሬዊ ሁኔታዎች ኑረውት፤ ግን ከታች ካሉት የድንጋይ ደረጃዎች ለየት ብሎ ደግሞ ሞቃት ነበር፡፡ የዚህ አይነት ደረጃዎች ያሉት የአየር ንብረት የሚገጥመው ከሚታዩት አውነተኛ ማስረጃዎችም ጋር ጨምሮ ምደር እረፍት ላይ ነች ከሚለው ጋር ብቻ ነው፡፡››

31) ከአባባል በ ‹‹Zetetic Cosmogeny›› መጽሐፍ ቶማስ ዊንሽፕ እንዳስቀመጠው፡- ‹‹እስኪ 8,000 ማየል ዲያሜትር ባላት የምትንቀሳቀስ ሉላዊ አካል ላይ አየር ሲኖረው የሚችለውን ጉልበት በሃሳባችን እንሳለውና፤ በሰዓት አንድሺህ ማየል እየተሽከረከረች፤ በሰዓት 65,000 ማየል በህዋ ላይ እየሮጠችና በመላው ሰማያት እየዞረች፤ እስኪ የሚተነብይ ሰው የሉሏ ኗሪዎች ፀጉራቸው እንዴት እንዲሆን ለማወቅ ይጣር፤ ሉል ምድር በሩሷ ዛቢያ አስፈሪ 1000 ማየል በሰዓት የምትሽከረከር ከሆነ፤ እንደዚህ የገዘፈው ክብደቷ እጅግ በጣም ትልቅና ፈጣን የሆነ ነፋስ በምትይዘው ቦታ ሁሉ ይፈጠር ነበር፤ ነፋሱ በአንድ አቅጣጫ ይጓዛል፤ ማንኛውም ልክ በምትሽከረከረው ሉል ተጽኖ የሚኖር ደመና ሁሉ ቢኖር በተመሳሳይ አቅጣጫ ይጓዛል፡፡ ምድር ረፍት ላይ እንደሆነች ሃቁ ግን በካይት በረራ ተረጋግጧል፡፡››

32) እስኪ ‹‹ግራቪቲ›› የዓለምን ውቅያኖሶች፣ ህንጻዎች፣ ሰዎችና የአየር ንብረቱ በፍጥነት በምትሽከረከረው ኳስ ገጽ ላይ ተለጥፈው እንዲቀሩ እስከማድረግ ጥንካሬ ያለው ኃይል እንደሆነ እውቅና ከተሰጠው፤ እንዲሁም በአንድ ጊዜ ደግሞ ግራቪቲ ወፎች፣ ትንኞች እና አውሮፕላኖች በማንኛውም አቅጣጫ ያለምንም ገደብ በነጻነት እንዲበሩ ለመፍቀድ ደካማ ሁኖ መገኘት፤ የማይመስል ነገር ነው፡፡

33) እንዲሁ ‹‹ግራቪቲ›› ግዙፉን የውቅያኖስ ጠረፍ በሉል ምድር ዙሪያ ተጠምዝዞ እንዲቀር እስከ ማድረግ ጉልበት ያለው ጠንካራ ኃይል እንደሆነ እውቅና ከተሰጠዉ፤ ለአሳዎችና ሌሎች ፍጥረቶች እንደዚህ በኃይል ተለጥፎ በተያዘ ባህር ዉስጥ መዋኘት የማይታሰብ ይሆን ነበር፡፡

34) የመርከብ ካፒቴኖች የትልልቅ እርቀቶችን አቅጣጫ ሲመሩ፤ የሚባለውን የምድር መጠምዘዝ ስሌታቸው ውስጥ አስገብተው ማቀናነስ አላስፈለጋቸውም፤ ሁለቱም የጠለል ጉዞ እና ታላቁ የክብ ጉዞ እንደዚሁ ነው፤ በጣም ታዋቂ የሆነው የአቅጣጫ መጠቆሚያ ዘዴ የሚጠቀመው ጠለልን ነው፤ ሉላዊ ቴሪጎኖሜትሪን አይደለም፤ ሁሉም ሒሳባዊ ስሌቶች የሚሰሩት ፍጹም ዝርግ በሆነ እሳቤ ነው፡፡ ምድር ሉል ሁና ቢሆን ኑሮ፤ እንደዚህ የተሳሳተ እሳቤ በቋሚነት በጣም ግልጽ ለሆነ ጉድለት ይዳርግ ነበር፡፡ ለሺህ ዓመታት የጠለል ጉዞ በሀሳብም በተግባርም ትክክለኛ ሁኖ አገላግሏል፤ በአሁኑም ሰዓት የጠለል ትሪጎኖሜትሪ በመላው ውቅያኖስ ያለን እርቀት ለማወቅ፤ ከሉል ትሪጎኖሜትሪ ይልቅ የበለጠ ትክክለኛ እንደሆነ የተረጋገጠ ነው፡፡



35) እውነት ምድር ሉል ከነበረች፤ ከወገብ በታች ሁሉም የኬክሮስ መስመር ወደ ደቡብ በጣም በወረድን ቁጥር ቀስበቀስ እያነሰ የሚመጣ ዙሪያ ሊኖረው ይገባ ነበር። ነገር ግን ምድር የተዘረጋች ጠለል ከሆነች፤ ወደ ደቡብ እየራቅን በሄድን ቁጥር ሁሉም የኬክሮስ መስመር ቀስበቀስ እየሰፋና እየሰፋ የሚሄድ ዙሪያ ይኖረዋል። ብዙ ካርቴኖች ሉላዊ ንድፈሃሳቡን ይዘው የደቡቡን ክፍል በሚዞሩበት ጊዜ፤ እራሳቸውን በከፍተኛ ሁኔታ ከሚገመተው ውጭ ሁነው የሚያገኙት ለዚህ ነው። ይበለጥ ወደ ደቡብ ከተጓዝን ለእውነታው ምድር ኪስ እንዳልሆነች አመሳከርን።



36) በካፒቴን ጀምስ ክላርክ ሮስ የአንታርክቲክን መዞር ጉዞ፤ ብዙ ጊዜ ማስታወሻው ላይ፤ እንዴት ሁልጊዜ እራሳቸውን ግራባጋባ መልኩ ከካርታቸው ውጭ ሁነው ያገኙ እንደነበር ጽፏል፤ ክላርክ ሲጽፍም፡ በሁሉም ቀን እራሳቸውን አማካኝ ከ12-16 ማየል ከሚገመተው ውጪ ሁነው ያገኙ እንደነበር አስቀምጧል፤ በኋላም በጣም ዝቅ ሲሉ በቀን እስከ 29 ማየል እንደነበር።

37) መቶ አለቃ ቻርለስ ዊልክስ፤ የዩናይትድ እስቴትን የባህር ሃይል ወደ አንታርክቲክ የማሰስ ዘመቻ፤ ከ1838 እስከ 1842 መርቷል። በማስታወሻውም ላይ በተከታታይነት ያለማቋረጥ በምስራቁ እንደሆነ በሚገመተው ክፍል ቀርተው እንደነበር ጠቅሷል፤ አንዳንዴም ከ18 ሰዓቶች ባነሰ ጊዜ ውስጥ ከ20 ማየል በላይ ይሆን እንደነበር ጽፏል።

38) የተከበሩ ቶማስ ሚልነርን አባባል እንጥቀስ ‹‹በደቡብ ንፍቀ ክበብ ወደ ህንድ የመርከብ ስቅጣጫ መሪዎች ብዙ ጊዜ ገና በምስፈሙ ሁነዉ እያስ እራሳቻውን በምስፈቁ የወደብ ክፍል እንደሆኑ ስድርገዉ ያስባሉ፤ እና ወደ ስፍፈካም ባህር ዳርቻ ደጓዛሉ፤ ከጀርባቸው ተቀምጦ እያስ ማስት ነው፤ ደህም ክስተት በዚሁ ግምታቸው መሰረት ነው። ደህ መጥፎ እድል ስፈጣኑ የጦር መርከብ ተወዳዳሪም ተከስቷል። በ1845 እንዴት የግርማደነቷ ድል ስድራጊ መርከብ ሊጠፋ ቻለ? እንዴት የብዙ ባላባት መርከቦች በስነስርዓት ተሰርተው በደንብ የሰለጠነ ሰው ደዘው፤ ትክክለኛ ስቅጣጫ ጠቋሚዎች ተቀምጠው፤ በፈጋ የስየር ሁኔታ መርከቦቹ ደሰበራሉ፤ በመጀመሪያ በባህር ዳርቻዎች በኋላ ደግሞ በውሃ በተሸፈኑ ድንጋዮች ከግምታቸው ውጭ ሁኖባቸው መርከቦቹ ደመታሉ፤ ደዛ በምሽት ወደም በጭጋግ ቀን ብቻ ስደደስም፤ በስፈሙ ብርሃናማ የቋሃደ ቀንም እንጅ? ቀላሉ መልስ ምድር ኪስ ስላልሆነች ነዉ።››



39) ተግባራዊ እርቀቶች ልኬታ ‹‹**The Australian Handbook, Almanack, Shippers' and Importers' Directory**›› እንዳስቀመጠው፤ ከሲድኒ ወደ ኔልሰን ቀጥተኛው እርቀት 1,550 ማየል እንደሆነ ነዉ የተረቀቀው፤ በኬንትሮስ ያላቸው ልዩነት 22 ዲግሪ *2'14"* ተብሎ ነው የተሰጠው፤ ስለዚህ ከ 360ው 22 ዲግሪ *2'14"* 1,550 ማየል ከሆነ፤ አጠቃላይ ልኬታው 25,182 ማየል ይሆናል። ይህ ልኬታ ኪሷ ዓለም ከወገቧ በኩል ካለው የበለጠ ነው ብቻ ሳይሆን፤ በመላ 4,262 ማየል ያህል ከሉሳ ደቡባዊ ኬክሮስ ሲድኒ ከሚኖረው ድርሻ የበለጠ ነው።

40) ከቅርብ ኬፕሆርን ችሊ ወደ ፖርት ፊሊፕ በሜልቦርን አውስትራሊያ፤ እርቀቱ 10,500 ማየል ነው፤ ወይም 143 ዲግሪ ኬንትሮስ ይርቃል፤ ለቀሪው 360 ዲግሪ የሚኖረውን ለማወቅ ስናባዛ፤ በአጠቃላይ 26,430 ማየል በዚህ ኬክሮስ ዙሪያ ይኖራል ማለት ነው። ምድር ከወገቧ በኩል ይኖራታል ከሚባለው ዙሪያ በ1,500 ማየል የበለጠ ነው። የዚህ አይነቱ ደቡብ ኬክሮስ ሊኖረው ከሚገባው ዙሪያ በብዙ ሺህ ማየል የበለጠም ማለት ነው።

41) ተመሳሳይ የሆነ ስሌት ከኬፕ አፍ ጉድ ሆፕ በደቡብ አፍሪካ ወደ ሜልቦርን አውስትራሊያም ተሰርቷል፤ በአማካኝ የ35.5 ዲግሪ ደቡብ ኬክሮስ እንዲሁ በአቅራቡ ከ25,000 ማየል በላይ የሆነ ውጤት ነው የሰጠው። አሁንም ለምድር አለ ከሚባለው ትልቁ ዙሪያ ጋር የተካከለ ወይም የበለጠ ነው። ከሲድኒ አውስትራሊያ ወደ ዋሊንግቶን ኒውዚረላንድ በተሰራ ስሌት፤ በአማካኝ የ37.5 ዲግሪ ደቡብ፤ በአቅራቡ ወደ 25,500 ማየል ሰጥቷል። አሁንም የበለጠ ነው፤ እንደ ኪሷ ዓለም ንድፈ ሃሳብ፤ የምድር ዙሪያ 37.5 ዲግሪ ደቡብ ኬክሮስ ላይ የጸደቀ የ19,757

ማየል ብቻ ነበር ሊኖር የሚገባው፤ ወይም ከእንደዚህ አይነቱ ልኬታ በስድስት ሺህ ማየል ያነሰ ማለት ነው።

42) በኳሷ ዓለም አንታርክቲካ የበረዶ ክምር ያለበት አህጉር ሁና፤ የኳሱን ዓለም ቁጥ ሸፍና ከ78 ዲግሪ ደቡብ ኬክሮስ እስከ 90 ዲግሪ ባለው ትገኛለች፤ ይህም ማለት ከ12,000 ማየል በላይ የሆነ ዙሪያ አይኖራትም ማለት ነው። ነገር ግን በቅርቡ ብዙ አሳሾች ካፒቴን ኩክን እና ጀምስ ክላርክ ሮስን ጨምሮ አንታርክቲካን ለመዞር ባደረጉት ጉዞ፤ ከ 3 እስከ 4 ዓመታትንና 50-60,000 ማየሎችን ወስዶባቸዋል። የብሪቲሹ ዋና መርከበኛም ቀጥተኛ ያልሆነ ግን የተሟላ ዙሪት በአንታርክቲካ ላይ 69,000 ማየሎችን አቋርጦ ዙሯል፤ እነዚህ ሁሉ እርቀቶች ግን ከኳሷ ዓለም ጋር የሚጣረሱ ናቸው።

43) ምድር ኳስ ከነበረች፤ በደቡብ ንፍቀ ክበብ ፈጣንና ቀጥተኛ በሆነ መንገድ አንታርክቲካን በማቋረጥ ጊዜና ነዳጅ መቆጠብ የሚያስችሉ ብዙ በረራዎች ነበሩ። ለምሳሌ ከሳንቲያጎ ችሊ ወደ ሲድኒ አውስትራሊያ አንታርክቲካን በማቋረጥ አጭርና ፈጣን በረራ ከማድረግ ይልቅ፤ ሁሉም በረራዎች ወደ ላይ ሰሜኑን ክፍል ዙረው ይጓዛሉ። ለዚህም የአንታርክቲካ በጣም ቀዝቀዛ የሆነ የአየር ንብረት ለአውሮፕላን ጉዞ የማይቻል እንዳደረገው ይገልጻሉ፤ የማይካደው ሃቅ ግን፤ ናሳ ወደዚህ ቦታ ለቁጥር የሚያዳግቱ በረራዎችን እያደረገ መሆኑ ነው፤ ለዚህ ጥያቄም፤ አየሮች በጣም ቀዝቃዛ እና በጣም ሞቃት ቦታዎች ላይ ለመብረር የሚያስችላቸውን ቴክኖሎጅ ለመፍጠር የሚደረግ ሙከራ እንደሆነ ነው ናሳ የሚመለሰው። የዚህ አይነት ማስተባበያዎች ግን እንዲሁ ማስተባበያ ብቻ ናቸው፤ እውነታው ደግሞ ምድር ኳስ ቅርጽ ስላልሆነች እና ስለማይቻል ነው።



44) ምድር ኳስ ከነበረች እና በአንታርክቲካ ላይ ለመብረር ያልተቻለው በጣም ቀዝቃዛ የአየር ንብረት በመኖሩ ከሆነ፤ ከሲድኒ ወደ ሳንቲያጎ ለመጓዝ ብቸኛው ቀጥተኛ መንገድ ፓስፊክን ማቋረጥ ሲሆን፤ እንዲሁ ነዳጅ መመላትም ግዴታ አስፈላጊ ሁኖ ከተገኘ፤ በኒውዘርላንድ ውይም በሌሎቹ መዳረሻዎች መመላት ይቻል ነበር። የደቡቡን ንፍቀ ክበብ ሳንለቅ ማለት ነው። አሁን ባለው እውነታ ግን ከሲድኒ ሳንቲያጎ ለመብረር፤ ወደ ሰሜኑ ንፍቀ ክበብ ተጉዞ በላክስ ወይም በሌላ የሰሜን አሜሪካ አየር መንገዶች ካረፈ በኋላ ተመልሶ ታች ወደ ደቡብ ንፍቀ ክበብ ይቀጥላል። እንደዚህ ዙሮ የተጠመዘዘ የቀሸመ በረራ በኳሷ ዓለም ላይ ምንም ስሜት አይሰጥም። ነገር ግን በገዘርጓ ዓለም፤ በትክክል ሁለቱን ሀገራት ለማገናኘት ቀጥተኛው መንገድ ሁኖ እናገኘዋለን።



45) በኳሷ ዓለም ከጆሀንስበርግ ደቡብ አፍሪካ ወደ ፐርዝ አውስትራሊያ ለመብረር፤ ቀጥታ የህንድን ውቅያኖስ በማቋረጥ ለነዳጅ መመላትም ምቹ ሁነው የሚገኙትን ማርቱስ ወይም ማዳጋስካርን መጠቀም ይቻል ነበር። በእውነታው ግን ሁሉም ከጆሀንስበርግ ወደ ፐርዝ የሚደረጉ በረራዎች፤ ዱባይ፣ ሆንግኮንግ ወይንም ማሊዥያ ላይ ማቆሚያቸቀውን ያደርጉና ተመልሰው ወደ ደቡብ ንፍቀ ክበብ ይበራሉ። ይህ በኳሱ ዓለማችን ላይ ትርጉም የማይሰጥ በረራ ሲሆን፤ በዝርጓ ዓለም ግን በቀላሉ የምንረዳው ምክንያት ይሆናል።

46) በካሷ ዓለም ከኬፕታውን ደቡብ አፍሪካ ወደ ቦነሳይረስ አርጀንቲና ለመብረር፤ በተመሳሳይ የኬክሮስ መስመር ላይ ቀጥታ አትላንቲክን በማቋረጥ ይሆን ነበር። በዚህ ፋንታ ግን ሁሉም በረራዎች ማቆሚያቸውን በማንኛውም በለንደን፣ በቱርክ ወይም በዱባይ እያደረጉ በመጀመሪያ ወደ ሰሜኑ ንፍቀ ክበብ ማገናኛ ስፍራ ይሄዳሉ። በድጋሜ ይሄ በሉሳ ዓለም በጭራሽ ስሜት የማይሰጥ ጉዳይ ነዉ። በዝርዝ ዓለም ካርታ ላይ ሲታይ ግን ሙሉበሙሉ የሚገባን ነው።

47) በካሷ ዓለም ከጆሀንስበርግ ደቡብ አፍሪካ ወደ ሳኦፓሎ ብራዚል ቀጥታ 25ኛውን የደቡብ ኬክሮስ ይዞ በመብረር ቶሎ መድረስ ይቻል ነበር። በዚህ ፋንታ ግን በብዛት ሁሉም በረራውች መጀመሪያ በሰሜኑ የ50ኛው ዲግሪ ኬክሮስ ለንደን ላይ ለነዳጅ መሙላት ይቆማሉ። ለእንደዚህ አይነቱ የተጃጃለ ማቆሚያ ብቸኛው ምክንያት ምድር ዝርግ መሆኗ ነው።

48) በካሷ ዓለማችን ከሳንቲያጎ ችሊ ወደ ጆሀንስበርግ ደቡብ አፍሪካ ለመብረር፤ ከትሮፒክ አፍ ካፕሪኮርን መስመር በታች ያለውን የደቡብ ንፍቀ ክበብ በመጠቀም በፍጥነት መድረስ የሚቻልበት ቀላል በረራ ይሆን ነበር። ነገር ግን የተዘረዘሩት በረራዎች በተለየ አካሄያድ ወደ ሰሜን ንፍቀ ክበብ ተጠግታ ባለችው ሴኔጋል ላይ ነዳጅ ሞልተው ይመለሳሉ። በዝርዝ ዓለም ካርታ ላይ ሁነን ስናየው ግን ምክንያቱ ግልጽ ነው። በቀጥታ በረራ ሴኔጋል በሁለቱ ሃገራት መካከል የምትገኝ መዳረሻ እንደሆነች እንረዳለን።

49) ምድር የምትሽከረከር ኳስ ሁና 93 ሚሊየን ማየል እርቃ ከምትገኘው ፀሐይ ብርሃን እያገኘች ከሆነ፤ እንዴት በአንድ ጊዜ የሚያቃጥል በጋ በአፍሪካ፣ ከጥቂት ሺህ ኪሎሜትሮች በኋላ ደግሞ አጥንት የሚሰብር በረዷማ ክረምት በአርክቲክ/አንታርክቲክ የለም የሚያስብል የፀሐይ ሙቀት ሊያገኙ ቻሉ?፤ ከፀሐይ ያለው ሙቀት 93,000,000 ማየል ተጉዞ የሳህራ በርሀ ከደረሰ፤ 4,000 ማየል ለምትርቀው የ(0.00004%) ልዩነት አንታርክቲካ የሚደረሰው የሙቀት መጠን እና ጥብቅ የሆነ ልዩነት ውጤቱ ነው ብሎ ማሰብ የማይመስል ነገር ነው።

50) በእውነት ምድር ሉል ከነበረች፤ የአርክቲክ እና የአንታርክቲክ ዋልታ ቦታዎችና እንዲሁ በሰሜንና በደቡብ የምድር ሰቅ ያሉ ተነጻጻሪ የኬክሮስ ስፍራዎች፤ ተመሳሳይ የሆነ የአየር ሁኔታ እና ጸባይ ሊጋሩ ይገባ ነበር፤ እንደዚህ ተዛማጅ የሆነ የሙቀት መጠን፣ የወቅት መቀየር፣ የቀን እርዝማኔ፣ እጽዋት እና የእንሰሳት ህይወት ሊኖራቸው ይገባ ነበር። በእውነታው ግን አርክቲክ እና አንታርክቲክ ሰሜን/ደቡብ የምድር ሰቅ ኬክሮስ ክፍሎች፤ በብዙ ሁኔታ በትልቁ ይለያያሉ ከኳሷ ሞዴል ጋር ሙሉበሙሉ አይመጣጠኑም። ከዝርጉ ሞዴል ጋር ግን ሙሉበሙሉ የሚገጥም ነው።

51) አንታክርቲካ በምድር ላይ በጣም ቀዝቃዛዋ ቦታ ስትሆን፤ በአማካኝ አመታዊ ሙቀት -57 ዲግሪ ፋራናይት እና ከሪከርድ ዝቅተኛው ደግሞ -135.8 ነው፤ የሰሜን ዋልታ አማካኝ አመታዊ ሙቀት ግን በአንጻሩ 4 ዲግሪ ሞቃት ነው፤ በአመት ውስጥ የአንታርክቲክ የሙቀት መጠን ከተነጻጻሪው የአርክቲክ ኬክሮስ ከግማሽ በታች በማነስ ይለያል፤ ሰሜኑ የአርክቲክ ክፍል መካከለኛ ሞቃት በጋ እና ቀለል ያለ ክረምት ያገኛል፤ በአንጻሩ ግን የደቡብ አንታርክቲክ ክፍል የሚዘንበውን በረዶ እስከማቅለጥ የሚያደርስ ሙቀት እንኳን የለውም። በፀሐይ ዙሪያ አጋድላ ወጥ ሁና እየተገላበጠች በምትሽከረከረው ኳሷ ዓለም የአርክቲክ እና አንታርክቲክ የሙቀት መጠንና ወቅቶች እንደዚህ መለያየት አልነበረበትም።

52) አይስላንድ በ65 ዲግሪ ሰሜን ኬክሮስ ለ870 የእጽዋት ዝርያዎችና ለብዙ የተለያዩ እንስሳቶች ቤት ነው። ይህን ከ 54ኛ ዲግሪ ደቡብ ኬክሮስ የጆርጅያ ደሴቶች ጋር ስናወዳድረው፤ 18

የእጽዋት ዝርያዎች እና በጣም ትንሽ የለም የሚያስብል የእንሰሳት ህይወት ነው የሚገኘው፤ በተመሳሳይ ኬክሮስ ሰሜን ግን እንደ ካናዳ ወይም ኢንግላንድ ባሉት ግዛቶች፤ ብዙ ጥቅጥቅ ያሉና የተለያዩ እረዛዝም ዛፎች የሚገኙበት ስፍራ ነው። ዝነኛው ካፒቴን ኩክ፤ ስለ ጆርጅያ ለጥርስ መፋቂያ የሚሆን አንድም ቁጥቋጦ እንኳን ማግኘት እንዳልቻለ ጽፏል፡ ኩክ ሲዕፍም፡- ‹‹ስንድም የሚታደ ዛፍ ስልነበረም፤ ወደ ደቡብ የተቀመጠዉ መፈት በዘላቂዉ የደጋ በረዷማ ቀዝቃዜ በተፈጥሮዉ የጠፋ ነዉ፤ ሞቃቱ የፀሐደን ጨረር እንዲሰማ ስያስችልም፤ እንደዚህ የሚያስጨንቀውንና ስስፈፉ ሁኔታ ስመግለጽ ቃላት የለኝም። በስንዳንድ ሰፋ ባሉት ስሙላላ ስፍራዎች እንኳ የባህር ላደ ህደጠት የሳሳ ነው፤ የባህር ወፍም እምብዛም ነው፤ በበረዶ በተሸፈነው ስፍራ ብቻውን የሚበር ወፍ ነው የተመስከትኩት። በስርክቲክና በስንታርክቲክ ዞኖች ያስው የተፈጥሮ ህደጠት መጠን ንጽጽር በጣም ስስደናቂ እና ትልቅ ትርጉም ያስው ነው።››



53) በተነጻጻሪ ኬክሮስ ሰሜን እና ደቡብ፤ ፀሐሃይ በምትሽከረከር ኳስ ምድር የማይጠበቅ በጣም የተለየ ጸባይ ታሳያለች፤ ነገር ግን በዝርዝ ዓለም በትክክል መሆን ያለበት ሁኖ እናገኘዋለን፤ ለምሳሌ ለሰሜኑ የምድር ሰቅ እረዝመ የበጋ ቀን ከደቡቡ የምድር ሰቅ እጅግ በጣም የበለጠ ነው። እንዲሁ የሰሜኑ የምድር ሰቅ አጭሩ የክረምት ቀን ከደቡቡ የምድር ሰቅ አጭር ቀን እጅግ በጣም ያጠረ ነው። ይሄ እየተገላበጠች በአንድ ወጥ ፍጥነት ለምትሽከረከር ኳስ ምድር በፍጹም ሊገለጽ የማይችል ነገር ነው። በዝርዝ ዓለም ሞዴል ግን ፀሐይ ከትሮፒክ እስከ ትሮፒክ ክብ እየተጓዘች ስታበራ በትክክል የሚገጥም ክስተት ነው።

54) ተነጻጻሪ በሆነ ኬክሮስ ላይ በሚገኙ ደቡብና ሰሜን ቦታዎች፤ በምትሽከረከረው ኳሷ ዓለም የማይጠበቅ የንጋትና የምሽት ልዩነት አለ። ይህ ግን በዝርዝ ዓለም የሚጠበቅ ልዩነት ነው፤ በሰሜኑ ንጋትና ምሽት ቀስ እያለ መጥቶ ከደቡቡ አንጻር እረዝም ለሚባል ጊዜ ይቆያል። በደቡብ ግን ንጋትና ምሽት ቶሎ ወጥቶ ቶሎ ይገባል። በአንዳንዶቹ የሰሜን ክፍሎች የፀሐይ ጥልቀት(twilight) ከአንድ ሰዓት በላይ መቆየት ይችላል፤ በተነጻጻሪ ኬክሮስ ደቡብ ላይ ግን በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ትጠልቃለች። ይህም በአንድአይነት ፍጥነት አጋድላ በምትሽከረከር ኳሷ ዓለም ሊገለጽ የማይችል ነው። ነገር ግን በዝርዝ ዓለም ፀሐይ በፍጥነት በደቡብ ሰፊውን የትሮፒክ አፍ ካፕሪኮርን መስመር ስትዞር እና ቀስ ብላ ደግሞ በሰሜን ጠባቡን የካንሰር መስመር ስትዞር በትክክል የሚጠበቅ ክስተት ነው።



55) ፀሐይ በየ24 ሰዓቱ በምድር ክበብ ዙሪያ የምትጓዝ ከሆነ፤ በየ6 ወሩ ያለአፍታ ከትሮፒክ እስከ ትሮፒክ እየተጓዘች፤ የሰሜኑ መካከለኛው ክፍል ከደቡቡ ዙሪያ ክፍል ይልቅ በጣም ብዙ ሙቀትና የፀሐይ ብርሃን ያገኛል። በ24 ሰዓት ውስጥ ለመሸፈን ሰፊውን የደቡብ ክፍል በፍጥነት መዞር ስላለባትና በተመሳሳይ የ24 ሰዓት ድርሻ ጠባቡን የሰሜን ክፍል በአንጻራዊ ፍጥነት መዞር ስላለባት ነው። ይሄ በአርክቲክ/አንታርክቲክ የሙቀት መጠን፤ ወቅቶች፤ የቀን እርዝማኔ፤ የዕጽዋት እና የእንስሳት ሕይወት ልዩነቶች መፈጠር ምክንያት በትክክል የሚያስረዳ ነው። ለዚህ ነው የአንታርክቲክ ጥዋት ንጋት እና ምሽት ድንግዝግዝታ ከሰሜኑ ጋር ሲነጻጸር በጣም ፈጣን የሆነው። ይሄ በአርክቲክ መሃል በጋ ወቅት ለምን ፀሐይ ከነጭራሹ እንደማትጠልቅም ያስረዳል።



56) በአርክቲክ የ‹‹እኩለሌሊት ፀሐይ›› ክስተት፤ በበጋ ፀሐይ ከምድር ወገብ በጣም በምትርቅባቸው ሁለት ጊዜያት በየዓመቱ ለተከታታይ ቀናቶች ይከሰታል። ተመልካች ከሩቅ የሰሜኑ ክፍል ድረስ በቀኑ ውስጥ ፀሐይ ከፍና ዝቅ እያለች በሰማዩ ላይ ክብ ስትዞር መሉበመሉ ግን ሳትጠልቅ 72+ ለሚቀጥል ሰዓታት ማየት ይችላል። ምድር በፀሐይ ዛቢያ እየዞረች የምትሽከረከር ሉል ከነበረች፤ እንደዚህ አይነቱ የእኩለሌሊት ፀሐይ ክስተት ሊሆን የሚችለው በዋልታዎቹ ብቻ ይሆን ነበር። በየትኛውም ወደታች ከ89 ዲግሪ ኬክሮስ የተመቸ ቦታም፤ ምንም አይነት ዝንባሌ ወይም ማጋደል ቢኖርም ለተከታታይ 24 ሰዓታት ፀሐይን ሊያዩ አይችሉም ነበር። በምትሽከረከረው ሉል መላውን የፀሐይ ዙሪት እዚህ ከዋልታው የራቀ ቦታ ላይ ለማየት፤ በብዙ ማየሎች ውስጥ ባለ መሬትና ባህር ውስጥ ማየት መቻል አለብን ማለት ነው። ይህም የዙሪቱን አንድ ክፍል ብቻ ለማየት ነው።››

57) ተቋመ፡ በአንታርክቲካ የእኩለሌሊት ፀሐይ እንደሚያጋጥም ይናገራል፤ ነገር ግን እነርሱ በሚያመች ሁኔታ ይሄንን የሚያሳይ ያልተቆረጠ ቪዲዮ የላቸውም፡፡ በተጨማሪም በክረምት የዚህ ወቅት ይሄንን አባባል ለማረጋገጥም ሆነ ለመቃወም ማንም ነጻ የሆነ አሳሽ ወይንም ተንቫር ወደ አንታርክቲካ እንዲጓዝ መብት የለውም/አይፈቅድም፡፡ በተቃራኒው በህዝብ ዘንድ የተገኘ የአርክቲክን የእኩለሌሊት ፀሐይ የሚያሳይ ያልተቆረጠ ደርዘን ቪዲዮ አለ፤ ይህም ያለምንም ቅሬታ የተረጋገጠ ነው፡፡

58) ንጉሳዊው የቤልጀም የጅኦግራፊ ማህበር በእነርሱ የ ‹‹**Expedition Antarctique Belge**›› በስባዱ የአንታርክቲክ ክረምት ወቅት እንደመዘገቡት፤ ወደታች ከ71ኛ ዲግሪ ደቡብ ኬክሮስ ከግንቦት 17ኛው ቀን እስከ ሀምሌ 21 መጀመሪያ፤ ፀሐይን ከአድማስ በላይ ማየት አልተቻለም/አልነበረችም፡፡ ይሄ ለኪሷ ዓለም ንድፈ ሃሳብ መሉበመሉ እንግዳ ነገር ነው፤ በዝርዝ ዓለም ሞዴል ግን በቀላሉ የተባራራ ጉዳይ ነው፡፡ የእኩለሌሊት ፀሐይ፤ በመጨረሻ የሰሜን ኬክሮስ ትልቅ ከፍታ ላይ በአርክቲክ በጋ ወቅት ይታያል፤ ምክንያቱም ፀሐይ በውስጠኛው ክብ መስመር ጠባቡን ክብ ይዛ መሀል በዋልታው አካባቢ እየዞረች ስለሆነ፤ ለዚህ አይነቱም የተመቸ ቦታ የፀሐዮ ክስተት ከአድማሱ በላይ የሚታይ ሁኖ ይቀመጣል፡፡ ልክ እደዚሁ ሁሉ በአርክቲክ በጋ ወቅት፤ በሩቅ ደቡብ ኬክሮስ ለሚገኙ ሀገራት ፀሐይ መሉበመሉ ከሁለት ወር በላይ ትጠፋለች፤ ምክንያቱም በሰሜኑ ትሮፒክ ስለምትሆን፤ በውስጠኛው ክበብ የመመላለስ ጉዞ ፀሐይ የሰሜኑን መሃል በጣም አጥባ ስለምትዞር ከደቡቡ ዙሪያ ለማየት አያስችልም፡፡

59) ከጋብሪል ሄንሪት አባባል ‹‹የምድር መሽከርከር ንድፈ ሃሳብ የሚከተሉትን የሚያጋጥሙ ነጥቦች በመጥቀስ ስለንዴና ስመጨረሻ ጊዜ በእርግጥም ከንቱ እንደሆነ ሲገለጽ ይገባል፡፡ የእሽክርክሪቱ ፍጥነት ወጥ ነው እና ሃያአራት ሰዓት ደመስዳል ተብሏል፤ በዚህ ጊዜ በአመት ውስጥ ቀንና ሌሊት እያንዳንዳቸው እንድአደነት የስአራሁስት ሰዓት ቆይታ ደኖራቸው ዘንድ ግድ ነው፡፡ ፀሐይ ሁልጊዜ በእንድአደነት ሰዓት ጥዋት መዉጣትና በተመሳሳይ ሰዓት ማታ መግባት ስለባት፤ በዚህ ውጤት ሁልጊዜ ከመስከረም 1ኛ እስከ ጳጉሜ 5ኛው በሁሉም ቀን (equinox)ቀንና ሌሊት እኩል የሚሆንበት ጊዜ ደሆን ነበር፡፡ እንዴ፡- ምድር የመሽከርከር እንቅስቃሴ ስላት፡ ከማስቱ በፊት፤ እዚህጋ ማቆምና ደህንን መገንዘብ ስስበት፡፡ ምድር በሃያአራት ሰዓት ውስጥ በእንድ ወጥ ፍጥነት የምትሽከረከር ከሆነ፤ እንዴት የስበት ህግ በቀንና ሌሊት እርዝማኔ ስመቀቶች ልዩነት መግስጫ ደሆናል!?››



60) ማንም የባህሩን አድማስ መሉበመሉ ቀጥተኛ እንደሆነና ምድር መሉበመሉ ዝርግ እንደሆነች፤ ጣውላና ባለሶስት እግር የካሜራ ማስቀመጫን ብቻ በመጠቀም ማወቅ ይችላል፡፡ ከባህር ጠለል በላይ በማንኛውም ከፍታ ከ6-12 ጫማ እረዝም ቀጥ ያለ ጣውላን ቁመታቸው እኩል በሆነ ሁለት የቆሙ እንጨቶች ላይ በማጋደም፤ ከጀርባ በባለ ሶስት እግሩ የካሜራ ማስቀመጫ የሰማዩን አግድም መመልከት፤ የአድማሱ ዳራ ሁልጊዜ ከላይኛው የጣውላ ጫፍ ጋር ትይዩ(parallel) ሁኖ ይስለፋል፡፡ በጣውላው የላይኛው ጫፍ በኩል እየተመለከትን፤ ከጣውላው አንዱ ጫፍ እስከ ሌላኛው ጫፍ በግማሽ ክብ ቅርጽ እየተንቀሳቀስን እያየን ብንንዝ፤ እንደያለንበት ከፍታ ከ10-20 ማየል ግልጽ ዝርግ የሆነ ዱካ እንከተላለን፡፡ ምድር 25,000 ማየል ዙሪያ ያላት ሉል ብትሆን ኑሮ፤ ይህ የማይቻል ነገር ይሆን ነበር፡፡ አድማሱ ከመሃከለኛዉ የጣውላ ቦታ ጋር አንድ ላይ ሁኖ፤ በሁለቱ ጫፎች በኩል ግን በቀላሉ በሚታይ ሁኔታ ዝቅ ማለት ነበረበት፤ እስከ ሁለቱ የጣውላ ጫፍ ትይዩ የሆነው የአስር ማየል ዝርግ አድማስ፤ በሁለቱም ጫፍ በቀላሉ የሚስተዋል መጠምዘዝ ወይም ዝቅታ ይኖረው ነበር፡፡ ከመሃከለኛው በሁለቱም ጫፍ የ66.6 ጫማ ዝቅታ እንዲኖረው ግድ ስለሆነ፡፡



61) በእውነት ምድር ትልቅ ኳስ ሁና 25,000 ማየል ዙሪያ ቢኖራት፤ አድማሱ ከባህር ከፍታ ላይ እንኳ በቀላሉ በሚስተዋል

መጠምዘዝ ይሆን ነበር። ወደ አድማሱ እየተጠጋ የሄደ ማንኛውም ነገር ከእይታችን አንጻር ቀስበቀስ ወደኋላ ዘምበል ያለ ሁኖ ይታይ ነበር። እሩቅ ወደ አድማሱ ያሉ ህንጻዎች ከተመልካቹ ወዲያ አዘንብለው ሊወድቁ ያሉ ማማዎች ይመስሉ ነበር። በኳኋ ዓለም የሙቅ አየር ባሉን ተነስታ እየተንሳፈፈች ያለማቋረጥ ከእኛ እየራቀች ስትሄድ፤ በቀጣይነት ቀስበቀስ ወደኋላ እያዘነበለች በጣም እየራቀች በሄደች ቁጥር የባሉኗ የላይኛው ክፍል እየጠፋ ይሄድና የቅርጫቱ ቂጥ ብቻ እየታየ ይመጣል። በእውነታው ግን ማንኛውም ህንጻ፣ ባሉን፣ ዛፍ፣ ሰዎች እና የትኛውም ነገር፤ ለየትም ተመልካች፣ እርቀትና ቁመት ከምድር/ከአድማሱ በቀጥተኛ ማዕዘን ቁመው ይገኛሉ።

62) የሳሙኤል ሮባተም ሙከራ፤ በ6 ማየል እርቀት ውስጥ ያለ የቦይ ውሃ ቀጥተኛ(ዝርግ) እንደሆነ ያሳየ ነበር። በመጀመሪያ ሳሙኤል በ8 ኢንች ከፍታ ቴሌስኮፑን በውሃው ላይ ተክሎ ቆመ፤ ጓደኛው ታንኳ ላይ 5 ጫማ ቁመት ያለው ባንዲራ አቁሞ ለ6 ማየል እራቀ፤ ምድር ኳስ ከነበረችና 25,000 ማየል ዙሪያ ካላት፤ ለ6 ማየል የተዘረጋው ውሃ የ6 ጫማ ጉብታ(arc) ሊኖረው ሲገባ፤ ታንኳው ከነባንዲራው ከእይታ በታች መሆን ነበረበት። ዳሩ ግን ሙሉበሙሉ ታንኳውን ከነባንዲራው በተመሳሳይ ከፍታ ሁኖ ለስድስት ማየል እርቀት ማየት ተችሏል።



63) በሁለተኛ ሙከራ ዶክተር ሮባተም ባለ 5 ጫማ ከፍታ ቋሚ ባንዲራዎችን ባህር ዳርቻ ላይ በየአንዳንድ ማየል ልዩነት ከተከላቸው በኋላ፤ ቴሌስኮፑን በ5 ጫማ ከፍታ ከመጀመሪያው ባንዲራ ጀርባ አቁሞ፤ በትክክለኛ ቀጥታ መስመር የተደረደሩትን 6 ባንዲራዎች ማየት ችሏል። ምድር 25,000 ማየል ዙሪያ ያላት ኳስ ብትሆን፤ ባናዲራዎቹ ከመጀመሪያው የቆመ ባንዲራ እይታ በኋላ፤ በየእርቀታቸው ወደታች ዝቅ እያሉ ሁለተኛው 8 ኢንች ወደታች ዘቅጦ፣ ሶስተኛው 32 ኢነች፣ አራተኛው 6 ጫማ፣ አምስተኛው 10 ጫማ ከ8 ኢንች እና ስድስተኛው 16 ጫማ ከ8 ኢንች ወደታች ሁነው ይታይ ነበር።



64) በ ‹‹Earth Not a Globe!›› ከሳሙኤል ሮባተም አባባል ‹‹መሬት ሳጽ ሳስ ተመልካች በየትኛውም ቀኝና ግራ እርቀት ቢስጠጥ፤ የባህረ ስጽማስ ምንጊዜም ቀጥተኛ መስመር ሁኖ እንደሚታይ የታወቀ ነው። የሚከተሰው ሙከራ በተስያዩ የሀገር ክፍሱች ተፈትኖ ነበር፤ በብራዶግችን በሰፈው ሚዳ፤ መርጫ ትራኩ ስቀራቢያ፤ ምድር ሳጽ ሁስት ግንዶች በ6 ያርድ ልዩነት ከባህረ በተቃራኒ ስቀጣጫ በኩል ተተክሱ፤ እናም በሁስቱ ግንዶች መካከል ከስድማሱ ጋር ትጽዩ የሆነ መስመር ተጠረ የመስመረ መሃከስኛው ክፍል ከ20 ማየል ያሳነሰ እጽታ ስቀፍ ጽጽዛል በሙሱጫ የ40 ማየል እርቀት የሸፈነ ሲሆን፤ መርከብ ቀጥታ ወደ ምስራቅ በኩል ሲጓዝ ታጽታል፤ መስመረ የመርከቡን ቋሚ ምሰሶ ከመርከቡ ወገብ በሳጽ ጥቂቱን ክፍል ጋረጽ፤ ስብዙ ሰዓታት መርከቡ 40 ማየሱን እስከሚያልፍ ድረስ የምሰሶው ጫፍ ተጋርጾ ስስፈ፤ መርከቡ ከምስራቅ እየመጣ ወደ እጽታ ሲገባ፤ ስ20 ማየሱች የጉብታው መካከስኛ ቦታ እስኪጽርስ ድረስ፤ ስዘንብሱ ከተዳፋት ቦታ ወጽሳጽ እየጠጣ መሆን ነበረበት፤ ጽህም ማስት ስተመሳሳጸ የ20 ማየል እርቢ ሁስት በ8 ሲንች ተባዝቶ በሚሰጠን 266 ጫማ ዝቅታ፤ 40 ማየል በሸፈነዉ መስመር የመጀመሪያው ጫፍ እና በሲሳኛው ጫፍ መርከቡ ከመስመረ በታች ስእጽታ ዝቅተኛ ቦታ ሳጽ መሆን ነበረበት።››

65) በተጨማሪም ዶ/ር ሮባተም ከጠቀሰው ‹‹ከሰሜን ሲቨርፑል በጥቂት ማየሱች እርቀት በዋተርሱ ስቀራቢያ በሚገኝ ባህር ዳርቻ ጥረ ቴሌስኮን ከሙሃው በሳጽ በ6 ጫማ ከፍታ ተተክስ፤ ስቀጣጫውን የመርሲን ወንዝ ስቅ ወደ ጾብሲን ወጽሚጓዝ ትልቅ በስንፋሱት ወጽሚሰፈ መርከብ ተጽደገ፤ ቀስበቀስ እየተገተተ የሚርቀው የመርከቡ ጫፍ ወደ ስድማሱ እየተጠጋ፤ ከስፈት ሰዓት በሳጽ ከሚሆን እረዝም ጉዞ ቡኋላ የመርከቡ ፈስ ተሰመረ/ከእጽታ ጠፋ፤ የተስመጸው የጾብሲን መርከብ ጉዞ በሰዓት ውስጥ ሙሱ የስምንት ማየል ነው፤ ስስዚህ የመርከቡ የሳጽኛው ጫፍ ወደ ስድማሱ እስከሚጠጋበት ሰዓት ድረስ በትንሹ የ32 ማየል እርቀት ጽጓዛል፤ በ6 ጫማ ከፍታ የቆመው ቴሌስኮን በከርቩ ምክንያት የሶስት ማየል ዝቅታ ሳጽ ሁኖ እንዲገኝ ግጽ ጽሆናል፤ ስዓያዘጠኙ ማየል እርቢ ሁስት በ8 ሲንች ተባዝቶ 560 ጫማ ሲሰጥ፤ ስመርከቡ ዋና ምሰሶ ቁመት 80 ጫማ ቀንሰን በጽኩልኩስነት ህግ መሰረት በመሳ መርከቡ ስ480 ጫማ ከስድማስ በታች መሆን ነበረበት። በባህር ሳጽ በሚጓዙ መርከቦች ሌሎች ብዙ የዚህ ዓይነት ምርመራዎች ተጽርገዋል፤ እናም ሁሌጊዜ ውጤቱ ሙሱበሙሱ ምድር ሱልነት ከሚስው ንድፌ ሃሳብ ጋር የሚገጥም እጽደስም።››

66) ዶ/ር ሮባተም ቴሌስኮፖችን፣ ውሃልኮችን፣ ሴክስታንት እና ቴዶላይቶችን በመጠቀም ብዙ የተለያዩ ኢክስፐርመንቶችን አካሂጺል። በቀጥታና በአግድም ገጽ ያሉ ማዕዘኖችን ለመለካት የተለየ ጥራት ያላቸውን መሳሪያዎች በመጠቀም በተመሳሳይ ከፍታ ላይ አስቀምጦ ትይዩ ካደረጋቸው በኋላ፤ በተሳካ ሁኔታ በተደጋጋሚ ጊዜ ለማየሉች ምድር ያለምንም ኢንች መጠምዘዝ ሙሉበሙሉ ዝርግ እንደሆነች አረጋግጧል። የእርሱ ግኝት የሳይንሱን ማህበረሰቦች በእጅጉ ያወከ ነበር። ለ30 ዓመት ጥረቱ ምስጋና ይግባውና፤ በ19ኛው ክፍለ ዘመን መግቢያ የምድር ቅርጽ ትልቁ የመወያያ አጀንዳ ሁኖ ቆይቷል።





67) የአየርላንድ ባህር ከማንስ ዶግላስ ሀርቦር ደሴት እስከ ግሬት ኦርም ራስ በሰሜን ዋልስ 60 ማየል ነው። ምድር ሉል ከነበረች፤ ከሁለቱ ባህር ዳርቻ መሀል ቦታ ላይ በ1,944 ጫማ ከፍታ በመካከላቸው ያለው ውሃ የ60 ማየል መጠምዘዝ ይፈጥር ነበር። በጠራ ቀን ከመጠነኛ የ100 ጫማ ከፍታ የግሬት ኦርም ራስ ከዶግላስ ሀርቦር እንደሚታይ በደንብ የሚታወቅ እና በቀላሉ የሚረጋገጥ ነው። ይሄ በ25,000 ማየል ዙሪያ ሉል ሙሉበሙሉ የማይቻል ይሆናል። የ100 ጫማው ከፍታ አድማሱን እስከ 13 ማየል ያሳያል ብለን እያሰብን፤ በቀሪው 47 ማየል የዊልሽ ዳርቻ አሁንም በማይሆን የ1,472 ጫማ ዝቅታ ከእይታ በታች እንዲሆን ግድ ነበር ማለት ነው።



68) የፊላደልፊያ ከተማ ከአፕል ፓይ ኮረብታ በኒዉጀርዚ ፒን ባረን፤ በ40 ማየል እርቀት ውስጥ በግልጽ ይታያል። ሉሏ ምድር 25,000 ማየል ዙሪያ ካላት፤ የአፕል ፓይ ኮረብታ 205 ጫማ ከፍታ ሲኖረው የፊላደልፊያ ከተማ ከ335 ጫማ በላይ በሆነ ጉብታ(curvature) ምክንያት ከእይታ በታች መሆን ነበረበት።

69) የኒዉዮርክ ከተማ ከሀሪማን ብሔራዊ ፓርክ ተራራ፤ በ60 ማየል እርቀት ላይ ሁኖ በግልጽ ይታያል። ምድር ኳስ ሁና 25,000 ማየል ዙሪያ ከነበራት፤ የ1,283 ጫማ ከጫፍ ተራራው ላይ ላለ እይት፤ በፓይታጎሪያኑ ቀመር ወደ አድማስ ያለውን እርቀት ለመወሰን 1.23 ሲባዛ ከቁመቱ እስከዮር ሩት ዉጤት ጋር በጫማ አድርገን፤ የኒዉዮርክ ከተማ ከ170 ጫማ የተጠመዘዘ ምድር በኋላ የማይታይ መሆን ነበረበት።

70) ከዋሽንግተን አስት ኒውጀርዚ በ400 ጫማ ከፍታ፤ በጠራ ቀን ሁለቱንም የኒዉዮርክን እና የፊላደልፊያን ከተማ በተቃራኒ አቅጣጫ በአጠቃላይ በ120 ማየል እርቀት መካከል ማየት ይቻላል። ምድር ኳስ ከነበረችና 25,000 ማየል ዙሪያ ካላት፤ ሁለቱም ከተሞች በ800 ጫማ ጉብታ ከእይታ በታች መሆን ነበረባቸው።

71) ከ60 ማየል እርቀት ባህር ላይ፤ የችካጎን ከተማ በሚሻገን ሃይቅ ላይ ማየት ተችሏል። ይህንንም ክስተት ፎቶ አንስቶ ያቀረበው ፎቶግራፈር ጆሽዋ ኒዊኪን፤ ብዙ የዜና ቻናሎች በፍጥነት ፎቶውን ‹‹superior mirage›› (በመቀት መገልበጥ የሚፈጠር ያልተጠበቀ የአየር ሁኔታ ነጸብራቅ) ነው፤ ሲሉ ገልጸውታል። በርግጥ የዚህ አይነቱ ነገር ይከሰታል፤ ነገር ግን እንደ ጭጋጋማው እውነተኛ ያልሆነ ነጸብራቃዊ ምስል ሳይሆን፤ ጥያቄው ከተማው ሳይዘቀዘቅ ወደ ላይ ቀጥ ብሎ እና ጥርት ብሎ መታየቱ ነው። በኳሷ ዓለም 25,000 ማየል ዙሪያ፤ ለ2,400 ጫማ ከአድማስ በታች መሆን ሲገባው።



72) ጥቅምት 16 1854 የታይም ጋዜጣ ወደ ግሬት ግሪምስቢ የንግስቷን ጉብኝት ዘግቧል፤ ከታችኛው የመርከብ ክፍል በተደረገ ቀረጻ፤ ከ70 ማየል እርቀት ባለ 300 ጫማውን የወደብ ማማ ማየት ችለዋል። በኳሷ ዓለም የ25,000 ማየል ዙሪያ የእነርሱን ከባህር በላይ የ10 ጫማ ከፍታ እና የማማውን የ300 ጫማ ከፍታ ስሌት ውስጥ አስገብተን፤ ከ70 ማየል እርቀት የወደቡ ማማ በመላ የ2,600 ጫማ ዝቅታ ከአድማስ በታች መቅረት ነበረበት።

73) በ1872 ካፒቴን ጊብሰን እና ባልደረቦቹ ‹‹Thomas Wood›› የመርከብ ጉዞ፤ ከቻይና ወደ ለንደን በጠራ ቀን ከ75 ማየል እርቀት የቅድስት ሄለናን ደሴት ማየት እንደቻሉ ሪፖርት አድርገዋል። በልኬታ ወቅት ከፍታቸው ግምት ውስጥ ገብቶ

በኪሷ ምድር የ25,000 ማየል ዙሪያ፤ ደሴቷ ለ3,650 ጫማ ከእይታ በታች መሆን እንደነበረባት ነዉ የታወቀው።

74) ከጌኗ ጣሊያን ከባህር ጠለል በላይ በ70 ጫማ ከፍታ የጎርጎና ደሴት ከ81 ማየል እርቀት ላይ ይታያል። ዓለም ኪስ ከነበረች እና 25,000 ማየል ዙሪያ ካላት፤ ጎርጎና ከ3,332 ጫማ በላይ በሆነ ጉብታ መጋረድ ነበረባት።

75) ከጌኗ ጣሊያን ከባህር ጠለል በላይ በ70 ጫማ ከፍታ፤ ከ99 ማየል እርቀት የኮርሲካ ደሴት ይታያል። ምድር ባለ 25,000 ማየል ዙሪያ ኪስ ከነበረች፤ ኮርሲካ ወደታች 5,245 ጫማ ወይም በሙሉዉ ወደ አንድ ማየል ከአድማስ በታች መሆን ነበረበት።



76) ከጌኗ ጣሊያን ከባህር ጠለል በላይ በ70 ጫማ ከፍታ፤ የካፕሪያ ደሴት በ102 ማየል እርቀት ይታያል። ዓለም ኪስ ሁና 25,000 ማየል ዙሪያ ከነበራት፤ ካፕሪያ በ5,605 ጫማ ጉብታ ውስጥ መሆን ነበረበት።

77) አሁንም ከጌኗ በብሩህ የጠራ ቀን፤ ከግሩም የ125 ማየል እርቀት የኢልባ ደሴት መታየት ይችላል። ምድር ባለ 25,000 ማየል ዙሪያ ኪስ ከነበረች ኢልባ ከ8,770 ጫማ ጉብታ በኋላ መቸም የማትታይ መሆን ነበረባት።

78) ከአንከሬጅ አላስካ በ102 ጫማ ከፍታ፤ ጥርት ባለ ቀን በ120 ማየል እርቀት የሚገኘው የፎርከር ተራራ ያለምንም መሳሪያ በአይን ብቻ ይታያል። ምድር ኪስ ሁና 25,000 ማየል ዙሪያ ከነበራት፤ የፎርከር ተራራ 17,400 ጫማ ከፍታ ሲኖረው፤ በሚፈጠረው የ7,719 ጫማ የተጠመዘዘ ምድር ተጋርዶ ለተመልካች ወደኋላ አዘንብሎ ይሆን ነበር። በእውነታው ግን ተራራው ከመሰረቱ እስከ ጫፉ ድረስ በግልጽ ይታያል ።

79) ከአንከሬጅ አላስካ በ102 ጫማ ከፍታ፤ በጠራ ቀን የሚኪንሊን ተራራ፤ ከ130 ማየል እርቀት ያለመሳሪያ እገዛ በአይናችን ብቻ ማየት ይቻላል። የሚኪንሊ ተራራ እስከ ጫፍ ባለው የ20,320 ጫማ ቁመት ወደ ኋላ ዘንበል ብሎ እና በሚፈጠረው የ9,220 ጫማ የተጠመዘዘ ምድር ምክንያት ግማሽ ክፍሉ ተጋርዶ መታየት ነበረበት፤ በእውነታው ግን ሙሉ ተራራው ቀጥ ብሎ ቁሞ ከመሰረቱ እስከ ላይኛው ጫፍ ድረስ በቀላሉ ይታያል።



80) በየካቲት 1895 በቻምበር መጽሔት፤ በማሪቱስ አቅራቢያ የመርከብ ተጓጉች ህንድ ውቅያኖስ ላይ ለ200 ማየል የሚርቅን መርከብ ማየት እንደቻሉ ሪፖርት አድርገዋል። በወቅቱ ይህ ክስተት በመርከበኞቹ ዙሪያ የጋለ ክርክርን አስነስቷል፤ በተጨማሪ ማስረጃ ሌላ ምስክርነት በአደን የመን ከ200 ማየል እርቀት የጠፋውን የቦምቤ መርከብ ማየት እንደቻሉ ሪፖርት አድርገዋል። ሰውየው በስነስርዓት የመርከቡን ትክክለኛ ገጽታ እና አቅጣጫ በመናገሩ፤ በመጨረሻም ሲደርሱበት አንድላይ በነበሩት ተሳፋሪዎች ትክክለኛ እንደነበር ተረጋግጧል። ምድር ባለ 25,000 ማየል ዙሪያ ኪስ ከነበረች የዚህ አይነቱ እይታ በፍጹም ሊገለጽ የማይችል ይሆናል። ለ200 ማየል የሚርቀው መርከብ ወደ 5 ማየል ወርዶ ከእይታ በታች ይሆን ነበር።

81) በዓለም ላይ የብዙ ላይት ሃውሶች/Light houses ብርሃን እርቀት ከኪሷ ምድር 25,000 ማየል ዙሪያ ባልተመጣጠነ መልኩ ከእሩቅ ባህር ላይ ይታያሉ። ለምሳሌ በደቡብ ፍራንስ የዳንከርኪው ብርሃን ባለ194 ጫማ ከፍታ ሲሆን፤ ከ28 ማየል እርቀት ከጀልባ(ከባህር ጠለል በላይ 10 ጫማ) ላይ ይታያል። በሉላዊ ትሪጎኖሜትሪ ምድር በአንድ ማየል እርቢ ሁለት የ8 ኢንች መጠምዘዝ የምትሰጥ ሉል ከነበረች፤ ይሄ ብርሃን ለ190 ጫማ ከአድማስ በታች ሁኖ ለእይታ መሰወር ነበረበት።

82) የኒኮልሰን ወደብ ብርሃን በኒውዝላንድ ከባህር ጠለል በላይ የ420 ጫማ ከፍታ ሲኖረው፤ ከ35 ማየል እርቀት ይታያል። 220 ጫማ ከአድማስ በታች መሆን ሲገባው።

83) የኢግሮ ብርሃን ከውሃው የ154 ጫማ ከፍታ ላይ ሲሆን፤ በ28 ማየል እርቀት ይታያል። 230 ጫማ ከአድማስ በታች መሆን ሲገባው።

84) በኢስፕላንድ የማድራስ ብርሃን ከባህር ጠለል በ132 ጫማ ከፍታ ሁኖ፤ በ28 ማየል እርቀት ይታያል። 250 ጫማ ከእይታ በታች መሆን ሲገባው።

85) በምዕራብ ፈረንሳይ ባህር ዳርቻ የኮርዶናን ብርሃን ባለ 207 ጫማ ከፍታ፤ ከ31 ማየል እርቀት ይታያል። 280 ጫማ ከእይታ በታች መሆን ሲገባው።

86) በኒው ፋውንድ ላንድ የኬፕ ቦናቪስታ ብርሃን የ150 ጫማ ከፍታ ሲሆን፤ ከ35 ማየል እርቀት ይታያል። 491 ጫማ ከአድማሱ በታች መሆን ሲገባው።

87) በቅዱስ ቦቶልፍ ፓሪሽ ቤተክርስቲያን ቦስተን የእስቴፕል ላይት ሃውስ ከባህር ጠለል በላይ 290 ጫማ ቁመት ሲኖረው፤ ከ40 ማየል እርቀት ይታያል። በሙሉው 800 ጫማ ከአድማስ በታች መሆን ሲገባው።

88) በእንግሊዝ የአይስል ኦፍ ዋይት ላይት ሃውስ ከባህር ጠለል በላይ የ180 ጫማ ቁመት ኑሮት፤ ከ42 ማየል እርቀት ይታያል። እንደ ዘመኑ ጠፈርተኞች አባባል ብርሃኑ ለ996 ጫማ ከእይታ በታች መሆን ሲገባው።

89) በደቡብ አፍሪካ የኬፕ ላቡላስ ላይት ሃውስ የ33 ጫማ ቁመት ሲኖረው፤ በአጠቃላይ ከባህር ጠለል በላይ 238 ጫማ ሁኖ፤ ከ50 ማየል በላይ እርቀት ላይ ይታያል። ምድር ሉል ብትሆን ብርሃኑ ከተመልካች የእይታ መስመር በታች ለ1,400 ጫማ መውረድ ነበረበት።

90) በኒውዮርክ የሚገኘው የነፃነት ሐውልት ቁመቱ ከባህር ጠለል በላይ 326 ጫማ ሲሆን፤ ጥርት ባለ ቀን እስከ 60 ማየል እርቀት ይታያል። ምድር ሉል ብትሆን ኑሮ ሴቷ ነፃነተኛ ከአድማሱ በታች በማይታሰብ የ2,074 ጫማ ዝቅታ ወርዳ ከእይታ ውጭ ትሆን ነበር።



91) በግብጽ የሳይድ ወደብ ላይት ሀውስ የ60 ጫማ ከፍታ ሲኖረው፤ በሚገርም ሁኔታ ከ58 ማየል እርቀት ላይ ይታያል። እንደ ዘመኑ ጠፈርተኞች አባባል ለ2,182 ጫማ ከእይታ በታች መሆን ይገባው ነበር።

92) የኖተርዳም አንትወርፕ ህንፃ ጣሪያ 403 ጫማ ቁመት ሲኖረው፤ በአጠቃላይ ከባህር ጠለል በላይ 468 ጫማ ይረዝማል፤ ህንጻው ላይ ቱሌኮፕ እገዛ መርከቦች ከእሩቅ እንደሚታዩና ካፒቴኖች ከሚገርም የ150 ማየል እርቀት ላይ ካቴድራሉን ማየት እንደሚችሉ ይገልጻሉ። ምድር ሉል ብትሆን በዚህ እርቀት የህንፃው ጣሪያ ለአንድ ማየል(5,280 ጫማ) ከአድማስ በታች ይሆን ነበር።

93) የሴንት ጆርጅ ወንዝ በሆሊሄድ እና በኪንግስተን ሀርበር መካከል ሁኖ በደብሊን አቅራቢያ የሚገኝ ሲሆን፤ የ60 ማየል ስፋት አለው። ወንዙን የሚሻገሩ መንገደኞች ከጀርባ ያለፉትን 44 ጫማ ቁመት ያለውን የሆሊሄድ ፒር ላይት ሃውስ ብርሃን እና እንዲሁም ከፊትለፊት ባለ 68 ጫማ ከፍታውን የፑልበግ ላይት ሃውስ ብርሃን በደብሊን፤ የሁለቱንም ብርሃን በጀልባው 24 ጫማ ከፍታ ላይ ሁነው ያስተውላሉ። ጀልባው በ30 ማየል መሃከል ላይ ሲሆን፤ በ25,000 ማየል ዙሪያ ኳስ ምድር ላይ ሁለቱም ብርሃኖች ከ300 ጫማ በላይ ከአድማስ በታች መሆን ነበረባቸው።



94) በኢንግላንድ በፖርትስማውዝ አቅራቢያ ከሀምሸር ኮረብታ ወደ አይስል ኦፍ ዋይት ደሴት መላ ደሴቱን ምልከታ፤ በሙሉ የደሴቱ መሰረት ውሃ ነበርና በ22 ማየል እርዝመቱ ሁሉም መሬቱም ውሃውም በአንድ ላይ ትክክለኛ ቀጥ ያለ መስመር ሰርተው ይታያሉ፡፡ እንደ ኳሷ ዓለም ንድፈ ሃሳብ የአይስል ኦፍ ዋይት ደሴት ስሚያስፈልገው መጠምዘዝ ከመሀከለኛው ቦታ በግራና ቀኝ ለ80 ጫማ ዝቅ ማለት ነበረበት፡፡ በዚህ አቅጣጫ በትክክለኛ ማዕዘን ቋሚ የሆነ ቴሌስኮፕ ቢቀመጥም፤ በተደጋጋሚ ጊዜ ውሃውና መሬቱ ቀጥ ብሎ የተዘረጋ መሆኑን ነው ያሳየው፡፡



95) በጠራ ቀን በዶግላስ ሀርቦር አቅራቢያ በ አይስል ኦፍ ማን ደሴት ኮረብታ፤ የሰሜን ዋልስ ባህር ዳርቻ ያለምንም መሳሪያ እገዛ በአይን ብቻ በደንብ ይታያል፡፡ ከዲ ወንዝ ጫፍ እስከ ሆሊሄድ ባጠቃላይ ለ50 ማየል የተለጠጠው ባህር ዳርቻ ሙሉበሙሉ አግድም ቀጥ ያለ እንደነበር ነው በተደጋጋሚ ጊዜ ማወቅ የተቻለው፡፡ በእውነት ልክ ናሳና የዘመኑ ጠፈርተኞች እንደሚሉት ምድር በአንድ ማየል እርቢ ሁለት ውስጥ 8 ኢንች የምትጠመዘዝ ከነበረ፤ በሊቨርፑል ባህረሰላጤ አግድም ለ50 ማየል ተዘርግቶ የሚታየው የዌልሽ ዳርቻ ከመሀከለኛው ቦታ በሁለቱም ጫፍ በቀላሉ የሚስተዋል የ416 ጫማ ዝቅታ እንዲኖረው ግድ ይሆን ነበር፡፡

96) ከ‹‹100 Proofs the Earth is Not a Globe›› በዊሊያም ካርፔንተር ‹‹በምሽት ወደታች ወደ ቸሳፒክ ባህረሰላጤ(Chesapeake Bay) ብንጓዝ፤ መርከቡ ከመድረሱ ከስንድ ሰዓት በፊት ከሻርፐስ ደሴት የሚስቀቀውን ብርሃን እናያለን፤ የመርከቡን ስቀጣጫ ቀደሊን ጉዞውን ወደብርሃኑ/ቢብርሃኑ መስመር ሳደ ትደዩ እንዲሆን በማድረግ ስንጓዝ በስጠቃላደ በመሳ ጉዞው ብርሃኑ በግልጽ ከፍታው ሰትንሽ ዲግሪም እንኳን ሳደዛነፍ እናገኛለን፤ ግን የስስፈሶስት ማየል እርቀት እኮ ቀርብ ነው ልትሱኝ ትችሳላችሁ፤ የጠፈርተኞቹ የመጠምዘዝ ንድፈ ሀሳብ(በስንድ ወደንም በኬሳ መንገድ) በግልጽ የብርሀኑ የ112 ጫማ ከፍታ የ8 ኢንች ልዩነት ደጠደቃል፡፡ ዳሊ ግን የ100 ጀጉሮችም ልዩነት የስም፡፡ የቸሳፒክ ባህረሰላጤ የተጠመዘዘ እንዳልሆነ ግልጽ የሚታደ ማረጋገጫ ስለን፤ ደህም ማስት ምድር ሱል እንዳልሆነች ማስረጃ ነው፡፡››

97) ናሳና የዘመኑ ጠፈርተኞች እንደሚሉት፡- ምድር ትልቅ ኳስ ነች በራሷ ዛቢያ አጋድላ እየተገላበጠች በሰዓት 1000 ማየል ትሽከረከራለች፤ በፀሐይ ዙሪያ በሰዓት 67,000 ማየል ክብ እየተጓዘች፤ በሚልኪ ዎይ ዙሪያ ሁሉም የስርዓተ ፀሐዩ በሰዓት 500,000 ማየል እየተጥመዘመዙ፤ መላ የከዋክብት ክምችቱ ደግሞ በሰዓት በሚያስደንቅ 670,000,000 ማየል ወደ ህዋ እየተተኮሰ ነው፤ የዚህ ሁሉ እንቅስቃሴ መሰረቱ ከ14 ቢሊየን ዓመት በፊት ‹‹ቢግባንግ›› የተባለው ኮዝሞጅኒያዊ ፍንዳታ ሲሆን አጠቃላይ ድምር በሰዓት 670,568,000 ማየል ከቡዙ የተለያየ አቅጣጫ ባለ እንቅስቃሴ፤ እንደሚባለው ከሆነ ሁላችንም በተመሳሳይ ሁኔታ አብረን እየሮጥን ነው፡፡ ግን በታሪክ ማንም ሰው አንድም የዚህ አይነቱን እንቅስቃሴ አይቶ፣ ሰምቶ፣ ለክቶ ወይም አረጋግጦ አያውቅም፡፡

98) ናሳና የዘመኑ ጠፈርተኞች እንደሚሉት፡- ፖላረስ ወይም የሰሜን ከዋክብት ከ323-434 የብርሃን ዓመት ወይም እስከ 2 ኳድሪሊየን ማየል ከእኛ ይርቃል፡፡ በመጀመሪያ ይሄ ልዩነት ማለት ከ1,938,000,000,000,000 - 2,604,000,000,000,000 ማየል ሲሆን፤ በመካከላቸው የሚኖረው ልዩነት 666,000,000,000,000 (ከስድስት መቶ ትሪሊየን በላይ) ማለት ነው፡፡ የዘመኑ ጠፈርተኞች በመቶ ትሪሊየን ማየሎችም የኮከቦችን እርቀት የማይስማሙ ከሆነ ምናልባትም የእነርሱ ‹‹ሳይንስ›› ጉድለት አለው እና ቲዎሪያቸው እንደገና መመርመር ያስፈልገዋል፡፡ እንደዚህ እርግጠኛ ያልሆነውን የከዋክብት እርቀት ብናምንላቸው እንኳ፤ ለእነርሱ የተንቀሳቃሿ ዓለም አማኞች፤ አዘንብላ እየተሸከረከረች በምትገላበጥ ምድር ላይ እንዴት ፖላረስ እራሱን ሁልጊዜ በሰሜን ዋልታ በኩል ብቻ እንደለጠፈ ለማብራራት የማይቻል ነው፡፡

99) ከኳሷ ዓለም እይታ ፖላረስ ቀጥታ በሰሜን ዋልታ በኩል ይገኛል፤ በየትኛውም የደቡብ ንፍቀ ክበብ ሊታይ አይገባም፤ ፖላርስ በሉላዊ ምድር የደቡብ ንፍቀ ክበብ እንዲታይ ተመልካች እንደምንም ‹‹በምድር ውስጥ›› እያየና ለማየሎች መሬትና ባህሩ በውስጣቸው የሚያሳዩ ብርሃን አሳላፊ አካላት ሁነውለት መሆን አለበት፡፡ ዳሩ ግን ፖላርስ ከ20 ዲግሪ በላይ እስከሚሆን የደቡብ ኬክሮስ ድረስ መታየት ይችላል፡፡

100) ምድር ኳስ ከነበረች የሳውዘርን ክሮስ እና ሌሎችም የደቡብ ህብረ ከዋክብት እንደ ሰሜኑ ሁሉ፤ ከፖላርስ ጋር አርሳ ማጆር/ማይነርና ሌሎችም በዙሪያው ያሉ ህብረ ኮከቦች በሁሉም የሰሜን ሜሪድያን በአንድ ጊዜ በአንድ አይነት ኬክሮስ ላይ ለሁሉም ኬንትሮስ እንደሚታዩ ሁሉ፤ የደቡቡም ህብረ ኮከቦች ልክ እንደ ሳውዘርን ክሮስ ያሉት ለደቡብ ሜሪድያን ሀገሮች መታየት ነበረባቸው፡፡ በአንጻሩ ግን ይሄ የሚያረጋግጠው እንደ ኳሷ ምድር ሞዴል የደቡቡ ንፍቀ ክበብ ‹‹ወደታች የታጠፈ›› እንዳልሆነ ነገር ግን እንደ ዝርጋ ዓለም ሞዴል ከመሃከለኛው ቦታ ከሰሜኑ እርቆ ወደ ውጭ ተለጥጦ የተዘረጋ መሆኑን ነው፡፡



101) ሲግማ ኦክቴንቲስ እንደ ፖላርስ ሁሉ በደቡብ መሃከለኛ ዋልታ እንደሆነ ይነገራል፤ ሁሉም የደቡብ ንፍቀ ክበብ ከዋክብቶች ከፖላረስ በተቃራኒ አቅጣጫ ይሽከረከራሉ። ሲግማ ኦክቴንቲስ ግን በአንድ ጊዜ በሁሉም ተመሳሳይ ኬክሮስ ላይ ያሉ ቦታዎች አይታይም። መሃከል ላይ አይደለም ከመሃል ቦታ 1 ዲግሪ ይወጣል ይላሉ፤ ቋሚ አይደለም ይንቀሳቀሳል ይላሉ፤ በእውነቱ በህዝብ ዘንድ ያሉ ቴሌስኮፖችን ተጠቅመንም መታየት አይችልም፤ ሲግማ ኦክቴንቲስን በተመለከተ ስለመኖሩ እንኳን የአግባብነት ግምቶች ናቸው ያሉት። ሌላው በላያችን ኮከቦች የሚንቀሳቀሱበት አቅጣጫ መሰረት፤ ከሩቅ እይታችንና ፊትለፊታችን ካለው አቅጣጫ አኳያ እንጅ ከንፍቀ ክበቡ አንጻር አይደለም።



102) አንዳንድ የተንቀሳቃሺ ዓለም አማኞች፤ የዋልታ ኮከቦች ተመልካች ወደ ደቡብ በተንዘ ቁጥር ከላይ ቀስበቀስ ወደታች እየዘቀጡ መታየት የሉሳ ምድር ማረጋገጫ ነው ይላሉ። የዋልታው ኮከብ ወይም ሌላ አካል ወደታች እየዘቀጠ መታየት በቀላሉ ጠለል/ዝርግ ገጽ ላይ የሚፈጠር የሩቅ እይታ ህግ ውጤት ነው። አንድ አካል ከሚታይበት ማዕዘን እና ቁመት አፈግፍገን እየራቅን ስንሄድ እያነሰና እየዘቀጠ ምስሉ እስከሚጠፋ ድረስ መሬቱ ከፍ እያለ የሄደ መምሰል(ምሳሌ የአድማስ መስመር) በሩቅ እይታ ህግ ስርዓት ምክንያት ነው። በኳሷ ሞዴል አድማሱ የምድር ጥምዝ ነው ይባላል፤ በእውነታው ግን አድማሱ የአይናችን፣ የመሳሪያዎች፣ የአየር ሁኔታ እና የከፍታ እይታ አቅሞች ውጭ ሲሆን የሚፈጠር በሩቅ የእይታ መጨረሻ ነው።



103) ከምድር ትልቅ እርቀት ላይ መታየት የሚችሉ ብዙ ህብረ ከዋክብት አሉ፤ አዘንብላ እየተሽከረከረች በምትሮጥ ኳስ ዓለም ሊታይ ከሚገባው ያለፈ ማለት ነው። ለምሳሌ አርሳማጆር ለፖላረስ በጣም ቅርቡ ሲሆን ከ90 ዲግሪ ሰሜን ኬክሮስ(የሰሜን ዋልታ) አስከ ታች 30 ዲግሪ ደቡብ ኬክሮስ መታየት ይችላል። በኳሷ ዓለም ይህ እንዲቻል የደቡብ ተመልካች ለመቶዎች ወይም ለሺህ ማየሎች በምድር ውስጥ የሰሜንን ሰማይ እያየ መሆን አለበት።

104) የቬልፔኩላ ህብረ ኮከብ ከ90 ዲግሪ ሰሜን ኬክሮስ ሙሉ እስከ 55 ዲግሪ ደቡብ ኬክሮስ መታየት ይችላል፤ ቶረስ፣ ፓይሲስ እና ሊኦ ከ90 ዲግሪ ሰሜን ሙሉ አስከ 65 ዲግሪ ደቡብ ይታያሉ፤ በኳሷ ዓለም ላለ ተመልካች በምንም አይነት ማጋደል ወይንም ማዘንበል፤ በየትኛውም ሎጅክ የዚህን ያህል እሩቅ ማየት አይቻለውም።

105) አኳሪየስና ሊብራ ከ65 ዲግሪ ሰሜን እስከ 90 ዲግሪ ደቡብ ይታያሉ፤ የቪርጎ ህብረ ኮከብ ከ80 ዲግሪ ሰሜን እስከ ታች 80 ዲግሪ ደቡብ ይታያል፤ ኦሪዮን ከ85 ዲግሪ ሰሜን ሙሉ እስከ 75 ዲግሪ ደቡብ ኬክሮስ መታየት ይችላል፤ ለዚህ ሁሉ ክስተት ምክንያቱ ‹‹ንፍቀ ክበቡ›› በጭራሽ ሉል ቅርጽ አለመሆኑ ብቻ ነው። መሃከል ላይ የሰሜን ዋልታን ከኮከቦቹ ጋር አድርጎ ክቡን አማክሎ ወደ ውጭ ተለጥጦ የተዘረጋ ኬክሮስ በመሆኑ ነው።

106) ‹‹ደቡብ ዋልታ›› እየተባለ የሚጠራው ከመነሻው እስከ መጨረሻው የአንታርክቲክ በረዶ ክፍል ሲሆን፤ በዝርግ/የእንጆራ ምጣድ በመሰለችው ዓለም ጠርዝ ዙሪያ ያለ ቦታ ነው። ደቡብ ዋልታ ብለው የጠቀሱልን ስፍራ ምናልባትም ትክክለኛው ደቡብ ዋልታ አይደለም፤ ምክንያቱም በምድር ጠርዝ ዙሪያ ተንሰራፍቶ ያለውን የበረዶ ስፍራ እንደ አንድ ውስን ቦታ በሉል ቂጥ በኩል ለጥፈው ይዜ ነው ስላሉንና ትክክለኛውን ደቡብ ዋልታ በኮምፓስ እገዛ ማረጋገጥ ስለሚቻል። ከተመልካቹ 360 ዙሪያ መሀል ያለው የሰሜን ዋልታ እንደሆነ ይጠቁሙናል፤ ነገር ግን የዚህ አይነቱ ጀብድ ባለመፈጸሙ ሞዴሉ ንጹህ ቲወሪ እንደሆነ ቀርቷል፤ ተቋሞቹ ለሚቀርበው ቅሬታ በሚሰጡት ሽፋን እንዲህ ይሉናል፡- ጅኡ መግነጢሳዊው ዋልታ ያለማቋረጥ መንቀሳቀሱ ላልመሰለን ነገር ምክንያቱ ነው።



107) ለምድር ምሳሌ የዚሁ አይነት ቀለበታማ ማግኔት በላውድ እስፒከሮች ውስጥ እንዳለ ይታወቃል፤ በመሃል ላይ የሰሜን ዋልታ ሲሆን ከመሃከል ቦታው ውጭ ያለው ዙሪያ በሙሉ ተቃራኒው የደቡብ ዋልታ ነው። ይሄ በትክክል የዝርጋ ዓለማችንን ማግኔቲዝም ያስረዳል። በአንጻሩ በኳሷ ዓለም ሞዴል የማግኔቲዝም ምንጭ የተባለው መላምታዊ ከሆነው የቀለጠ መግነጢሳዊ ኮር ከኳሷ መሀል ቦታ ከሚገኘው መጣ የሚለው

ነው። ለእነርሱ ceremonial poles የተለያየ የተድበሰበሰ ማስረጃ፤ እነርሱ እንደሚሉት ሁለቱንም ዋልታዎች ያለማቋረጥ በሚያመች ሁኔታ ያንቀሳቅሳል። በእውነታው በታሪክ ትልቁ ቁፋሮ የሩሲያው ኮላ አልትራ ዲፕ ማሳካት የቻለው ወደታች 8 ማየል ብቻ ነው። በት/ቤት እያሳዩ ያስተማሩን ቅርፊት፣ ውጨኛ ማንትል፣ ውስጠኛ ማንትል፣ ውጨኛ ኮር እና ውስጠኛ ኮር ደለሎች የቅርፊትን ክፍል እንኳን ዘልቀን መግባት እስካልቻልን ድረስ ሁሉም ግምቶች ብቻ መሆናቸው ግልጽ ነው።



108) የማሪነርን ኮምፓስ በኳሷ ዓለም ለመጠቀም የማይሆን እና ምንም ትርጉም የማይሰጥ መሳሪያ ሁኖ እናገኘዋለን፤ በአንድ ጊዜ ሰሜንና ደቡብን በዝርግ ገጽ ላይ ነው የሚጠቁመው። የኮምፓሷ ጫፍ በምትሽከረከረው ሉል ተግባር በተቃራኒ አቅጣጫ ያለማቋረጥ የሚንቀሳቀሰውን ጅኦ መግነጢሳዊ ዋልታ እየጠቆመ ነው ይላሉ፤ ከመላምታዊ ከምድር ኮር የቀለጠው ብረት ከሚሉት የተመሰረተውን ማለት ነው። በእውነት የኮምፓሷ መርፌ ወደ ሰሜኑ ዋልታ የሉል ክፍል ጠቁማ ቢሆን ኑሮ፤ ተቃራኒው ‹‹ደቡብ›› መርፌ ደግሞ ወደ ላይ ወደ ውጭ ህዋ እየጠቆመ ይሆናል ማለት ነው።

109) በዝርግ ምድራችን ብቸኛ ውስን ቦታ ሁኖ የተረጋገጠው የሰሜን መካከለኛ ዋልታ ብቻ ነው። ልክ ውስን የሆነ ደቡብ እንደሌለ ሁሉ፤ ‹‹ምስራቅ›› ወይም ‹‹ምዕራብ›› የተባለ ውስን ቦታ የለም። ደቡቡ ሁሉም ከዋልታው የወጣው ቀጥተኛ መስመር ሁኖ፤ ምስራቅና ምዕራብ የክቡ ማዕከላዊ ዙሪያው ሲሆኑ ከዋልታው በመደበኛ 90 ዲግሪ ማዕዘን ናቸው። በምድር ምዕራባዊ ዙሪት በፖላሪስ ዙሪያ ቀኝን ይዞ መጓዝ ነው። ምስራቃዊ ዙሪት ደግሞ በፖላሪስ ዙሪያ ሁልጊዜ ግራን ይዞ መጓዝ ማለት ነው።

110) ማጅላንና ሌሎችም ምስራቅ/ምዕራብ የምድር አሳሾች ጉዞ ብዙጊዜ የኳሷ ሞዴል ማረጋገጫ እንደሆነ ይጠቀሳል። በእውነታው ግን ከሰሜን ዋልታ በቀጥተኛ ማዕዘን መጓዝ ወይም መብረር እና ተመልሶ ከመነሻ ቦታ መድረስ፤ በሉል ላይ ከማድረግ ውጭ ከባድ እና ሚስጥራዊ አይደለም። ልክ አንድ አርክቴክት የኮምፓሱን መሀል በዝርግ ወረቀት ላይ ተክሎ በዋልታው ዙሪያ ክቡን እንደሚያዞር፤ ልክ እንደዚሁ መርከብ ወይም አየር ዝርጋን ምድር መዞር ይችላሉ።



111) ሰሜን ዋልታ እና አንታርክቲካ በበረዶ የተሸፈኑ ሁነው ‹‹በረራ የሌለበት›› ዞኖች ተብለው በመጠበቃቸው፤ ምንም መርከብ ወይንም አየር ምድርን ሰሜን/ደቡብ አቅጣጫ በመዞር አይታወቅም። ብቸኛው በዝርጋ ዓለም ሊደረግ የማይችለው ዙሪትም ሰሜን/ደቡብ ጽንፍ ነው። በከፍተኛ ሁኔታ ተፈጻሚ እንዲሆን ለተደረገው የበረራ እገዳ ዋናው ምክንያትም ማለት ነው፤ ምድርን ሰሜን/ደቡብ የሚያረጋግጥ አንድም ዙሪት አለመኖሩ ምድር ኳስ ላለመሆኗ ቋሚ ማስረጃ ነው።



112) ፀሐይ በላይ ሁና በክባዊ መስመሩ በምድር ዙሪያ እያለፈች ስትዞር፤ በ24 ሰዓቶች ውስጥ ለእያንዳንዱ 15 ዲግሪ የሚካለል ስፍራ ቀትርን ትለግሳለች፤ በዚህም የጊዜ ክልሎች/time-zones ተፈጥረዋል። ከዚህ ይልቅ ግን የጊዜ ክልሎች የተፈጠሩት ኳስ ምድር በፀሐይ ዙሪያ በምታደርገዉ የአንድ ወጥ ፍጥነት እሽክርክሪት ምክንያት ቢሆን ኑሮ፤ በየ 6 ወሩ ምድር እራሷን በሌላዉ የፀሐይ ጎን ስታገኝ፤ በዓለም ዙሪያ ያሉ ሰዓቶች በሙሉ 12 ሰዓት ይገለበጡ ነበር፤ ቀኑ ምሽት ምሽቱ ደግሞ ቀን ይሆን ነበር።

113) በአንዳንዱ የመሬት ክፍሎች ሰዎች የሚቆሙት፣ መርከቦች የሚጓዙት እና አየሮች የሚበሩት ተዘቅዝቀው ነው የሚለውና፤ ሌሎች ደግሞ 90 ዲግሪ እና በሌሎች የማይቻሉ አንግሎች አጋድለው ነው ያሉት የሚለው እሳቤ ሙሉ ሞኝነት ነው። ሰው ቀጥታ ወደታች ጉድጓድ እየቆፈረ በመጨረሻ ከሌላኛው ምድር ጎን ከሰማይ ብቅ ይላል ብሎ ማሰብ ማላገጥ ይሆናል። እንደ

ኒውተናዊው/አንስታይናዊዉ አስተሳሰብ ‹‹ሁሉም ነገር አንጻራዊ ነው›› ሳይሆን ለሁሉም ነጻ አስተሳሰብ ላለው ሰው የስሜት ህዋሳችን የሚናገረው በተፈጥሮ ‹‹ላይ›› እና ‹‹ታች›› መኖሩን ነው፡፡

114) በ ‹‹**On the False Wisdom of the Philosophers**›› ከላካንቲስ አባባል ‹‹የሱል ሰዎች በሌላው ጎን እግሬቸው ከእሬሳቸው በላይ ሁኖ ዝናብና በረዶ ወደ ላይ እየወደቀ፣ ዛፍና ሰብሎች ተዘቅዝቀው እያደጉ እና ሰማዩ ከመሬት ዝቅ ይላልን? አረማዊ ፈላስፋዎች ባህሩ ከተማው እና ተሬሮቹ ያለምንም ድጋፍ ከምድር ላይ ተንጠልጥለው እንዲሆን ያምናሉ፤ ከዚህ ጋር ስናነጻጽረው የጥንት ባቢሎናዊያን እቤት ላይ ተዘቅዝቆ በመንጠልጠል እድገቱን እንዲቀጥል የታሰበው አትክልት እየመነመነ የሄደው በምንም ምክንያት አልነበረም ማለት ነው፡፡››

115) ያለው የሚኖረው የእፍግታና የመንሳፈፍ ሃይል ህግ፤ ገና መጀመሪያ የነበረ እና የተሾመው የፍሪማሶን ‹‹Sir›› አይዛክ ኒውተን የ‹‹ግራቪቲን›› ቲዎሪ ለዓለም ከመስጠቱ በፊት የነበረ በትክክል ቁሶች የሚወድቁበትን ፊዚክስ ያስረዳ ህግ ነው፡፡ አንድ ቁስ ከቁሱ አንጻር አነስ ያለ እፍግታ ያለው ስፍራ ላይ ሲሆን ወደታች እንደሚዘቅጥና፤ ጥቅጥቅ ያለ እፍግታ ያለው ስፍራ ላይ ደግሞ ወደ ላይ እንደሚንሳፈፍ የታወቀ ነው፡፡ ላይና ታች ለሌላት ለተንቀሳቃሿ የዓለም ሞዴል እንዲገጥም ግን፤ ኒውተን በዚህ ፋንታ ቁሶች ከትልቅ ክብደቶች ጋር ይሳሳባሉ ወደ መሃል ቦታ ይመጣሉ ብሏል፤ ኒውተን እንደሚለው፡- ‹‹ግራቪቲ›› እኛን በምድር ላይ እንድንቀመጥ ፀሐይ ጨረቃ ከዋክብት እና ፕላኔቶችን ደግሞ በአንድ አካባቢ ተሰባስበው እንዲቆዩ አድርጓል፡፡ በታሪክ ግን አንድም ሙከራ አንድ ቁስ በቂ በሆነው ግዝፈቱ ምክንያት በክብደቱ ደግነት ብቻ ሌሎች ትንንሽ ክብደቶች ወደ እሱ ተስበው እንዲቆዩ እንዳደረገ ያሳየ የለም፡፡



116) እንዲሁ በታሪክ አንድም ሙከራ፤ አንድ አካል በጣም በቂ በሆነ ግዝፈቱ ምክንያት በክብደቱ ደግነት ብቻ ሌላ ትንሽ ክብደት ያለው አካል በራሱ ስፍራ እንዲዞረው ማድረግ እንደቻለ ያሳየ የለም፡፡ አስማታዊው የግራቪቲ ቲወሪ ውቅያኖሶች፣ ህንፃዎችና ሰዎች ለዘላለም በታችኛው የምትሽከረከር ኳስ ክፍልም ተለጥፈው እንዲቀሩ ያደርጋል፤ በአንድ ጊዜ ጨረቃና እንደ ሳተላይት ያሉትን ደግሞ በምድር ላይ ክባዊ ዙሪት ብቻ እንዲጓዙ ያዛል፤ ሁለቱም ሀሳቦች እውነት ከነበሩ ሰዎች ወደላይ ዘለው በምድር ዙሪያ ክብ መዞር መጀመር ይችሉ ነበር፤ ወይም ጨረቃ ከብዙ ጊዜ በፊት ምድር ላይ ተለጥፋ መሆን ነበረበት፤ አንድም የዚህ አይነቱ ቲወሪ ግን በሙከራዎች አልተረጋገጠም፡፡ እና ለሚታየው ውጤት ምክንያት አድርገው የሰጡት ክስተት እርስበርስ የሚቃረን ነው፡፡

117) ኒውተንም ሀሳቡን ሰጥቶበታልና አሁን በጋራ የሚታሰበው በሉል የውቂያኖሱ ተወጥሮ መቆም በግራቪቲያዊው የጨረቃ ስበት አማካኝነት ነው በማለት ነው፡፡ የጨረቃ አጋማሽ/**diameter** 2,160 ማየል ብቻ ከሆነ፤ የምድር ደግሞ 8,000 ማየል ከሆነ፤ የራሳቸውን ሂሳብና ‹‹ህግ›› በመውሰድ ከጨረቃ ምድር በ87 ጊዜ ብልጫ ከባድ ነች ከተባለ፤ ስለዚህ ትንሹ ሳይሆን ትልቁ አካል ነው መሳብ ያለበት፡፡ የምድር ትልቁ ግራቪቲ ከሆነ ጨረቃን በምድር ዙሪያ ያስቀራት፤ እንደውም በባህር ላይ የጨረቃን ስበት ይጎትታል በሚባለው ስፍራ፤ የጨረቃ ያነሰው ግራቪቲ የምድርን ግራቪቲ እንዲተካ የማይቻል ነው፡፡ በእውነት የጨረቃ ግራቪቲ የምድርን ስበት ተክቶ በሉል ውሃው ወደላይ ተለጥጦ እንዲቀር ካደረገም፤ ወደየራሳቸው የመሳሳባቸውን ኃይል ከመቀጠል ሊያግዳቸው የሚችል ነገር አይኖርም ነበር፡፡



118) በተጨማሪም የጨረቃ ፍጥነቷ እና መስመሯ ወጥ ነው፤ ስለዚህ ወጥ የሆነ ተጽኖ በምድር የተወጠረ ውሃም ልትፈጥር ይገባል፡፡ በእውነታው ምድር ላይ የተዘረጋው ውሃ በትልቁ ይለያልና የጨረቃን ጉዞ አይከተልም፤ የምድር ሃይቆች ኩሬዎች የረግረጋማ ቦታዎችና የሌሎችም የመሬት አካል ውሃዎች ያለምንም ችግር ምንጊዜም ከጨረቃ ግራቪቲያዊ እርዳታ ውጭ

ይፈሳሉ፡፡ እስኪ ‹‹ግራቪቲ›› ውቅያኖሱን ወደ ጨረቃ አቅጣጫ አቁሞ አስቀርቶ ከነበረ፤ ሁሉም ሀይቆች ኩሬዎችና ሌሎችም የተኙ የውሃ አካላት በእርግጠኝነት ወደ ጨረቃ ተወጥረው መሆን ነበረበት፡፡

119) ሌሎች ፕላኔቶች ሉል ስለሆኑ ምድርም ሉል መሆን አለባት ተብሎ ይታሰባል፤ በመጀመሪያ ምድር ‹‹ጠለል/plane›› ነች ‹‹ፕላኔት/planet›› አይደለችም፤ ስለዚህ የእነዚህ በሰማይ ላይ ያሉት ‹‹ፕላኔቶች›› ቅርጽ ከእግራችን በታች ያለችውን ምድር ቅርጽ አያስለውጡም፤ ሲቀጥል ደግሞ እነዚህ ‹‹ፕላኔቶች›› በዓለም ዙሪያ ለብዙ ሺህ አመታት ‹‹ልዩ ከዋክብት›› በመባል ይታወቃሉ፡ ምክንያቱም በአንጻራዊ እንቅስቃሴያቸው ብቻ ከሌሎች ኮከቦች ይለዩ ስለነበር፤ባልተዛባው ንጹህ ዓይናችን ወይም ቴሌስኮፕ ስናይ እነዚህ ቋሚ የተለዩ ኮከቦች ባለ ብሩህ የዲስክ ብርሃን ሁነው ይታያሉ፤ ሉላዊ አካል አይደሉም፡፡ በናሳ የሚቀርብ የፕላኔቶችን ሉላዊ አካል የሚያሳይ ምስል ሁሉም ግልጽ ሀሰተኛ በኮምፒውተር የተፈጠረ ምስል ነው፤ ትክክለኛ ፎቶግራፍ አይደለም፡፡

120) የቃሉ ‹‹planet›› ስነ ቋንቋ የመጣው ከድሮው እንግሊዘኛ planete ከድሮው ፍራንስ planete (ከዘመኑ ፍራንስ planète) ከላቲን planeta ከግሪክ planetes ለ(ልዩ ኮከቦች) planetai ‹‹wandering (stars)›› ከጆርመኒ ‹‹to wander›› ለማይታወቅ የከዋክብት መሰረት ምናልባት ከ PIE *pele ‹‹flat, to spread›› ወይም notion of ‹‹spread out›› እና Plane (n) “flat surface,” c. 1600, from Latin planum “flat surface, plane, level, plain,” planus “flat, level, even, plain, clear.” They just added a “t” to our Earth plane and everyone bought it.

121) ፀሐይና ጨረቃን ስናይ ሁለት እኩል የሚመስሉና በተመሳሳይ አቅጣጫ የሚጓዙ ሰማዩን በመዞር ለምድር እንደሚያበሩ ነው የምናስተውለው፡፡ በቀን በቀን ልምምዳችን የስሜት ህዋሶቻችን የሚነግሩን ሁሉ ስህተት እንደሆነ ናሳ ውስጥ ያሉ ‹‹ሊቆች›› እንዲህ ይሉናል፡- ምድር ዝርግ አይደለችም ግን ትልቅ ኳስነች፤ ቋሚ አይደለችም ነገር ግን በሰከንድ 19 ማየል ትሽከረከራለች፤ እንደሚታየው ፀሐይ በምድር ላይ አትዞርም፤ ምድር በፀሐይ ዙሪያ ትጓዛለት እንጅ፤ በሌላ ሁኔታ ደግሞ ጨረቃ ምድርን ትዞራለች፤ ዳሩ ግን እንደምናየው ከምስራቅ ወደ ምዕራብ አይደለም፤ ከምዕራብ ወደ ምስራቅ እንጅ፡፡ ጨረቃና ፀሐይ ተመሳሳይ ግዝፈት ያላቸው መስሎን ሳለ ነገር ግን ፀሐይ ከጨረቃ 400 እጥፍ ትገዝፋለች፤ እኩል መስለው እንዲታዩን ግን ፀሐይ ከምድር 400 እጥፍ ትርቃለች፡፡ እኛ ግን ተመሳሳይ መጠን እንዳላቸውና በተመሳሳይ ከፍታ ላይ እንዳሉ እናያለን፡፡ ምድር ዝርግ እንደሆነችም እናያለን፤ እንደማትንቀሳቀስም ነው የሚሰማን፤ ሆኖም ግን በዘመኑ ጠፈርተኞች ዶክትሪን መሰረት እንደዚህ አይናችንን እና የህይወት ተሞክሯችንን ካመንን ጅሎች ወይም መሳለቂያዎች ነን፡፡

122) አለንዬ‹ቭ እንዳለው፡- ‹‹ስለኪ ስለተዳደረ ዉዩም ናሳ ምድር ቋሚ እንደሆነች ነግሮናል እንበልና፤ ስለቡት እና እኛ ደግሞ ‹‹ለዩ ምድር ቋሚ ስዩዩስችም በ32 እጥፍ የጥዩት ፍጥነት ወዩፌት እየተጓዘችና፤ በሰዓት 1000 ማየል ደግሞ እየተሸከረከረች ነው›› ብሰን ስማሳመን ብንሞክር፤ ዩሳቅብን ነበር፤ ብዙ ሰዎች እብድ ናችሁ ምድር ስትንቀሳቀስም ዩሱን ነበር፤ ስተመሳሰከሙ የሚንቀሳቀስ ዓለም ምንም ሳዩንሳዊ ማስረጃ ባስመያዛችን ዩሳስቁብን ነበር፡፡ ዩህ ብቻ ስዩዩስም ሰዎች ‹‹እሽ የማዩንቀሳቀሰውን ቋሚ ከባቢ እየር እና የሚታየውን የፀሐዩ እንቅስቃሴ እንዴት ትገልፁታሳችሁ›› ብስው ዩጠዩቁን ነበር፤ ስስቡት እኛም እንዲህ ብስን ስንመልስ ‹‹ስዩ ስዩ ከባቢ እየሬም ስብር በሚገርም ሁኔታ ከምድር ጋር እየዞሬ ነው›› ስስዚህ ምክንያቱ ምድር ቋሚ ስስሆነች ብቻ ሳዩሆን እኛ እያልን ያስነው ስሜት የሚሰጠውን ነገር ነው፤ የሚንቀሳቀሰው ዓስም ንድፌ ሃሳብ ምንም ስሜት ስዩስጥም የቋሚዋ ዓስም ንድፌ ሃሳብ ነው ስሜት የሚሰጠው እያልን መሳስቂያ ሁነናል፡፡ ዩዜ ሁኔታ ምን ያህል የሚያስቅ እንደሆነ ስመረዳት በሴሳው ቦታ ሁኖ ማየት ተገቢ ነው፤ ዩህን የስተዳዳረን እና የናሳን ስባባል፤ ምድር ስዘንብሳ እየተሸከረከረች ፀሐዩንም ደግሞ ትዞራስች የሚስውን ሰዎች ስጥብቀው ተጠምጥመውበታል ስፌሳቸውን እንደማትንቀሳቀስ ዉዩሚያመሳክቱት ማስረጃዎች ማቀረብ ስዩችሉም፤ እንቅስቃሴ ስዩሰማንም፤ ከባቢ እየሬ ተበትኖ ስልዒዩብንም፤ ፀሐዩ በምስፌቅ ወጥታ በምሰፌብ ትገባስች፤ ሁሱን ነገር በማትንቀሳቀስው ዓስም መረዳት ዩቻሳል፤ ነባሪን እውነት ስመቀየር ሴሳ መሳምችችን ሳንዩረዩር፡፡››

123) የተንቀሳቃሿ ዓለም ጠፈርተኞች ስሌት ሁልጊዜ ትክክለኛና እቅጯን ነው ይባላል፤ ነገር ግን ከተለያዩ ሞዴሎቻቸው ጋር እንዲጣጣሙ በታሪክ ውስጥ በተደጋጋሚ ጊዜ በጣም በትልቁ ብልሹ የሆነ ስሌት ነው የነበራቸው፡፡ ለምሳሌ ኮፐርኒከስ በዘመኑ የፀሐይ ከምድር እርቀት 3,391,200 ማየል እንደሆነ አሰላ፤ በቀጣዩ ክፍለ ዘመን ጆንስ ኪፕለር 12,376,800 ማየል እንዲሆን ወሰነ፤ አይዛክ ኒውተን አንድ ጊዜ ‹‹28 ዉዩም 54 ሚሊዮን ማየል እርቀት ብንገምተው ስያስችገርም ከዙስቱ ባንዱ ደስፌል›› ብሏል፡፡ ምን ያህል ሳይንሳዊ ነው? ቤንጅመን ማርቲን በ81 እና 82 ሚሊያን ማየል መካከል እንዲሆን አሰላ፤ ቶማስ ዲልወርዝ 93,726,900 ማየል ነው አለ፤ ጆን ሂንድ በእርግጠኝነት 95,298,260 ማየል ነው ብሎ አስቀመጠ፤ ቤንጃሚን ጉልድ ከ96 ሚሊየን ማየል በላይ ነው አለ እና ክርስቲያን ማየር ከ104 ሚሊየን በላይ እንዲሆን አሰበ፤ በተቃራኒው የዝርዝ ዓለም ዓማኞች ለዘመናት ይህንን ለማስላት ሴክስታንትና ጠለል ትሪጎኖሜትሪን በመጠቀም ፀሐይና ጨረቃ ሁለቱም የ32 ማየል አጋማሽ/diameter ብቻ እንደሆነ ያላቸው እና ከምድር በጥቂት ሺህ ማየል እንደሚርቁ አውቀዋል፡፡



124) ከዳመና በላይ በተለቀቁ አማተር ባሉኖች ቀረጻ፤ ለእይታ የሚያምር ማረጋገጫ ተገኝቷል። ይህም ፀሐይ በሚሊየን ማየል ከእኛ እንደማትርቅ ነው፤ በብዙ ቀረጻዎች ላይ የፀሐይን ግልፅ የሆነ ነጸብራቅ በደመናው ላይ ከፀሐይ በታች ማየት ይቻላል። ፀሐይ በሚሊየን ማየሎች ከእኛ የምትርቅ ቢሆን ኑሮ፤ እንደዚህ ትንሽ የሆነ በአንድ ቦታ ላይ የተወሰነ ነጸብራቅ ሊፈጠር አይችልም ነበር።

125) ሌላው ፀሐይ በሚሊየን ማየሎች እንደማትርቅ የሚያስረዳው በደመናው ውስጥ ሰንጥቀው የሚወጡትን የፀሐይ ጨረሮች ዘዌ ስንከተል ነው። ይህንን ሁኔታ የሚያሳዩ ብዙ ገጠመኞች እና እንዲሁም ፎቶዎች አሉ። በእርግጥም አጋድለው ለሚወጡት ጨረሮች መነሻ ፀሐይነች፤ በዚህም ፀሐይ በሚሊየን ማየሎች እንደማትርቅ ግልፅ ነው። ይልቁንም ለምድር ቅርብ በሚያስብል ሁኔታ ከዳመናዎች በላይ እንደሆነች ነው የምንረዳው።



126) ቀናት ሌሊቶችና ወቅቶች ላላቸው ጸባይና የጊዜ ቆይታ ልዩነት ምክንያቱ፤ የፀሐይ ከትሮፒክ እስከ ትሮፒክ ከጥግ እስከ ጥግ የምታደርገው አመታዊ ጉዞ ነው። ለዚህ ነው በመሃል ላይ ያለዉ የኢኳተሪያል ክልል በአመት ውስጥ ብዙ በጋና መቀት የሚያጋጥመው። በአንፃሩ ግን ወደ ላይኛው ኬክሮስ ሰሜንና በተለይ ደቡብ በጣም ልዩ የሆኑ ወቅቶች ከከባድ ክረምት ጋር ይገጥማቸዋል። በተንቀሳቃሿ ዓለም ሞዴል ለወቅቶች መቀያየር መንስኤ የሚባለው በኪሷ ምድር ‹‹አክሲሳዊ ማዘንበል›› እና በፀሐይ ዙሪያ ባለው ‹‹ሞላላ ምህዋር›› ምክንያት በሚደረገዉ እንቅስቃሴ ነው የሚለው ነው። አሁን ያለው የእነርሱ እንከን የሞላበት ሞዴል፤ በሰሜን ጥር ወደ ፀሐይ አቅርቦ በ(91,400,000 ማየል) እርቀት ላይ ያስቀምጠናል፤ በእውነቱ ወቅቱ ክረምት ሁኖ ሳለ። እንዲሁ በሰሜን ሃምሌ ከፀሐይ አርቆ በ(94,500,000 ማየል) እርቀት ላይ ያስቀምጠናል፤ በእውነቱ የበጋ ወቅት ሁኖ ሳለ።



127) ባህር ላይ የፀሐይና የጨረቃ ነጸብራቅ ከአድማስ ጥግ እስከ ተመልካቾቹ ድረስ ቀጥተኛ መስመር ሁኖ መታየት ምድር ኳስ እንዳልሆነች ማረጋገጫ ነው። የምድር ገፅ የተጠመዘዘ/curve ያደረገ ቢሆን ኑሮ፤ ከአድማስ ጥግ እስከ ተመልካቹ ድረስ በውሃው ላይ ተንጸባርቆ የሚታየው ብርሃን፤ በኳሱ ላይ ተጠምዝዞ አልፎ እንዲታይ የማይቻል ይሆን ነበር።

128) ከተሰሩበት ጊዜ ጀምረው እስካሁኗ ደቂቃ ድረስ በትክክል ሰዓት መቁጠር የሚችሉ የትልቅ ክፍለ ዘመን እድሜ ያላቸው የፀሐይ/sundials እና የጨረቃ/moondials ድንጋዮች በሁሉም የዓለም ዙሪያ ይገኛሉ፡፡ በዘመኑ ጠፈርተኞች እንደሚባለው፤ በእውነት ምድር ፀሐይና ጨረቃ እንደዚህ እየተጥመዘመዘ ለሚሮጥ፣ ለሚሽከረከርና በአንዱ ዙሪያ እየተገላበጠ ለሚጓዝ የሚፃረሩ እንቅስቃሴዎች ተጠያቂ ቢሆኑ ኑሮ፤ እነዚህ ሀውልቶች ያለምንም ማስተካከያ ለዘመናት በትክክል ሰዓትን እንዲናገሩ የማይቻል ይሆን ነበር፡፡



129) ከዊሊያም ካርፔንተር አባባል ‹‹ሰምን በስሜት ህዋስ ስም ተመልካቾች ሰቅንጣት ያህልም እንዳይንቀሳቀሱ በቋሚ ድንጋይ ሳይ ቴሌስኮፑን ይተክሳሉ፤ ያቆሙባት ምድር በእርግጥ በሰከንድ የአስራዘጠኝ ማየል ድርሻ ይዛ የምትንቀሳቀስ ከሆነ፤ የምድር ስድስት ሺህ ሚሊየን ሚሊየን ሚሊየን ቶኖች ክብደት በህዋ ውስጥ ሰዘሳሰም ወደፊት እየተንከባሰሰ ወደ ፀሐይ እየበረረ ወደ ጋሳክሲው ደግሞ እየተተኮሰ ፍጥነቱን ስናወዳድረው፤ የጥይት ተኩስማ ከዚህ አንፃር ‹‹በጣም ዘገምተኛ›› ነው፡፡ በድንጋይ አምድ ሳይ ቋሚ የተደረጉት የጠፈር መመልከቻ ቴሌስኮፖች ለተመቻቸ ትክክለኛ ምልከታ የነብር አይን እይታ ያለው ጠፈርጠኛ ቢኖር እንኳ ወደፊት ያለውን የሺህ ቅንጣቶች አካል ልዩነት ማስተዋል መቻል ትዓምርን እንደመረዳት ይሆናል፤ ከተመዘገቡት ትዓምሮች ጋር ስናወዳድር ከዚህ አንጻር ሁሉም ተራ ናቸው፡፡ እኛ ግን (በመሀል ሰሜን ኬክሮስ) የሰሜን ኮከብን ማየት እንችሳለን፤ ፊትለፊት ባለው መስኮት ውስጥ ሁነን፤ በአንድ መስኮት ውስጥ በአንድአይነት የመስታውቱ ጥግ አመቱን ሙሉ ማየት መቻሳችን፤ ለማንም ሰው በስሜቱ ከነጭራሹ ምንም እንዳልተንቀሳቀሰን በቂ ማስረጃ ነው፡፡ እንዲሁም ምድር ሉል እንዳልሆነች፡፡››

130) ከ ‹‹Earth Not a Globe!›› በሳሙኤል ሮባተም ‹‹ከስድስት ጫማ ያሳነሰ እርዝመት ያሳቸው ሁለት የብረት ትቦዎችን አንድ ያርድ አለያይተን በእንጨት ክፈፍ ወይም በወጥ አግድም እንጨት ሳይ በተቃራኒ ጎን አስቀምጠን የሁለቱም ቀጥተኛ እይታ በትክክል እርስበርሳቸው ትይዩ እንዲሆን እናስተካክል፡፡ ከዛም አቅጣጫቸውን የሚታወቅ ኮከብ ወደሚታይበት ሰማይ እናድርግ፤ ከእንቅስቃሴው ትንሽ ሰከንዶች በፊት ተመልካቾች በሁለቱም ቱቦዎች እያዩ ይቀመጡና ኮከቡ በመጀመሪያው ትቦ እይታ ሲገባ በዚህ ጊዜ በሁለተኛው ትቦ ተመልካች እንዲደገም ትልቅ ደወል ወይም ሌሳ ምልክት ይሰጥ፤ እንዲሁ በሁለተኛው ትቦም ተመሳሳይ ኮከብ በመጀመሪያ እይታ ሲሆን ማለት ነው፤ በሚሰጡት ምልክቶች መካከል የጊዜ ልዩነት ይፈጠራል፤ ምልክቶቹ በፍጥነት ተከታትለው የሚመጡ ናቸው፤ ግን አሁንም በመካከሳቸው የሚፈጠረው ጊዜ ሁለት ትይዩ የሆኑ የእይታ መስመሮች በአንድ ያርድ ልዩነት ብቻ ቁመውም በሁለቱም አንድአይነት ኮከብ በተመሳሳይ ጊዜ እንደማይታይ ለማሳዎቅ በቂ ምክንያት ነው፡፡ በአንድ አይነት ቅፅበት ኮከቡ እንዲታይ ሁለተኛው ትቦ ትንሽ ዘንበል ብሎ እንዲሆን ያስፈልጋል፡፡ ትቦዎቹ ለስድስት ወራት በቦታቸው ተቀምጠው እንዲቆዩ ይደረግና በመጨረሻም በዚህ ጊዜ ተመሳሳይ ሙከራዎች ወይም እይታዎች አንድ አይነት የሆነ ውጤት ያመጣሉ፡፡ ለትቦው አቅጣጫ ምንም አይነት ትንሽ ማስተካከያ ሳያስፈልግ ኮከቡ በተመሳሳይ የሜሪዲያን ሰአት ይታያል፡፡ ከተሰጠው ማጠቃለያ ምድር ህዋ ውስጥ በዛቢያ አንድ ያርድ እንኳን ተንቀሳቅሳ ቢሆን ኑሮ፤ በትንሹ እንኳን በአንድ ያርድ ልዩነት እንዲቀመጥ ያስፈለገውን ትቦ ዝንባሌ ማስተዋል ይቻል ነበር፡፡ ነገር ግን በትቦዎቹ አቅጣጫ የዚህ አይነት ልዩነት አልተፈጠረም <u>ማጠቃለያውም ሊዎገድ የማይችል ነው፡፡ በተሰጠው ስድስት ወር የምድር ገጽ ሜሪዲያን አንድም ያርድ አልተንቀሳቀሰም፡፡ ስለዚህ ምድር የጥቂት ዲግሪም ዛቢያዊ እንቅስቃሴ የሳትም፡፡››</u>

131) ናሳና የዘመኑ ጠፈርተኞች እንደሚሉት፡- ጨረቃ ፕላኔታዊ ቅርጽ ነው ያላት የሰው ልጅ በሮ ሂዶ እግሩን ማሳረፍ የቻለባት፤ እንዲሁም ጨረቃ የራሷ ብርሃን የሌላት ፈለክ እንደሆነች እና ከፀሐይ የተቀበለችውን ብርሃን እንደምታንጸባርቅ ይናገራሉ፡፡ በእውነቱ ግን ጨረቃ ጠጣር አካል አይደለችም፤ ግልጽ ክባዊነች ግን ሉላዊ አይደለችም፤ በምንም መልኩ ሰው እግሩን ማሳረፍ የሚችልባት ፕላኔታዊ አካልም አይደለችም፡፡ በግሀዱ ጨረቃ ባብዝሃኛዉ በውስጧ የምታሳይ ብርሃን አሳላፊና ሙሉበመሉ እራሷን የምታበራ፤ የራሷን ልዩ ብርሃን የምትሰጥ ፍጥረት ነች፡፡

132) የፀሐይ ብርሃን ወርቃማ፣ ሞቃት፣ ደረቅና የቁስል መድሃኒት ነው፡፡ የጨረቃ ብርሃን ደግሞ ብርማ ቀለም፣ ቀዝቃዛ፣ እርጥብ፣ የሚያበሰብስ እና ቁስልን የማያደርቅ ነው፡፡ የፀሐይ ጨረር የውጭ ላይ እሳት መቀጣጠልን ይቀንሳል፤ የጨረቃ ጨረር ግን መቀጣጠልን ይጨምራል፤ ለፀሐይ ብርሃን የተጋለጡ የእጽዋት እና የእንስሳት አካሎች በፍጥነት ይደርቃሉ፣ ይተረሻሉ፣ ይጠወልጋሉ፣ የመበስበስ እና የመፈራረስ ፀባያቸውን ያጣሉ፤ ወይኖች እና ሌሎች ፍራፍሬዎች ጠጣር ይሆናሉ በከፌል ልክ እንደ ከረሚላ እና እንደ ዘቢብ የደረቁ ይሆናሉ፡፡ ከቀናት በኋላ ሬሳ ወይም የእንስሳት ስጋ ይረጋል ተለዋዋጭ አየራዊ አካሎቹን ያጣል ይከስማል፣ ይደርቃል፣ ለመበስበስ ይዘገያል፡፡ በአንጻሩ የእጽዋት እና የእንስሳት አካል ለጨረቃ ብርሃን ሲጋለጥ ግን የመበስበስ እና የመፈራረስ ምልክቶችን ማሳየት ይጀምራል፡፡ ይህ የሚያረጋግጠው የፀሐይና የጨረቃ ብርሃን የተለያየ እንደሆነና በጅኦሴንትሪክ ዝርጉ ሞዴል እንደተቀመጠውም ብርሃናቸው የነጠረ ልዩ እና ተቃራኒ መሆኑን ነው፡፡

133) በቀጥታ የፀሐይ ብርሃን ላይ የተቀመጠ ቴርሞሜትር ከሌላው ጥላ ውስጥ ከተቀመጠው ቴርሞሜትር ይልቅ የበለጠ

ሁኖ ይነበባል። በአንጻሩ ግን በቀጥታ የጨረቃ ብርሃን ላይ የተቀመጠ ቴርሞሜትር ከሌላኛው ጥላ ውስጥ ከተቀመጠው ቴርሞሜትር ያነሰ ሁኖ ይነበባል። የፀሐይ ብርሃን ከአንድ ትኩረት ነጥብ ባለ ትልቅ ሌንስ ተወርውሮ ቢሆን፤ የሚታይ መቀትን መፍጠር ይችል ነበር። ተጠራቅሞ ተንጸባረቀ የሚባለው የጨረቃ ብርሃን ግን ምንም አይነት መቀት የለውም፤ በ‹‹Lancet Medical Journal›› ከመጋቢት 14 1856 ጀምሮ ብዙ የተለያዩ መኽራዎች የቀረቡ ሲሆን፤ እነዚህም የጨረቃ ጨረር የሚያርፍበት ቴርሞሜትር ከስምንት ዲግሪ በሚበልጥ ቅዝቃዜ መቀቱን እንደሚቀንሰው ያረጋገጡ ነበሩ። ስለዚህ ሁለቱም የፀሐይና የጨረቃ ብርሃኖች በግልፅ የተለያየ ጸባይ ነው ያላቸው።

134) በተጨማሪም ጨረቃ ራሷ በአካል ሁለቱንም ሉላዊና የፀሐይ ብርሃንን አንጸባራቂ ልትሆን አትችልም። አንጸባራቂዎች የብርሃን ጨረሮች በማንኛውም ማዕዘን እንዲከሰቱ ዝርግ ወይም ጎድጓዳ ምስሪት አካል መሆን አለባቸው። የአንጸባራቂው ገጽ እብጥ ምስሪት ቢሆን ሁሉም የብርሃን ጨረር ከራዲየሱ ጋር በቀጥተኛ ነጥብ ከገጹ ጋር ደግሞ በ90 ዲግሪ ዘዌ ሁኖ ነጸብራቅ የሌለው ውጤት ያስከትል ነበር።

135) ጨረቃ የራሷ ልዩ ብርሃን ያላት ብሩህ አካል ብቻም አይደለችም፤ ግን በትልቁ እንዲሁ በውስጧ የምታሳይ ብርሃን አሳላፊም ነች፤ በቀን ውስጥ ሙሉ ወይም ግማሽ ጨረቃ በሚታይበት ወቅት በጨረቃ ውስጥ ሰማያዊውን ሰማይ ማየት ይቻላል። ጥርት ባለ ምሽት በሙሉ ወይም በጠፍ ጨረቃ ዑደት ወቅት አልፎአልፎ ከዋክብትና ‹‹ፕላኔቶችንም›› እንኳ ቀጥታ ጨረቃ ገጽ ላይ በጨረቃ ውስጥ ማየት ይቻላል። ንጉሳዊው የጠፈርተኞች ማህበር በታሪክ ውስጥ ብዙ የዚህ አይነት ክስተቶችን መዝግቧል። ሁሉም ፀሐይን ማዕከል ያደረገውን የተንቀሳቃሿን ዓለም ሞዴል የተቃወመ ነበር።

136) ብዙ ሰዎች የዘመኑ ጠፈርተኞች በትክክል የጨረቃና የፀሐይ ግርዶሽን መተንበይ መቻል፤ የተንቀሳቃሿን ዓለም ንድፈ ሀሳብ እውነተኛነት ማረጋገጫ ውጤት ነው ይላሉ። እውነታው ግን የ ‹‹የተንቀሳቃሿ ኳስ ዓለም›› ንድፈ ሃሳብ በኮፐርኒከስ ከመሰራቱ በፊት ለሺህ አመታት በመላው ዓለም ያሉ ባህሎች ግርዶሽን በትክክል እየተነበዩ መኖራቸው ነው። ቶለሚ በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን(ከልደተ ክርስቶስ በኋላ) ለስድስትመቶ አመታት በትክክል ግርዶሽን መተንበይ ችሏል። ወደኋላ በ 600 አመተ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ፤ ቱልስ በሚዳውያን እና በሊዲያዎች መካከል የነበረውን ጦርነት ያስቆመውን ግርዶሽ በትክክል ተንብዮል። ግርዶሽ በመደበኛነት በየ18 አመት ዑደት ይከሰታል፤(ከተርጓሚ ቃል፡ ጥንት ኢትዮጵያውያንም በአቡሻኽር መጽሐፋቸው ይህ የሚፈጠርበትን ስሌት ሲያውቁ ኑረዋል። በየአስራዘጠኝ አመቱ የሚፈጠር የፀሐይና የጨረቃ ግንኙነት ሲል <u>ዓውደ አበቅቴ</u> ብሎ ባሕረ ሀሳብ ያስቀምጠዋል።) ስለዚህ ቋሚው ወይም ተንቀሳቃሹ ዝርጉ ወይም ሉላዊው ምድርን በተመለከተ ሳይሆንም ግርዶሽ በትክክል ከእነዚህ ምክንያቶች ውጭ ሁኖ ለብቻ መሰላት ይችላል።

137) ሌላው የምድርን ቅርጽ ማረጋገጫ ነው ተብሎ በተንቀሳቃሿ ዓለም አማኞች ዘንድ የሚታሰበው፤ የጨረቃ ግርዶሽ የሚከሰተው የምድር ጥላ ጨረቃ ላይ በሚያርፍበት ጊዜ ነው የሚለው ነው። እነርሱ እንደሚሉት ፀሐይ ምድርና ጨረቃ ሉሎች እንደ ሶስት የጉል ኳሶች በትክክለኛ ረድፍ ሲሰለፉ ነው፤ ስለዚህ የፀሐይ ብርሃን የምድርን ጥላ በጨረቃ ላይ ያሳርፋል መባሉ ነው። በሚያሳዝን ሁኔታ ግን በተንቀሳቃሿ ዓለም አማኞች የተሰጠው የዚህ አይነቱ ማብራሪያ በእውነታው በሚታየው፤ በተፈጠረውና እየቀጠለም በተከታታይ በመፈጠር ላይ ባለው የጨረቃ ግርዶሽ፤ ሁለቱም ፀሐይና ጨረቃ ከአድማስ በላይ በሰማዩ ላይ እየታዩ ግርዶሹ መከሰቱ፤ ማብራሪያውን ሙሉበሙሉ ዋጋቢስ አድርጎታል። የፀሐይ ብርሃን የምድርን ጥላ በጨረቃ ላይ እንዲያሳርፍ ሶስቱም አካሎች በቀጥተኛ የ180 ዲግሪ አሰላለፍ መደርደር ነበረባቸው፤ ነገር ግን በቅርብ በፕሊኒ ወቅትም እንደነበረው፤ የጨረቃ ግርዶሽ ሁለቱም ፀሐይና ጨረቃ በሰማዩ ላይ እየታዩ ሲከሰት የመዘገቡ ሰነዶች አሉ። ስለዚህ የጨረቃ ግርዶሽ አድራጊ ምድር/የምድር ጥላ ሊሆን አይችልም። ሌላ ማብራሪያ እንዲሰጥ ያስፈልጋል።



138) ሌላው ጥሩ ማስረጃ ብለው የኳሷ ዓለም አማኞች የሚያቀርቡት፤ ለተመልካች ከባህር ዳርቻ ላይ የመርከብ አካል በውሃው እየተጋረደ መሄድና መርከቡ በጣም እርቆ ሲሄድ ሙሉበሙሉ ከእይታውጭ መሆኑን ነው። የመርከቡ የላይኛው ጫፍ እየታየ ታችኛው ክፍል በውሃው ለእይታ መጋረድ ምክንያት መርከቡ በኳሷ ምድር እብጥ ምስሪት በሆነው ከርቭ ላይ እየተንዘ ነው የሚለው ነው። አሁንም በድጋሜ ግን የእነርሱ ችኩል የሆነ ማጠቃለያ ያወጣው የተሳሳተ ፍቃድን ነው፤ ይህም የዚህ አይነቱ ክስተት የሚፈጠረው በኳሷ ዓለም ብቻ ነው ብሎ ማሰቡ ነው፤ በእውነታው ታሪክ እንዲሁ የሩቅ እይታ ህግ በዝርግ ገጽ ላይ የሚያሳየውና እንድንረዳ የሚያስገድደው በትክክል ተመሳሳይ ክስተትን ነው፤ ለምሳሌ ቀሚስ የለበሰች ሴት ሜዳ ላይ ወደ አድማሱ ስትንገዘ፤ በጣም እርቃ በሄደች ቁጥር እያነሰችና ወደታች

እየዘቀጠች ትታያለች፤ በመጀመሪያ እግሯ ከይታ ውጭ ይሆናል ከዛም በመሬቱና በቀሚሷ ጫፍ መካከል የነበረው ክፍተት ቀስበቀስ እየጠፋ ይሄዳል፤ እንዲሁ ከግማሽ ማየል በኋላ ቀሚሷ መሬት ነክቶ እና በማይታይ እግር እየሄደች ይመስላል፤ በዝርግ ገጽ ላይ ጉዳዩ ልክ እንደዚህ ነው። የአካሉ የታችኛው ክፍል ከሚታይበት ነጥብ እርቆ ሲሄድ የግድ ከላይኛው ክፍል ቀድሞ ይጠፋል።

139) የመርከብ አካል እየዘቀጠ ከእይታ መጥፋት በዝርግ ገጽ የእርቀት እይታ ህግ ላይ ብቻ የተብራራ ጉዳይ አይደለም፤ በእርግጥ እውነት እንደሆነ በጥሩ ቴሌስኮፕ እገዛም የተረጋገጠ ነው። በአይናችን ብቻ መርከብ ወደ አድማሱ እርቆ እየሄደ በተባለው የምድር ክርቭ ምክንያት መርከቡ ሙሉበሙሉ ከእይታ ውጭ ሲሆን ካየን፤ ወዲያውኑ በቴሌስኮፕ ውስጥ ደግሞ ስናይ፤ ቀርቦና መላ መርከቡ ከላይ እስከታች እይታ ውስጥ ሲገባ እናስተውላለን። ከእይታ ውጭ የሆነው ክርቭ ባደረገው የውሃ ግድግዳ ተጽዕኖ ሳይሆን በሩቅ እይታ ህግ ምክንያት እንደሆነ ሲያረጋግጥልን ነው።

140) በዙሪዜ የፎኮልት ፔንዱለም የምድርን እሽክርክሪት ማሳያነው ነው ይላሉ፤ ነገረ ግን በቅርብ ምርመራ ተቃራኒው እንደሆነ ነበር የታወቀው። ሲጀመር የፎኮልት ፔንዱለም በአንድ አይነት አቅጣጫ አይሽከረከሩም አንዳንዴ ከግራ ወደቀኝ ሌላጊዜ ደግሞ ከቀኝ ወደግራ ነው የሚሽከረከሩት፤ አንዳንዴ መሽከርከርም ሁሉ ያቅታቸዋል፤ የሆነግዜ ደግሞ እጅግ በመፍጠን ይሽከረከራሉ፤ በእውነቱ የፔንዱለሞቹ ጸባይ የሚወሰነው 1) እሽክርክሪቱን ለማስጀመር በተጠቀምነው የመጀመሪያ ጉልበት እና 2) የተጠቀመው ኳስ እና የኳሱ ማንከባለያ መገጣጠሚያ አንጓ በየትም ክባዊ ዙሪትን ያመቻቸ በመሆኑ ነው። የሚባለው የምድር እሽክርክሪት ሙሉበሙሉ ከፔንዱለም እንቅስቃሴ ጋር የማይኳኋን እና የማይገናኝ ነው። የተባለው የማያቋርጥ የምድር እሽክርክሪት በማንኛውም መልኩ በፔንዱለሞች ላይ ተጽዕኖ አድርጎ ቢሆን፤ የፔንዱለሞችን እንቅስቃሴ በእጃችን ማስጀመር አይጠበቅብንም ነበር። የምድር ዕለት ዕለት እሽክርክሪት ሁልጊዜ ወጥ ሁነው 360 ዲግሪ ለሚዞሩ ፔንዱለሞች ምክንያት ቢሆን ኑሮ፤ በምድር ላይ በየትኛውም ቦታ እሽክርክሪት የሌለው የቆመ ፔንዱለም ሊኖር አይገባም ነበር።



141) ሌላው ብዙ ጊዜ የኮሪዮሊስ ውጤት(Coriolis Effect) የሽንት ቤት ጽዳጅ ውሃ በሰሜኑ ንፍቀ ክበብ አንድ አቅጣጫ ይዞ እየተሽከረከረ ይገባል፤ በደቡቡ ንፍቀ ክበብ ደግሞ በተቃራኒ አቅጣጫ ሁኖ እየተሽከረከረ ይገባል በሚል ይሄ የምድርን እሽክርክሪት ማሳያ ነው መባሉ ነው። አሁንም ግን በድጋሜ እንዲሁ በሌላ አቅጣጫም እንደሚዞሩት ልክ እንደ ፎኮልት ፔንዱለም በሰሜኑና በደቡቡ ንፍቀ ክበብ የገንዳ ውሃዎች እና የሽንት ቤት ጽዳጆች በቋሚነት አንዱን አቅጣጫ ብቻ ይዘው አይሽከረከሩም። ብዙ ጊዜ በአንድ ቤት ውስጥ ባሉ ገንዳዎች እንኳን እሽክርክሪቱ የሚወሰነው በመላ የገንዳው ቅርጽና ውሃው ከሚገባበት አንግል አንጻር በመሆኑ የተለያየ አቅጣጫን ይዘውም እንደሚዞሩ ማወቅ ተችሏል፤ በሚባለው የምድር እሽክርክሪት ምክንያት አይደለም።

142) ሰዎች ምድር ዝርግ ብትሆን ኑሮ ቴሌስኮፕን በመጠቀም ባህር ማዶ ድረስ በግልጽ ማየት እንችል ነበር ብለው ያስባሉ። ነገር ግን ይሄ ሞኝነት ነው ምክንያቱም አየሩ በሞላ ብዙ ንጥረ ነገሮችን በውስጡ ስለሚይዝና ወደላይ እየተነኑም ጉምን የሚፈጥሩ ጢሶችን በመያዙ፤ በተለይ በባህሮች ላይ እና እንዲሁም በተለይ በታችኛው ጥቅጥቅ ባለው የከባቢ አየር ክፍል ከሩቅ ምስልን ለማሳየት ብርሃን አሳላፊ አይደለም። የሩቅ የመንገድ ላይ ፎቶዎች በሞቃትም በቀዝቃዛም ቀናት ይደበዝዛሉ፤ እጅግ ጥሩ የሚባለው ቴሌስኮፕ እንኳ ገና ከባህር ማዶ ከማየታችን አስቀድሞ ይደበዝዛል፤ በአንጻሩ ግን በኳሷ ባለ 25,000 ማየል ዙሪያ ምድር የማይቻለውን ቴሌስኮፕን በመጠቀም በይበልጥ ዝርዝ ምድራችንን እያቀረብን ማየት እንችላለን።

143) ሰዎች ምድር ዝርግ ሁና ቢሆን ኑሮ እና ፀሐይ በእኛ ላይ ክብ እየዞረች ቢሆን፤ በምድር ላይ በየትኛውም ቦታ ላይ ሁነን ፀሐይን ማየት እንችል ነበር፤ እንዲሁ በምሽት ጊዜም የቀን ብርሃን ይሆን ነበር ብለው ይሟገታሉ። ምክንያቱ ፀሐይ 93 ሚሊየን ማየል ስለማትርቅና እንደሚባለው በጣም ግዙፍ ስላልሆነች፤ ግን ደግሞ በትንሽ ሺህ ማየሎች ከፍታ ላይ ስለሆነች፤ የምታበራውም ልክ እንደ አምፖል በመሆኑ ነው። በኋላ ሁኔታ አንድ ጊዜ ካለንበት ቦታ በጣም እርቃ ስትሄድ፤ ከአድማሱ ባሻገር አልፎ የማይታይ ይሆናል፤ ሙሉበሙሉ እስከምትጠፋ ድረስ የቀን ብርሃን ቀስበቀስ ይደበዝዛል። ፀሐይ 93 ሚሊየን ማየል የምትርቅና ምድር የምትሽከረከር ኳስ ቢሆኑ ኑሮ፤ ከቀን ብርሃን ወደ ምሽት የሚኖረው ሽግግር የተጠመዘዘውን መስመር እንዳለፈ ፈጣን ይሆን ነበር።



144) የጨረቃ ፎቶ በደቡብ ንፍቀ ክበብ ከላይ ወደታች ተዘቅዝቃ፤ በሰሜኑ ንፍቀ ክበብ ደግሞ ወደላይ ተቃንታ መታየት ብዙጊዜ ለምድር ኪስነት እንደ ማስረጃ ዋቢ ተደርጓል፤ አሁንም በድጋሜ በቀረበ ምርመራ ሌላው የዝርጉ ሞዴል ማስረጃ እንደሆነ ነው ያወቅነው፤ በእርግጥም የጊዜ ዑደትን የሚያሳይ ፎቶም የሚያስረዳው ጨረቃ በምድር ዙሪያ ክብ ስትዞር ልክ ራሷ ከመሀል ቦታው ተወጥሮ እንደተያዘ የሰዓት መቁጠሪያ ተሽከርካሪ ሁና፤ ወደ መሀለኛው ቦታ እያመለከተች በሰዓታዊ አቅጣጫ በምድር ላይ እንደምትዞር ነው፡፡ በቀላሉ የተነሳበትን ጊዜና ቦታ ብቻ መሰረት በማድረግ የጨረቃን የተለያዩ የ360 ዲግሪ ዝንባሌዎች የሚያሳዩ ፎቶዎችን ማግኘት እንችላለን፡፡



145) ጨረቃ ምንም እንኳ ገጽታዋ ግልጽ ዝርግና ብርሃናማ ዲስክ ሁኖ ቢቀርብም፤ የተንቀሳቃሿ ዓለም እማኞች ጨረቃ ኳስ ቅርጽ ነች ብለው ያምናሉ፡፡ እኛ ሁልጊዜ የጨረቃን ተመሳሳይ አንድ ገጽ ብቻ ነው የምናየው(ምንም በተለያየ ዝንባሌ ቢሆንም እንኳን)፤ ሆኖም ግን ሌላ ሁልጊዜ ተደብቆ የሚቀር ‹‹ጨለማው የጨረቃ ክፍል›› የሚባል ገጽ እንዳላት ነው የሚነገረው፤ ናሳ እንደሚለው፡- የጨረቃ እሽክርክሪት ከምድር እሽክርክሪት በተቃራኒ አቅጣጫ ነው፤ በፍጽም እኩል በሆነው የተቃራኒ አቅጣጫ እሽክርክሪታቸው እንቅስቃሴያቸው እርስበርሱ ተጣፍቷል፡፡ ስለዚህ እኛ እነርሱ ከሚያቀርቡልን መጥፎ የሀሰት ፎቶግራፍ(CGI) ውጭ በምቹ ሁኔታ የሚባለውን የጨረቃ ጨለማ ክፍል ልንመለከት አልቻልንም፡፡ በእውነታው ግን ጨረቃ ሉል ብትሆን ኑሮ፤ ከአንታርክቲክ ያለ ተመልካች ከምድር ሰቅ ካለው ይልቅ የተለየ ገጿን ማየት ይችል ነበር፤ ምንም ቢሆን ግን አያዩም፡ እንዲሁ ተመሳሳዩን ዝርግ ገጽ ከልዩ ዘዌ ዙሮ ነው የሚያዩት፡፡

146) የኳሱ ዓለም ሞዴል ጨረቃ በምድር ዙሪያ በየ28 ቀን አንዴ ነው የምትዞረው ብሎ ያቀርባል፡፡ የሚገርመው ግን ጨረቃ በእያንዳንዷ ቀን ምድርን እንደምትዞር ለማንኛውም ሰው የሚታይ ግልጽ ጉዳይ መሆኑ ነው፤የጨረቃ ዙሪት ፍጥነት ከወሐይ በጥቂቱ ያንሳል፤ ይሁን አንጅ የወሐይን ተመሳሳይ መንገድ እየተከተለች ከትሮፒክ እስከ ትሮፒክ ከሶላስቲክ እስከ ሶላስቲክ ከ25 ሰዓት በታች በሆነ ጊዜ በምድር ላይ ሙሉ ክብን እየሰራች ትዞራለች፡፡

147) የኳሱ ዓለም ሞዴል ወሐይ በትክክል ከጨረቃ 400 እጥፍ አደምትገዝፍና ከምድር ደግሞ 400 ጊዜ እንደምትርቅ በዚህም ‹‹በተሳሳተ መልኩ›› ሁለቱንም ወሐይና ጨረቃን ተመሳሳይ ግዝፈት ያላቸው መስሎ እንዲታየን እንዳደረገ ይገልጻል፡፡ አሁንም እንደገና የኳሱ ሞዴል በተፈጥሮ አሰራራቸው በቃ እንዲሁ ነው ብቻ ሊባል የሚችለውን ነገር ገጠመኝ ነው ብለን እንድንቀበል እየጠየቀን ነው፡፡ ወሐይና ጨረቃ በሰማዩ ላይ ተመሳሳይ መጠን ያለው ቦታን ይይዛሉ፤ በሴክስታንት ተለክተውም እኩል መጠንና እኩል እርቀት ነው ያላቸው፡፡ በሌላኛው መልኩ መሟገት ግን ከአይናችን፣ ከልምምዳችን፣ ከሙከራዎች እና ከስሜት ህዋሳችን ጋር መቃረን ነው፡፡



148) በ ‹‹Earth Not a Globe!›› መጽሐፍ ከሳሙኤል ሮባተም አባባል ‹‹በምልከታ የተገኘው ደህ ነው: ኮከቦች በየ24 ሰዓቱ ከፀሐዩ 4 ደቂቃ ቀደም ብለው ወደ ሜሪዲያኑ ደመጣሉ፤ የፀሐዩን ሰዓት እንደ መደበኛ መቁጠሪያ ስንመለድ በ30 ቀናት ውስጥ የ120 ደቂቃ በለመት ውስጥ ደግሞ የ24 ሰዓት ልዩነት ደፈጥራል፡፡ ደህም ማለት ሁሉም ህብረ ኮከብ ከፀሐዩ በፊት ወደም ከዛ ሰዓት ቀድሞ እያለፈ ነው፤ ደሄ በቀላሉ የሚታዩ የተፈጥሮ እውነታ ነው፡፡ ነገር ግን በድኩልኩልነት ንድፈ ሀሳብ በምህዋርና ዛቢያዊ እንቅስቃሴ ደሄ ክስተት ቦታ የለውም፤ የሚታዩ እውነቶች መመገድ ስለባቸው፤ ምክንያቱም ደሄ ቲመሬ የሚቆመው ተከታዮቹን ነገሬ እንዳደገባቸው ለመጠበቅ ነው፡፡››

149) በሺህ አመታቶች ውስጥ ህብረ ከዋክብቶቹ ባሉበት ተመሳሳይ አቀማመጥ ቋሚ ሁነው ነው የቀሩት፤ ምንም ቢሆን ሀረጋቸውን ሳይለቁ፡፡ ልክ ናሳ እንደሚለው ምድር ትልቅ ኳስ ሁና በትልቅ ፀሐይ ዙሪያ እየተሽከረከረች፣ በትልቅ ጋላክሲ እየዞረች፣ ከቢግባንጉ እየተተኮሰች ቢሆን ኑሮ፤ በእነርሱ ሞዴል መሰረት

ህብረ ከዋክብቱ ቋሚ ሁኖ እንዲቆይ የማይቻል ይሆን ነበር። በእውነቱ እኛ በእያንዳንዱ ምሽት ሙሉበሙሉ የተለየ የምሽት ሰማይ ልናይ ይገባ ነበር፤ በትክክል አንድአይነት የሆነ የከዋክብት አቀማመጥ ደግመን ልናይ አይገባም።

150) ምድር የምትሽከረከር ኳስ ብትሆን ኑሮ በፖላሪስ ዙሪያ የጊዜ ዑደትን በሚያሳይ ፎቶግራፍ/star-trail time-lapse ፍፁም ክብ ቅርፅ ሲዞር ማንሳት የማይቻል ይሆን ነበር፤ ከየትም ግን በሰሜን ዋልታ። በሁሉም ሌላ አመች ቦታ ኮከቦች ከተመልካች እግር በታች አለ በተባለው በሰዓት የ1000 ማየል እንቅስቃሴ ምክንያት በተመልካች አድማስ እዳር አስከዳር ከሞላ ጎደል አግድም ሲጓዙ ነበር እንዲታይ የሚሆነው። በእውነታው ግን በፖላሪስ ዙሪያ ያሉ ኮከቦች እታች እስከ ትሮፒክ ኦፍ ካፕሪኮርን ድረስ ምንጊዜም በመሀከለኛው ኮከብ ዙሪያ በትክክለኛ ክብ ቅርጽ ሲጓዙ መቅረጽ ይቻላል።

151) ምድር የምትሽከረከር ኳስ ሁና በፀሐይ ዙሪያ የምትጓዝ ቢሆን ኑሮ፤ በእውነቱ በሰሜን ዋልታ እንኳ የኮከብን የጊዜ ዑደት በሚያሳየው ፎቶ ትክክለኛ ክብ ቅርጽን እንድናይ የማይቻል ይሆን ነበር። ምክንያቱም ምድርም እንደተባለችው በሰዓት 67,000 ማየል በፀሐይ ዙሪያ እየተንቀሳቀሰችና፤ ፀሐይ በሰዓት 500,000 ማየል ወደ ሚልኪወይ እየሄደች፤ በመላ ጋላክሲው ደግሞ በሰዓት 670,000,000 ማየል እየተጓዘ ስለሆነና እነዚህ እርስበርስ የሚጋጩ እንቅስቃሴዎች ሁሉንም የኮከብ የጊዜ ዑደት የሚያሳይ ፎቶ ቅርጽአልባ የተጠመዘዘ መስመርን እንዲያሳይ ያደርጉት ነበር።

152) በ2003 የሶስት ዩንቨርስቲ ጆኦግራፊ ፕሮፌሰሮች በመተባበር የካንሰስ ግዛት በእርግጥም ከፓንኬክ ይልቅ ዝርግ ነው የሚለውን ለማረጋገጥ ጥናት አድርገዋል። መልካምድራዊ ጆኦደቲክ መመርመሪያዎችን በመጠቀም ከ80,000 ማየል ካሬ በላይ ቦታን አዳርሰው፤ በመላ ግዛቱ ውስጥ ካንሰስ የ0.9997 የዝርግነት ንጽጽር እንዳለው ነበር የተገለጸው። አማካኙ የፓንኬክ በትክክል ኮንፎካል ሌዘር ማይክሮስኮፕን በመጠቀም ሲለካ ወደ 0.957 ነው የመጣው፤ ይህም ምክንያት ካንሰስን በግልፅ ከፓንኬክ ይልቅ ዝርግ ያደርገዋል።



153) ‹‹Atlas of Physical Geography›› ከተከበሩ ቶማስ ሚልነር አባባል እንዳገኘነው ‹‹ብዙ ስፍራዎች በትክክለኝነት ዝርግ የሆነ ወሰል ስላቸው፤ በ1,500 ማየል ውስጥ ከካርፓቲያንስ እስከ ዩራልስ በደቡብ ባልቲክ ምንም ያህል ልዩነት የሰም፤ ዘገረ በጣም ዝርግ በመሆኑ በሸንድ ቦታ የሚነፍሰው የሰሜን ነፋስ የስታቲነር ሀፍን ውሃ እስከ ኦደር ስፍ ድረስ ደነዳዋቧል፤ እና ወንዙን ከ30 እስከ 40 ማየል የኋሊት ፍሰት እንዲኖረው ያደርጋል። በደቡብ ስሜፈላ በተሰዩ ከኦርኖኮ በስተግራ የቬንዙዌላና የኒው ግራናዳ ሜዳ ሲላኖስ ወደም ስጥ ያሉ ስፍራዎች ተብሱ ደጠራል፤ ባብዝሀኛው ቦታው ውስጥ ስ270 ማየል ካሬ ገጹ ስሸንዲት ጫማ ያህልም ሸንኳ ልዩነት ስደፈጥርም። ከወንዞች የስማዞኑ እስከመጨረሻው በ700 ማየል እርዝመቱ የ12 ጫማ ያህል ብቻ ነው ወደታች ቁልቁል የሚወርደው፤ የሳንሳታ በማየል ውስጥ የሸንድ ስላሳስተኛ ሲንች ብቻ ነው ቁልቁል የሚወርደው።››

154) የፊሊክስ ባምጋርትነር ሬድቡል ዝላይ የውጨ ካሜራ ከላይ ከመዝለያው ከፍታ እና ከሚያርፍበት የምድር ወለል ከፍታ ላይ ተመሳሳይ የሆነ ከርቭ ‹‹የምድር መጠምዘዝ›› ነው የሚያሳየው፤ የማታለያ fish-eyed wide-angle lens እንደተጠቀመ እያረጋገጠልን ነው። በውስጥ ያለው መደበኛ ካሜራ ግን ከ128,000 ጫማ ከፍታ በትክክል ዝርግ የሆነውንና ከአይን ከፍታ ጋር እኩል ሁኖ የሚታየውን አድማስ እያሳየ ነው። ይህም ማለት ከዝርግ ጠለል ጋር ብቻ ነው ሊጣጣም የሚችለው።



155) አንዳንድ ሰዎች በአውሮፕላን መስኮት ውስጥ የምድርን መጠምዘዝ ማየት እንደቻሉ ይሞግታሉ፤ ዳሩ ግን በሁሉም የህዝብ ማመላለሻ አውሮፕላኖች የሚገጠሙ መስታውቶች ከውጨኛው የአየሩ ክፍል ጋር እንዲገጥሙ ተብሎ ስለሚሰራ የተጠመዘዙ በመሆናቸው ነው፤ ይህ ትንሽ ተጽኖ ይፈጥራል፤ ከአድሎ ማረጋገጫነት ጋር ተቀይጦ ሰዎች በስህተት የሚባለው የምድር መጠምዘዝ እንደሆነ አድርገው ይወስዳሉ። በእውነታው በዚሁ በ35,000 ጫማ ከፍታው በአየራችን ግራና/ቀኝ መስኮቶች አድማሱን ከአይን ከፍታ ጋር እኩል ሁኖ የምናይበት ሀቅ የሚያስረዳው የምድርን ዝርግነት ነው። ምድር ኳስ ብትሆን ኑሮ

ምንም ያህል ትልቅ ብትሆን አድማሱ በትክክል ባለበት ይረጋ ነበር፤ እና አድማሱን ሙሉ ለማየት በተጨማሪ ወደታች እያቀረቀርን ማየት ነበረብን፤ በ35,000 ጫማ ከፍታ ወደግራም ወደቀኝም ቀጥታ ወደመስኮት ስናይ የምድር አድማስ ከእኛ በታች መሆን ስለነበረበት ሊታየን የሚገባው ሌላ ምንም ሳይሆን የውጨኛው ህዋ ነበር፡፡ አድማሱ በውጭ በኩል በሁለቱም ጎን መስኮቶች ከአይን ከፍታ ጋር እኩል ሁኖ ከታየ ምክንያቱ ምድር ዝርግ ስለሆነች ነው፡፡



156) ሰዎች አሁንም በ ጎፕሮ ወይም በሌላ የትልቅ ከፍታ ካሜራዎች አድማስ ቀረጻ መጠምዘዙን እንዳዩ ይናገራሉ፡፡ በእርግጥ እውነት ነው በእንደዚህ አይነት ቀረጻ አድማሱ የጎበጠ ሁኖ ይታያል፤ ብዙ ጊዜ በዚህ አነሳስ ጎብጦ ወይም ዝርግ ሁኖ መታየቱ የሚወሰነው በካሜራው ዝንባሌ/እንቅስቃሴ ነው፡፡ የዚህ ውጤት ምክንያት በአጭሩ የተዛባ wide-angle lense በመደረጉ ነው፡ ሌንሱ ሲስተካከልና ያለ ዋይድ አንግል ቴክኖሎጅ በተነሱ ሁሉም የትልቅ ከፍታ አማተር ቀረጻዎች በትክክል ዝርግ ሁኖ ነው የሚቀርበው፡፡

157) ‹‹ግራቪቲ›› በአስደናቂ ሁኔታ የአየር ንብረቱንም ጎትቶ ከምትሽከረከረው ኳስ ምድር ጋር አብሮ እንዲዞር ካደረገ፤ ያም ማለት በምድር ሰቅ አቅራቢያ ያለው የአየር ንብረት በሰዓት ከ1000 ማየል በላይ ይሽከረከራል፤ ከመሀከለኛው ኬክሮስ በላይ ያለው ደግሞ በሰዓት ወደ 500 ማየል ይሽከረከራል እና ቀስበቀስ እየቀነሰ ሂዶ ዋልታው ላይ ያለው የአየር ንብረት በዚህ ምንም ሳይጠቃ በሰዓት የ0 ማየል እንቅስቃሴ ይሆናል ማለት ነው፡፡ በእውነታው ግን በምድር ውስጥ እኩል ሁሉም ቦታ ያለው የአየር ንብረት በሚባለው እንቅስቃሴ ጉልበት ተፅእኖ ውስጥ አይደለም፡፡ ተለክቶ ወይም ተሰልቶ ስለማያውቅና አውሮፕላኖች ያለማቋረጥ ሳይገደቡ በማንኛውም አቅጣጫ መብረር በመቻላቸው እንዲሁም ያለምንም አይነት የሚዞር አየር ንብረት ለውጥ ገጠመኝ መሆኑ፤ የዚህ አይነቱ መሽከርከር እንደሌለ ነው የሚያሳየው፡፡



158) ‹‹ግራቪቲ›› በአስደናቂ ሁኔታ ከባቢ አየሩንም ጎትቶ ከምትሽከረከረው ኳስ ምድር ጋር አብሮ እንዲዞር ካደረገ፤ ይህም ማለት ከፍታ በጨመርን ቁጥር የከባቢ አየሩም መሽከርከር እየፈጠነ እየሄደ በዋናው እሽክርክሪት ዙሪያ በመዞር እየታጠፈ መሆን አለበት ማለት ነው፤ በእውነታው ግን ይህ እየሆነ ቢሆን ኑሮ ዝናብ እና እርችቶች ከአንደኛው ቦታ ወደ ሌላኛው ቦታ ቀስበቀስ እሽክርክሪቱ እየቀነሰ እየቀነሰ ወደሚመጣው የአየር ንብረት ወደታች ሲወርዱ ሙሉበሙሉ የተለየ ፀባይ ያሳዩ ነበር፡፡ የሙቅ አየር ባሉኖች ወደላይ ፍጥነቱ እየጨመረ ወደሚሄደው ከባቢ አየር በተጠጉ ቁጥር ያለማቋረጥ ከምስራቅ ወደ ምዕራብ እየፈጠኑ እንዲጓዙ ያስገድዳቸው ነበር፡፡

159) ከፍታ በጨመረ ቁጥር ቀስበቀስ እየፈጠነ እየፈጠነ የሚሽከረከር የአየር ንብረት ቢኖር ኑሮ፤ አንድ የሆነ ከፍታ ላይ በድንገት ይሄ ነገር ይቆማል ማለት ነው፡፡ ይህም ፈጣኑ ግራቪቲያዊው የሚሽከረከረው የአየር ንብረት ክፍል እና የሚባለው ግራቪቲያዊ ያልሆነው የማይሽከረከረው አየር ንብረት ያልሆነው የማያልቀው ባዶ ህዋ/vacuum space የሚገናኙበት ቦታ ነው፡፡ ናሳ በምን ያህል ከፍታ ላይ እንደሆነ ይህ የማይመስል ነገር የሚከሰተው አልጠቀሰም፤ ግን ይሄ በቀላሉ በፍልስፍናውም በአንድላይ አየር ያለበት እና አየር የሌለበት ባዶ ስፍራ ተያይዘው እንደማይኖሩ በቀላሉ እውነታ ውድቅ የተደረገ ነው፡፡ ቢቻል ኑሮ እንኳን አየር የሌለበት ባዶ ስፍራ(vacuum) የሚኖሩትን ጸባያት ስንከተል፤ ለሮኬቶች ‹‹space ship›› በእንደዚህ አይነት ሽግግር ተጽኖ ሊኖር የሚችለውን አስከፊነት መጥቀስ አያስፈልግም፡፡

160) ለሮኬቶች ወይም ለማንኛውም በጀት ግፊት ሞተር ለሚሰራ፤ በሚወራለት አየር የሌለው ባዶ ህዋ ላይ ለመብረር የማይቻል ነው፡፡ ምክንያቱም ገፍተውት ይጓዙ ዘንድ አየር/የአየር ንብረት ባለመኖሩ መሳሪያው ወደፊት እንዲጓዝ ምንም አይነት ጉልበት አያገኝም፤ ይልቁንም ሮኬቶችና ሻትሎች መቆጣጠር በማይቻልበት ሁኔታ በሁሉም አቅጣጫ ልክ እንደ ጃይሮስኮፕ በራሳቸው ዛቢያ እየተሽከረከሩ ይጓዛሉ፤ ወደ ጨረቃ ለመብረር ወይም ወደሌላ አቅጣጫ ለመጓዝ ምንም ቢሆን የማይቻል ይሆናል፡፡ በተለይም ‹‹ግራቪቲ›› እውነት ከነበርና ያለማቋረጥ ወደ ቅርቡ ግዙፉ አካል የሚጎትተን ከሆነ፡፡

161) በእውነት ምድር ኳስ ብትሆን ኑሮ ወደ ‹‹ውጨኛው ህዋ›› ለመብረር ሮኬትን የምንጠቀምበት ምንም ምክንያት አይኖርም

ነበር፤ ምክንያቱም በቀላሉ በአውሮፕላን ውስጥ በማንኛውም ከፍታ ላይ ቀጥ ብሎ ለአረዝም ሰዓት መብረር ምድርን አስጥሎ ወደ ውጨኛው ህዋ ሊልከንና ሊያስወጣን ይገባልና። አውሮፕላናቸው ከካሲ ምድር ታካኪ መስመር ሁኖ እንዳይበር ለመጠበቅ፡ ፓይለቶች ያለማቋረጥ ወደታች ዝቅ በማድረግ ጉዟቸውን ማስተካከል ይኖርባቸዋል። አለበለዚያ የንግድ አውሮፕላን አማካኝ በሰዓት 500 ማየል እየበረረ በትንሽ ሰዓቶች ውስጥ ብቻ ራሳቸውን ‹‹በውጨኛው ህዋ›› ጠፍተው ያገኛሉ። ፈፅሞ ይህ ያልተከሰተበት ምክንያት እንዲሁም አርቲፊሻሉ አድማስ ፓይለቱ ከፈለገው ከፍታ ጋር ትይዩ መስመር መሆኑ እና በቋሚነት ወደታች የሚደረግ ማስተካከያ አለማስፈለጉ፤ ምድር ኳስ እንዳልሆነች ነው የሚያረጋግጠው።

162) ሁሉም የናሳና የሌሎች ህዋ ምርምር ተቋም ሮኬት ጉዞ ቀጥተኛ ሁኖ ወደላይ ሂዶ አያውቅም፤ ሁሉም ሮኬቶች ፓራቦላ የመሰለ መጠምዘዝን ይፈጥራሉ፤ እና ተመልሶ ወደ ምድር መውደቅ መጀመሩ የማይቀር ነው። ‹‹ስኬታማ›› ተደርገው የሚገለጹት ሮኬቶች የተወሰኑት እነዚህ ያልፈነዱት ወይም በቅርቡ ተመልሰው ያልወደቁት ግን ተመልሰው በተከለከሉ የውሃ ስፍራዎች ሲወድቁ ከተመልካች እይታ ውጭ የሆኑት ናቸው። ሮኬት ወይም ሌላ ነገር በቀላሉ ወደላይ ሂዶ ከዛ በድንገት በህዋ ላይ ‹‹በነጻነት መንሳፈፍ›› የሚጀምርበት አስማታዊ ከፍታ የለም። ይሄ ሁሉ ልብወለድ ነው፤ በገመዶች፣ በአረንጓዴ እስክሪኖች፣ በጨለማ ገንዳዎች፣ በአንዳንድ ፐርም የተቀቡ ፀጉሮች እና በዜሮጅ አውሮፕላኖች የተፈጠረ ማስመሰል ነው።

163) ናሳ እና ሌሎች የህዋ ምርምር ተቋሞች የ‹‹ውጭኛው ህዋ›› ቀረጻቸው በተደጋጋሚ ጊዜ የአየር አረፋዎች ሲፈጠሩ እና እየተንሳፈፉ ሲወጡ የሚያሳዩ ቪዲዮዎች መሆናቸው ተይዘባቸዋል። ጠፈርተኞችም የውሃ መዋኛ scuba-space-gear እንደተጠቀሙና ለመንቀሳቀስ እግራቸውን እንዳማቱ ማየት ተችሏል። እንደውም እነርሱ በሚሉት የህዋ ላይ እግር ጉዞ/space-walk፤ ጠፈርተኛ ለካ ፓርሚታኖ ውሃ ሄልሜቱን እየሞላ በመሄዱ ለትንሽ ህይወቱን አጥቶ ነበር። ልክ እንደ ናሳ ‹‹Neutral Buoyancy Lab›› ጠፈርተኞች ‹‹የህዋ ላይ እግር ጉዞ››የሚሰለጥኑት በውሃ ውስጥ እንደሆነ የታወቀ ነው፤ ግን ከ ‹‹ህዋ አረፋዎች›› እና ከሌሎች ለህዝብ ከቀረቡ የተሳሳቱ ‹‹space-walk›› ቀረጻዎቻቸው ግልፅ የሚሆነው ሀሰተኛነታቸው እና በውሃ ውስጥ መቀረጻቸው ነው።

164) ከ ‹‹ዓለምአቀፉ የህዋ ምርምር ጣቢያ›› የብዙ ውስጣዊ ቪዲዮዎች ምርመራ፤ የካሜራ ማታለያ ዘዴዎች ልክ እንደ አረንጓዴ እስክሪን፣ መንጠልጠያ ትጥቆች እና እንዲሁም ብዛት ፐርም የተቀባ ፀጉር፤ እነዚህን ሁሉ መጠቀም ግራቪቲ የሌለበትን አይነት ምስል እንደሚያስገኝ ያሳየ ነበር። ከ‹‹ህዋ ጣቢያቸው›› ግራቪቲ በሌለበት ስፍራ ያሉ ይመስል ጠፈርተኞች እየተንሳፈፉ የሚያሳየው ቀረጻ፤ ከ ‹‹vomit comet›› ዜሮጅ አውሮፕላን ቀረጻ ጋር ልዩነት የለውም። ፓራቦላ በሆነ ስልት በመብረር የዚህን የዜሮጅ አየር የመንሳፈፍ ውጤት እረዘም ላለ የማያቋርጥ ቪድዮ በተደጋጋሚ ጊዜ ማድረግ እና አንድ ላይ ማቀናበር ይቻላል፤ ናሳ ቀላል ገመዶችን እና የአረንጓዴ እስክሪን ቴክኖሎጅን በመጠቀም ተይዟል።



165) አንድ ሰው ዓለምአቀፉ የህዋ ጣቢያ(Iss) በአናት ላይ ሲያልፍ መመልከት እና መኖሩን ማረጋገጥ ይችላል ብሎ ናሳ ይናገራል። ግን ‹‹Iss››ን ስንመረምረው በካሜራዎች አቅርቦ በማየትም የሆነ ሀሎግራም/ድሮውን ነገር እንጅ አካላዊ የሚንሳፈፍ የህዋ ላይ ቁስ እንዳልሆነ ነው የምናየው፤ ከዚህ የጽሑፍ ማስረጃየም ላይ እንደምታዩት ‹‹Iss›› የተባለው የፈጠራ ወሬ ሲቀርብ እና ሲርቅ በማይታመን እና በሚገርም ሁኔታ ቅርጽ እና

ከስር ይቀይራል። አቅርበን እስከምናጣራው ድረስ ህብረ ቀለማዊ ቀስተ ደመና ምስልን እያሳየ በጣም ልክ የድሮ ቴሌቪዥን ሲከፈት እና ሲዘጋ እንደሚያሳየው ምስል ይመስላል።



166) ‹‹በህዋ ላይ ቋሚ የሆኑ የመገናኛ ሳተላይቶች›› የሚለው ሀሳብ መጀመሪያ የተፈጠረው በፍሪማሶናዊው የልብወለድ ጽሐፊ አርተር ሲ. ክላርክ ነበር። እነርሱ እንደሚሉት ከአስር አመታት በኋላ የሳይንስ እውነታ ሁኖ ቁጭ አለ። ከዚህ በፊት ግን ራዲዮ ቴሌቪዥን እና ልክ እንደ LORAN እና DECCA ያሉ አቅጣጫ ጠቋሚ ስርአቶች ቀድሞውኑ በሚገባ የተሰሩ እና መሰረታቸውን ምድር ላይ ባደረጉ ቴክኖሎጅዎች ብቻ በደንብ ይሰሩ የነበሩ ተቋም ናቸው። በአሁኑ ግዜ ትልልቅ ፋየር አብቲክ ገመዶች በውቅያኖስ ውስጥ ኢንተርኔቱን ያገናኛሉ። የገዘፉ የኔትወርክ ማማዎች የጂፒኤስ ሲግናል ይቀባበላሉ። አይናስፈራዊው ማስፋፊያ የአራዲዮንን ሞገድ ያለምንም ልብወለዳዊ ጥሩ የተባለ ‹‹ሳተላይት›› እገዛ እየነጠረ በሁሉም እንዲሰራጭ ያደርጋል።

167) እንደሚባለው ከሆነ ሳተላይቶች በቴርሞስፌር ዙሪያ እየተንሳፈፉ ይገኛሉ። የሙቀት መጠኑ ወደላይ 4,530 ድግሪ ፋራናይት ነው ብለው ያስቀምጣሉ። ለሳተላይቶች ጥቅም ላይ የሚውለው እንደ አልሙንየም ወርቅ እና ታይታኒየም ያሉት የመቅለጫ መጠናቸው ግን በተከታታይ 1,221፣ 1,948 እና 3,034 ዲግሪ ነው። ሁሉም መቋቋም ከሚችሉት በታች ዝቅተኛ ናቸው።

168) ‹‹ሳተላይት›› ተብሎ የሚጠራው፤ በካዛኪስታን በጣም ውስን በሆኑ የኔትወርክ ማማዎች ምክንያት ስልኮች የመቀበል ችግር እንደነበረባቸው ነው የታወቀው። ምድር ኪስ ከነበረች እና 20,000+ ሳተላይቶች በዙሪያዋ ካሉ፤ በማንኛውም ገጠራማ የሀገር ክፍሎች በመደበኛነት እንደዚህ አይነት የኔትወርክ መጥፋት ሊፈጠር አይገባም።

169) ‹‹ሳተላይት›› ተብሎ የሚጠራው፤ የቲቪ ዲሾች በብዛት ሁልጊዜ በ45 ድግሪ ማዕዘን ተቀምጠው አቅጣጫቸው ወደሚቀርበው መሰረቱ መሬት ላይ ከሆነው ደጋሚ ማማ ጋር ይሆናል። የቲቪ አንቴናዎች በእውነት መልክቶቹን ከ100+ ማየል ከህዋ ሳታላይቶች እየተቀበሉ ቢሆን ኑሮ፤ ብዙ የቲቪ ዲሾች ከሞላ ጎደል ቀጥታ ወደ ሰማይ መጠቆም ነበረባቸው። ‹‹ሳተላይት›› ዲሾች በጭራሽ ቀጥታ ወደላይ የማይጠቀሙበት እና በብዛት ሁሉም በ45 ዲግሪ ዘዋ የሚቀመጡበት ምክንያት፤ መልክት የሚቀበሉት ከመሬት ላይ ከቆሙት ማማዎች እንጅ ‹‹ከውጭ ህዋ ሳታላይቶች›› እንዳልሆነ ነው የሚያሳየው።

170) ሰዎች እንዲሁ በአይናቸው ብቻ ሳተላይቶችን ማየት እንደቻሉ አድርገው ይናገራሉ፤ ነገር ግን ይሄ ሞኝነት ነው፤ እነዚህ ከባስ ያነሱና እንደሚሉት ወደ 100+ ማየል ሲርቁ በዚህን ያህል እርቀት እንደዚህ ያነሰን ነገር ማየት የማይቻል ነው። ማንም የሳተላይትን ቅርጽ ማየት እንደቻለ ሊናገር አይችልም። ነገር ግን የሚያልፍ የሚንቀሳቀስ ብርሃን ማየቱን ሊያብራራ ይችላል፤ እንዲሁ ከአውሮፕላን ጀምሮ እስከ ድሮውን እና ተወርዋሪ ኮከብ ሊሆን ይችላል፡ ወይም ሌላ ምንነቱ ያልታወቀ በራሪ አካል ይሆናል።

171) ናሳ እንደሚለው፡- ወደላይ 20,000 ሳተላይቶች በምድር የላይኛው ህዋ ዙሪያ እየተንሳፈፉ ይገኛሉ፤ ለእኛ የራዲዮ፣ ቴሌቪዥን፣ ጅፒኤስ መረጃ እየላኩልን እና ፕላኔቷን ፎቶግራፍ እያነሱ። እነዚህ ሁሉም የሳተላይት ፎቶ የሚባሉት ግን ‹‹በፎቶሾፕ የተቀናበሩ መሆናቸው›› የታመነባቸው ምስሎች ናቸው። ከሳተላይቶች ‹‹ሪባን ቁራጭ ምስሎች›› እንደሚቀበሉና የተቀናጀ የምድር ምስልን ለመፍጠር ከአንድ ላይ መገጣጠም እንዳለበት ይናገራሉ፤ ሁሉም በግልጽ ኮምፒውተር የፈጠረው ምስሎች ናቸው፤ ፎቶግራፍ አይደሉም። በእውነት ምድር ኪስ

ሁና 20,000 ሳተላይቶች እየዞሯት ቢሆን ኑሮ፤ ካሜራን ለማስቀመጥ እና ትክክለኛ ፎቶዎችን ለማንሳት በጣም ቀላል ጉዳይ ይሆን ነበር፡፡ ናሳ ከሚለቃቸው ‹‹ሪባን የተቀናበሩ የኮምፒውተር ፈጠራ ምስሎች›› ውስጥ አንድም ትክክለኛ የሳተላይት ፎቶግራፍ አለመኖር በተጨማሪነት የሚያረጋግጠው ለእኛ እውነቱ እንዳልተነገረን ነው፡፡

172) በሰማዩ ላይ አንዱን ዳመና መርጠን ለተወሰኑ ደቂቃዎች ብንመለከት ሁለት ነገሮች ይከሰታሉ፤ ዳመናው ይንቀሳቀሳል እና ቀስበቀስ ቅርጹን እየቀየረ ይሄዳል፡፡ በናሳ ለህዝብ በሚለቀቁ የምትሽከረከር ኳስ ምድር ቀረጻዎች፤ ልክ እንደ ‹‹ጋለሊዮ›› የጊዜ ዑደት የሚያሳይ ቪዲዮ ላይ ግን ዳመናዎች ለ24+ ሰዓታት በቋሚነት ምንም ሳይንቀሳቀሱ ወይም ምንም አይነት እንኳን የቅርጽ ለውጥ ሳያሳዩ ምድር ትሽከረከራለች፤ ይሄ ሙሉበሙሉ የማይቻል ነገር ነው፡፡ ናሳ ሀሰተኛ በኮምፒውተር የተፈጠሩ(CGI) ቪዲዮዎች እንደሚያዘጋጅም ሌላ ማረጋገጫ ነው፡፡ እንደገና ምድር የምትሽከረከር ኳስ እንዳልሆነችም ተጨማሪ ማስረጃ ነው፡፡

173) ናሳ የኳስ ምድር ፎቶግራፎች ናቸው የተባሉ የተወሰኑ ምስሎች አሉት፤ ከእነዚህም አንዳንድ በትክክል ተመሳሳይ ቅጅ ያላቸው የደመና ቅርጾች መኖራቸው ነው የሚታየው፤ በአንድ ፎቶ ላይ በትክክለኛነት ተመሳሳይ ቅርጽ ያላቸው ሁለት ወይም ሶስት ዳመናዎችን የማግኘት አጋጣሚ፤ በእድለኛነት የሁለት ወይም የሶስት ሰዎችን የእጅ አሻራ አንድአይነት ሁኖ እንደማግኘት ነው፡፡ በእርግጥም ዳመናዎቹ በኮምፒውተር ፕሮግራም ኮፒ እና ፔስት እንደተደረጉ ብርቱ ማስረጃ ነው፡፡ እንደዚሁ ኳስ ቅርጽን የያዘች ምድር የሚያሳዩ ፎቶዎች ሀሰተኛ ናቸው፡፡



174) የናሳ ግራፊክስ አርቲስቶች ፊቶችን፣ ድራጎኖችን እና እንዲሁም ‹‹SEX›› የሚለውን ቃል እንኳን በተለያዩ የኳስ ምድር ፎቶዎቻቸው የዳመናዎች ቅርጽ ላይ አስቀምጠዋል፤ የእነርሱ የቅርብ ጊዜ የ2015 ፕሉቶ ፎቶ እንኳን በግልጽ የዲዚኒው ‹‹ፕሉቶ›› ውሻ መደብ ነው የተለጠፈው፡፡ እንደዚህ አይነቱ የጎላ ማታለል ባላስተዋለው ህዝብ ዘንድ ሳይነቃ ቢቀርም፤ ለናሳ ህገወጥነት እና ለእነርሱ የሚሸከረከር ኳስ ፕላኔት አፈታሪክነት ግን ተጨማሪ ማስረጃ ሁኖ ይቀርባል፡፡

175) በፎቶ ባለሙያ ተንታኞች በአንዳንድ የናሳ ኳስ ምድር ምስሎች ምርመራ፤ በኮምፒውተር እንደተዘጋጁ የማያስክድ ማረጋገጫ ተገኝቷል፡፡ ለምሳሌ የምድር ፎቶ ከጨረቃ ላይ ነው የተነሳው በተባለው ላይ የብራይትነስ እና የኮንትራስት ደረጃውን በማስተካከል በምድር ዙሪያ ከጀርባ በተገኘው የአራት ማዕዘን ቅርጽ ማስረጃነት ከሌላ ቦታ ኮፒ ፔስት እንደተደረገ ነው የተረጋገጠው፡፡ እውነት እነርሱ ጨረቃ ላይ ሁነው ቢሆን ኑሮ እና በእውነት ምድር ኳስ ብትሆን፤ እንደዚህ አይነት ፎቶዎችን መዋሸት ባላስፈለገ ነበር፡፡

176) የናሳን ኳስ ምድር ፎቶዎች አንዱን ከአንዱ ስናወዳድር፤ የመሬቱ ቀለማቶች/የውቅያኖሱ እና የአህጉሮቹ አንጻራዊ መጠን በቋሚነትና በጣም በከፍተኛ ሁኔታ አንዱ ከአንዱ ይለያያል፡፡ ከዚህም በላይ በማንኛውም ምክንያታዊ ጥርጣሬ ፎቶዎቹ ሁሉ ሀሰተኛ እንደሆኑ ነው የምናረጋግጠው፡፡

177) ‹‹A Funny Thing Happened on the Way to the Moon›› በሚለው ዶክመንታሪ ላይ ከመደበኛ የናሳ ቀረጻዎች ሾልኮ የወጣውን ቪድዮ መመልከት ትችላላችሁ፤ የአፖሎ 11 ጠፈርተኞች በገ አልደርን፣ ኒል አርምስትሮንግ እና ማይክል ኮሊንስ ለአንድ ሰዓት ያህል ብርሃን አሳላፊ ነገሮችን በመጠቀም ሀሰተኛ የክቧ ምድር ቀረጻን ለማምጣት ሲጥሩ ያሳያል። እንዴት በጥሩ ሁኔታ አስመስለው መቅረጽ እንዳለባቸው መቆጣጠሪያው ሂውስተን ላይ በሆነው የድምጽ መገናኛ ይነጋገሩ ነበር፤ እና አንድ ሰው የሚፈለገውን ውጤት ለማግኘት እንዴት ካሜራውን መቆጣጠር እንዳለባቸው ይመክራቸው ነበር፤ በመጀመሪያ ወደታች ክብ ቅርጽ ከሚያሳየው መስኮት እነርሱ ከብዙ ጫማ ከፍታ እርቀት ላይ ካሜራው የሚያየው ብለው ካለመብት በስተቀር ሌላውን በሙሉ አጨለመ፤ ይሄ ኪስ ቅርጽ ያላት ምድር ዙሪያዋን በህዋ ጨለማነት ተከባ የሚመስል እይታን ፈጠረ፤ በእርግጥ በቀላሉ በእነርሱ ክፍል ውስጥ ያለ ክብ መስኮት ሁኖ ሳለ፤ ኒል አርምስትሮንግ ይህ ቦታ ከምድር 130,000 ማየል እርቀት ላይ ነው ይላል። ወደ ጨረቃ ግማሽ መንገድ ላይ ማለት ነው፤ የሚገርመው ግን፤ የካሜራ ማጭበርበሮች ሲያልቁ ተመልካቾች ለራሳቸው ጠፈርተኞቹ ለተወሰነ ደርዘን ማየሎች እንኳ ከምድር ገጽ እንዳልራቁ ማየት ይችላሉ።



178) ሰዎች የጎግል ኧርዝን ክባለ ትልቅ ከፍታ አየር በተነሱ ፎቶዎች እና እንዲሁ የጎዳና መኪና ላይ ካሜራዎች በተነሱ ፎቶዎች አንድላይ ተቀናብሮ በኮምፒውተር በተዘጋጀ የኪስ ምድር ሞዴል(CGI) ላይ የተለጠፈ መሆኑን ሳያስተውሉ፤ ጎግል ኧርዝም እኮ የምድርን ኪስ ሞዴልነት ማረጋገጫ መሆን ይችላል ይላሉ፤ እንዲሁ ተመሳሳይ ነገር በቀላሉ በአራት ማዕዘን ቅርጽ ምድር ላይ ወይም በሌላ ምንም አይነት ሞዴል ላይ መደረግ ይችላል። ስለዚህ ይሄ ለምድር ድቡልቡልነት እንደ ማረጋገጫ ሁኖ ሊወሰድ አይችልም።

179) ምድር ወደ ምስራቃዊ አቅጣጫ ያለማቋረጥ በሰዓት 1000 ማየል እየተሽከረከረች ከሆነ፤ የአውሮፕላኖች በረራ ወደ ምስራቃዊ አቅጣጫ እና ወደ ምዕራባዊ አቅጣጫ የሚደረግ ጉዞ የሚወስደው ጊዜ በጎላ ሁኔታ መለያየት ነበረበት። በአማካኝ የንግድ አውሮፕላን በሰዓት 500 ማየል የሚጓዝ ከሆነ፤ ከዚህም የተነሳ ወደ ምዕራብ ምድር ወገብ የሚደረጉ በረራዎች ወደ ምስራቅ ተመልሰው ሲበሩ ካላቸው ፍጥነት ይልቅ ወደ ሶስት እጥፍ ፈጥነው መድረስ ይችላሉ ማለት ነው። በእውነታው ግን ወደ ምስራቅ/ምዕራብ በረራዎች የሚወስዱት ጊዜ ሁልጊዜ የጥቂት ደቂቃዎች ልዩነት ነው፤ እና በሰዓት 1000 ማየል በምትሽከረከር ኪስ ምድር ሊፈጠር ከሚችለው ነገር ጋር ምንም ነገር ሊቃረብ አይችልም።

180) የሚሽከረከረው ኪስ ሞዴል፤ ምድር እና የአየር ንብረቱ በአንድ ላይ በመሀል ኬክሮስ አካባቢ በአቅራቡ በሰዓት ወደ 500 ማየል እየተንቀሳቀሱ እንዲሆን ያዛል፤ ከ LA ወደ NYC በረራ በአማካኝ የንግድ አውሮፕላን ወደ ምስራቅ ከሚባለው የምድር እሽክርክሪት ጋር በሰዓት 500 ማየል እየተጓዘ 5.5 ሰዓት ይወስዳል፤ ስለዚህ የመመለሱ የምዕራብ በረራ 2.75 ሰዓቶች ብቻ መውሰድ ነበረበት። በእውነቱ ግን በአማካኝ ከNYC ወደ LA የሚደረግ በረራ 6 ሰዓቶችን ይወስዳል። የበረራ ጊዜው ሙሉበሙሉ ከሚሽከረከረው ኪስ ሞዴል ጋር የሚጻረር/የማይገናኝ ነው።

181) ከሚባለው ኪስ ምድር እሽክርክሪት አቅጣጫ ጋር ምስራቃዊ በረራ ከቶኪዮ ወደ LA በአማካኝ 10.5 ሰዓቶች ይወስዳል፤ ስለዚህ ከሚባለው እሽክርክሪት በተቃራኒ የመመለሱ ምዕራባዊ በረራ በአማካኝ 5.25 ሰዓቶች ነው መውሰድ የነበረበት፤ በሚታየው እውነት ግን በአማካኝ 11.5 ሰዓቶችን ይወስዳል። ሌላ ሙሉበሙሉ ከሚሽከረከረው ኪስ ሞዴል ጋር የሚጻረር የበራራ ሰዓት ነው።

182) ከሚባለው ኪስ ምድር እሽክርክሪት አቅጣጫ ጋር ምስራቃዊ በረራ ከNY ወደ ለንደን በአማካኝ 7 ሰዓቶች ይወስዳል፤ ስለዚህ ከሚባለው እሽክርክሪት በተቃራኒ የመመለሱ ምዕራባዊ በረራ በአማካኝ 3.5 ሰዓቶች ብቻ መውሰድ ነበረበት፤ በሚታየው እውነት ግን በአማካኝ 7.5 ሰዓቶች ይወስዳል። የበረራ ሰዓቱ ሙሉበሙሉ ከሚሽከረከረው ኪስ ሞዴል ጋር ይጻረራል።

183) ምስራቃዊ በረራ ከችጋጎ ወደ ቦስተን ከሚባለው ኪስ ምድር እሽክርክሪት ጋር በአማካኝ 2.25 ሰዓቶች ይወስዳል፤ ስለዚህ የመመለሱ ምዕራባዊ በረራ ከሚባለው እሽክርክሪት በተቃራኒ በአማካኝ ከአንድ ሰዓት በላይ ብቻ መውሰድ ነበረበት፤ በእውነታው ግን በአማካኝ 2.75 ሰዓቶች ይወስዳል። አሁንም በድጋሚ ከሚሽከረከረው ኪስ ሞዴል ጋር ሙሉበሙሉ ይጻረራል።

184) ምስራቃዊ በረራ ከፓሪስ ወደ ሮም ከሚባለው ኪስ ምድር እሽክርክሪት ጋር በአማኝ 2 ሰዓቶች ይወስዳል፤ በዚህም ከእሽክርክሪቱ በተቃራኒ የመመለሱ ምዕራባዊ በረራ በአማካኝ 1 ሰዓት መውሰድ ነበረበት፤ በእውነቱ ግን አማካኙ የበረራ ጊዜ 2 ሰዓት ከ10 ደቂቃዎች ነው። የበረራ ሰዓቱ ከሚሽከረከረው ኪስ ሞዴል ጋር ሙሉበሙሉ ይቃረናል።

185) ምድርና አየር ንብረቱ በአንድ ላይ በትክክል ወጥ በሆነ ፍጥነት እንደሚሽከረከሩ ተነግሮናል፡፡ ማንም ግን በታሪክ ይሄንን አይቶም፣ ሰምቶም፣ ለክቶም አያውቅም፡፡ የሚባለው በሰዓት የ1000 ማየል እንቅስቃሴ ብዙ ጊዜ በወጥ ፍጥነት ከሚጓዝ መኪና ጋር ይነጻጸራል፤ እንቅስቃሴው የሚሰማን መኪናው ፍጥነት ሲጨምር ወይንም ሲቀንስ ነው ይላሉ፤ በእውነታው ግን አይናችን ተጨፍኖ እንኳን፣ መስኮት ተዘግቶ በለሰለሰ አስፓልት ላይ በሰዓት ወጥ በሆነ የ50 ማየል ጉዞ በቅንጦት መኪና ውስጥ ሁነንም እንቅስቃሴው በስነስርዓት ይሰማናል፡፡ ከዚህ ፍጥነት 20 እጥፍ የሚሆነው የምድር በሰዓት 1000 ማየል ምናባዊ እሽክርክሪት በእርግጠኝነት በቀላሉ በሁሉም ዘንድ የሚታይ፣ የሚሰማ፣ የሚስተዋል ይሆን ነበር፡፡

186) ለጉዞ ህመም ተጋላጭ የሆኑ ሰዎች በትንሿ የአሳንሰር ወይም የባቡር ጉዞ እንቅስቃሴ እንኳን ልዩ ጭንቀት እና አካላዊ መጎሳቆል ይሰማቸዋል፤ ይህም ማለት በሰዓት 1000 ማየል ወጥ የሆነ የሚባለው የምድር እሽክርክሪት በእንደዚህ አይነት ሰዎች ላይ ምንም ተጽኖ የለውም ማለት ነው፡፡ ነገር ግን ሌላ ተጨማሪ ወጥ በሰዓት 50 ማየል የመኪና ፍጥነት ሲደመር ሆዳቸው መታወክ ይጀምራል፤ በሰዓት የ1000 ማየሉ ላይ የጉዞ ህመም የሚለው ሀሳብ በየትም ቦታ በማንም ላይ እንደማይሆን ግልጽ ነው፡፡ ድንገት ግን በሰዓት 1050 ማየል ሁኖ ሲመጣ ነው የሚለው ሞኝነት ነው፡፡ እና ከዚህም የምንረዳው ምንም ቢሆን ምድር እንቅስቃሴ ላይ እንዳልሆነች ነው፡፡

187) ሁለተኛው የቴርሞዳይናሚክስ ህግ ወይም በሌላ አጠራር የኢንትሮፒ ህግ በመባል የሚታወቀው፤ መሰረታዊው የሰበቃ/መቋቋም መመሪያዎች በሚለው ውስጥ፤ የምድር ወጥነት ያለው የሚሽከረከር ኳስ መሆን የማይቻል መሆኑን ይገልጻል፤ በጊዜ ሂደት ውስጥ የምትሽከረከረው ኳስ ምድር ሊለካ የሚችል መጠን ያለው የሚጎትት ኃይልን ትጋፈጣለች፡ በቋሚነት የእሽክርክሪቷን ፍጥነት እየቀነሰውና በቀን ውስጥ ያለውን የሰዓት መጠን እያረዘመው ይሄዳል፡፡ ትንሽም እንኳን የዚህ አይነቱ ለውጥ በዓለም ታሪኮች ውስጥ ተመዝግቦ ባለመታየቱ፤ ምድር ለአንድ ኢንች እንኳን ተጉዛለች ብሎ መገመት ዘበት ነው፡፡



188) በአመታት ውስጥ ናሳ የምድርን ቅርጽ በተመለከተ ሁለት ጊዜ ታሪካቸውን ቀይረዋል፡፡ በመጀመሪያ ምድር ትክክለኛ ሉል ነች ብለው አስቀምጠው ነበር፤ በኋላ ላይ ወደ ‹‹ሞላላ ክብ›› ዋልታዎቹ አካባቢ ዘርጋ ያለ በሚል ተቀይሯል፤ ከዛም እንደገና እንደሚሉት የደቡቡ ንፍቀ ክበብ ጎላ ብሎ መውጣት ስለነበረበት ‹‹ሽክኒት ቅርጻማ›› ነው ብለው ቀይረውታል፡፡ ለናሳ ግን በሚያሳዝን ሁኔታ አንድም ከእነርሱ የሚለቀቅ ፎቶ ሞላላ ክቡን ወይም ሽክኒት ቅርጻማውን ምድር አያሳይም፡፡ ሁሉም የእነርሱ ፎቶዎች ከቃላቸው በተቃራኒ ሉላዊውን(በግልጽ ሀሰተኛውን(CGI)) ምድር ነው የሚያሳየው፡፡



189) መጽሐፍ ቅዱስ፣ ቁርአን፣ ስራይማድ ባሀጋቫታም እና ሌሎችም ብዙ ቅዱስ መጽሐፎች ከአጽናፈ ሰማይ በታች መሀል ላይ ያለ እና የማይንቀሳቀስ ዝርግ ምድር መኖሩን ነው የሚያስረዱትና የሚጠቁሙት፡፡ ለምሳሌ መጽሐፈ ዜና መዋዕል ቀዳማዊ 16:30 እና መዝሙረ ዳዊት 96:10 ሁለቱም ‹‹እርሱም ዓለምን እንዳይናወጥ አጽንቶታል›› ሲሉ ይነበባሉ፤ እንዲሁም መዝሙረ ዳዊት 93:1 ‹‹ዓለምን እንዳትናወጥ አጸናት›› ይላል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስም ምድር የምትሽከረከር ኳስ እንዳልሆነች መንፈሳዊ ማረጋገጫወችን እየሰጠ በተደጋጋሚ ጊዜ በዙሪያዋ ሰማይ ያላት ሳይሆን ከሁሉም አቅጣጫ ወደ ላይ በኩል ወደ ውጭ ተለጥጦ ከተዘረጋ ሰማይ ጋር ምድር እንደ ጠለል ወደውጭ የተዘረጋች ዓለም መሆኗን ነው የሚያሳውቀው፡፡





190) መሀከለኛ ቋሚ እና የማይንቀሳቀስ ዝርግ ምድር መኖሩን ነበር ሁሉም በታሪክ ውስጥ በዓለም ዙሪያ ያሉ ባህሎች የገለጹትና የጠቆሙት፤ ግብጻዊያን፣ ህንዳውያን፣ ማያዎች፣ ቻይናውያን፣ ትውልደ አሜሪካውያን እና ባጠቃላይ ሁሉም ጥንታዊ የምድር ስልጣኔዎች ምድርን መሀከለኛ ያደረገ የዝርግ ዓለም ኮስሞሎጅ ነበራቸው፤ ከፓይታጎረስ በፊት የሚሽከረከር ኳስ ምድር የሚል ሃሳብ አልነበረም፡፡ ከፓይታጎረስ በኋላ እንኳን እስከ 2000 አመታት ኮፐርኒከስ የተንቀሳቃሹን ዓለም ንድፈ ሃሳብ ማደስ እስኪጀምር የዚህ አይነት ሃሳብ አልነበረም፡፡

191) ከፓይታጎረስ እስከ ኮፐርኒከስ፣ ጋሊሊዮ እና ኒውተን እስከ ዘመኑ ጠፈርተኞች እንደ አልደርን፣ አርምስትሮግ፣ ኮሊንስ እና የናሳ ዳይሬክተር ሌላም እስከ ታላቁ ባለ 33 ዲግሪ ማዕረግ አዛዥ ሲ.ፍሬድ ክላይንቸት ድረስ፤ ሁሉም የምትሽከረከረው ኳስ ዓለም አፈታሪክ ዋና ጸንሳሽ አባቶች ፍሪማሱኖች ነበሩ፡፡ የዚህ ትልቅና

ጥንታዊ ሚስጥራዊ ማሕበር ብዙ አባላቶች እንዳሉት እስካሁን የመኖር እውነት፤ በአንድ ላይ ተባብረው በማሴር በግሀድ ‹‹ዓለምአቀፋዊ አብዮት›› ለማምጣት ነው ከሚለው ጋር ግጥምጥሞሽ ሊሆን ከሚያስችለው ዕድል በላይ ነው፤ ብዙ የተታለለ ትውልድን ለመፍጠርና ለመጠበቅ የተደራጀ የሴራ ተቋም ስለመኖሩ ማስረጃ ሁኖ ይቀርባል፡፡

192) ከአባባል ‹‹Terra Firma›› በዴቪድ ዋርድላው እስኮት ‹‹በዘመኑ ጠፈርተኞች የተማርነው የአጽናፈ ዓለሙ ስርዓት ሙሉበሙሉ መሰረቱን ያደረገው በቲወሪው ላይ ነው፤ ለእውነቱ ማጣቀሻ የሚሆን አንድም ትክክለኛ ማስረጃ ማግኘት ባልቻሉበት ቲወሪ፤ በሚሰጧቸው መላምቶች ላይ ሊመጣ የሚችለውን የተቃውሞ ጥያቄ ለመቀነስ ራሳቸውን በሴራው ዝምታ ውስጥ እንዲከቱ አድርጓቸዋል፡፡ የአረማዊውን ፈላስፋ የፓይታጎረስን ቲወሪ ያደሰው ራሱ ኮፐርኒከስ እና የእርሱ ትልቅ አጋፋሪ የሆነው ሰር አይዛክ ኒውተን የእነርሱ የሚገላበጥ የምድር ስርዓት ሊሆን የሚችል እድል ብቻ እንደሆነ እና በእውነታው ሊረጋገጥ እንደማይችል ተናዘዋል፡፡ የእነርሱ ተከታዮች ብቻ ናቸው ‹‹ትክክለኛ ሳይንስ›› በሚል ስም ያሸሞነሞኗት፡፡ አወ እንደነርሱ ከሆነ ይሄ ‹‹ከሁሉም ሳይንስ ይልቅ በጣም ትክክለኛው ነው››፡፡ ሁኖም ግን አንድ ለኢንግላንድ ንጉሳውያን የሆነ ጠፈርተኛ አንድ ጊዜ እንዲህ ብሎ ነበር ‹‹ስለ መላ ስርዓተ ፀሐዩ እንቅስቃሴ መናገር ችግሩ፡ እርግጠኛ ላለመሆኑ በጣም ምቹ ነጥቦችን ትቶ ማለፉ ነው፤ አንድም በዚህ ጉዳይ የሚረዳኝ ሰው ባገኝ በጣም ደስ ይለኛል፡፡›› እንዴት ያለ በጣም የሚያሳዝን የስራ ድርሻ ነው ‹‹ትክክለኛ ሳይንስ›› ተብሎ የሚኬደው እንደዚህ ሲሆን፡፡››



193) ማንም ህፃን ወይም ያልተዋሸ ሰው፤ በትክክለኛ አይምሯቸው ለራሳቸው በተሰጣቸው መሳሪያ፡ የራሳቸው በሆነ ምልከታ፤ ምንም ቢሆን ምድር የምትሽከረከር ኳስ እንደነበረችና በፀሐይ ዙሪያ እንደምትገላበጥ ሊደመድሙ ወይም ሊያስቡ አይችሉም፡፡ እንደዚህ አይነት ምናባዊ ንድፈ ሀሳብ በማንም ሰው የዕለት ልምምድ በየትም ቦታ ሊኖር አይችልም፡፡ ይሄንንም የተሳሳተ እምነት ለመጫን በጣም ግዙፍ መጠን ያለው የማያቋርጥ ፕሮፖጋንዳን ይጠይቃል ጠይቋልም፡፡



194) ከዴቪድ ዋርድላው እስኮት አባባል፤ ‹‹ህፃን እያለሁ ምድር ትልቅ ኳስነች በፀሐይ ዙሪያ በጣም ፈጣን በሆነ መጠን የምትሽከረከር ተብየ ስማር አስታውሳለሁ፡፡ ለመምህሬም በውቅያኖሶች ውስጥ ያሉት ውሃዎች አይወድቁም እንዴ የሚለውን ፍራቻየን ስገልጽለት፤ በኒውተን ትልቁ ግራቪታዊ ህግ ይህን ከማድረግ ተከልክለዋል ተብየ ነበር፤ ሁሉንም ነገር በትክክለኛ ቦታው እንዲቆይ ባደረገው ህግ ማለት ነው አለ፤ የኔም ፊት የተወሰነ የጥርጣሬ ምልክቶችን አሳይቶ መሆን አለበት ብየ እገምታለሁ፤ መምህሬ ወዲያውኑ እንዲህ ሲል አከለ፡- የዚህን ቀጥተኛ ማረጋገጫ ላሳይህ እችላለሁ፡ አንድ ሰው በውሃ የተሞላን ባልዲ አንጠልጥሎ በአናቱ ዙሪያ ያለምንም ጠብታ ማሽከርከር ይችላል፤ ስለዚህ ልክ እንደዚህ በተመሳሳይ ሁኔታ ውቅያኖሶቹ በፀሐይ ዙሪያ ያለምንም ጠብታ ተይዘው መዞር ይችላሉ፡፡ ማብራሪያው ያስፈለገው በግልጽ ችግሩን ለመፍታት ስለነበር ከዛ በኋላ በእርዕሱ ላይ ምንም ነገር አላልኩም፡፡ ከጊዜ በኋላ ግን ትልቅ ሁኘ ሳስበው፡ በተወሰነ ደረጃ እንኳን እንዲህ እንደሚከተለው ብየ መመለስ ነበረብኝ፡ ‹‹መምህር ባልዲ ሙሉ ውሃ በአናት ላይ ሲሽከረከር ብለህ የሰጠኸው ማብራሪያ እና ውቅያኖሶች በፀሐይ ዙሪያ ሲገላበጡ የሚለው በምንም አንግል ለጥያቄው መልስ ሁኖ መቅረብ አይችልም፤ ምክንያቱም በሁለቱም ጉዳዮች ውስጥ ያለው ውሃ ሙሉበሙሉ የተለያየ በሆነ አኳኋን ስር ነው የተቀመጠው፤ ተነጻጻሪ እንዲሆን ግን በሁለቱም ጉዳዮች መካከል ያሉ ሁኔታዎች ተመሳሳይ መሆን አለባቸው፡፡ እዚህ ላይ ግን እንደዛ አይደሉም፤ ባልዲው ጎድጓዳ እቃ ነው ውሃውን በውስጡ መያዝ የሚችል፤ እንደ አንተ አስተምህሮት ግን ምድር ወደ ውጭ ቀጣይነት ያለው መጠምዘዝ ያላት ኳስ ነች፤ ይህም ከተፈጥሮ ህግ ጋር የሚስማማው ውሃውን ይዞ ማቆየት የማይችል በመሆን ነው››

195) ጠፈርተኞች አስማታዊው የግራቪቲ ስበት እንደሆነ ውቅያኖሶቹን ሁሉ በኳሷ ምድር ላይ ተለጥፈው እንዲቀሩ ያደረገው ይናገራሉ፡ እነርሱ ...ምክንያቱም ምድር በጣም ግዙፍ በመሆኗ አየር ንብረቱን በጥብቅ በምትሽከረከር ኳስ ላይ ተለጥፈው እንዲቀሩ በማድረግ መያዝ የሚያስችል አስማታዊ ኃይልን መፍጠር ችላለች ብለው ያስባሉ፡፡ በሚያሳዝን ሁኔታ ግን ከፕላኔታዊ መመዘኛ ባነሰ አንድም የዚህን ተግባራዊ ምሳሌ ማቅረብ አልተቻለም፡፡ ለምሳሌ ውሃ የተነከረች የሜዳ ቴንስ ኳስ በትክክል ከሚባለው ኳስ ምድር ተቃራኒ የሆነ ጸባይን ታሳያለች፡ እየበረረ 360 ዲግሪ የሚዞር ውሃ ውጤትን እየሰጠች እላይዋላይ ፈሶ የነበረ ማንኛውም ውሃ ወደጎን ይረግፋል ...ልክ ውሻ ከታጠበ በኋላ እንደሚያርገፈግፈው፡፡ ጠፈርተኞቹ እርጥቡ የቴንስ ኳስ ምሳሌ እነርሱ ከሚሉት ኳስ ምድር ተቃራኒ የሆነ ውጤትን እንደሚያሳይ ያምናሉ፤ ግን አንድ የሆነ መጠኑ ያልታወቀ ትልቅ

ግዝፈት ኑሯት ቢሆን፤ ትአምራዊዉ የግራቪቲ የማጣበቅ ጸባይ የምትሽከረከረው እርጥብ የቴንስ ኳስ ምድር ‹‹በስበቷ ተይዞ የነበረ›› ውሃ ጠብታዎች በሙሉ በገጹ ላይ እንዲለጠፉ በመፍቀድ ድንገት ስራውን ይጀምራል ብለው ያስባሉ፡፡ እንደዚህ አይነት ያልተረጋገጠ ቲወሪ ከሁሉም ሙከራዎች፣ ልምምዶች እና የስሜት ህዋሶች ጋር የሚቃረን ሁኖ ሲመጣ ጊዜው መሆን ያለበት ቲወሪውን የመጣል ነው፡፡



196) ከማርሻል ሀል አባባል ‹‹በእርግጥም በአጭሩ ፀሐይ ጨረቃና ከዋክብት በትክክል በታሪክ ውስጥ ሁሉም ሰው ሲያደርጉ ያያቸውን ነገር ነው በማድረግ ላይ ያሉት፡፡ አይናችን የሚነግረንን ነገር አናምንም ምክንያቱም የተማርነው ሀሰተኛ ስርዓት ሁኖ በሙከራ ወይም በምልከታ ያልተረጋገጠን ነገር እንድናምን የሚጠይቅ በመሆኑ፤ ያ ሀሰተኛ የሆነ ስርዓት ምድር በ‹‹ዛቢያ›› እንደምትዞር በየ24 ሰዓቱ ምድር ወገብ ላይ በሰዓት የ1000 ማየል ፍጥነት እንዳላት እንድናምን ይጠይቀናል፤ ማንም ግን የዚህ አይነቱ እንቅስቃሴ በጭራሽ በጭራሽ ታይቶት ወይም ተሰምቶት አያውቅም(እንዲሁ ምድር በዛቢያዋ ሁና በፀሐይ ዙሪያ በሰዓት የ67,000 ማየል ጉዞ ወይም በጋላክሲው ዙሪያ በሰዓት የ500,000 ማየል ፍጥነቷ ወይም በዚሁ ውስጥ በሰዓት 670,000,000 ማየል ከ‹‹ቢግባንግ›› ማፈግፈግ የሚባለው ታይቶን ወይም ተሰምቶን አያውቅም፡፡) አስታውሱ ምድር እንደምትንቀሳቀስ ያሳየ ምንም አይነት ኢክስፐርመንት የለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሳይንሳዊ እውነታ ተብሎ የተማርነው የእሽክርክሪቷ ፍጥነት፤ አንዱ ከምድር ወገብ ወደ ሰሜን ወይም ወደ ደቡብ ሲጓዝ በየኢንቹ ወይም በየማየሉ መቀነስ ይገባው ነበር፤ ስለዚህም በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ልክ እንደዚህ በትክክለኛነት ከአየር ላይ በቦምብ ማጥቃት መቻል (ወደታች ችምኒ ላይ ከ25,000 ጫማ ከፍታ አየሩ በትልቅ ፍጥነት በየትም አቅጣጫ እየበረረ ታች ላይ የሚፈለገውን ሀገር ማጥቃት መቻል) በብዙ መቶ ማየሎች በምትንቀሳቀስ እና በቋሚነት በየኬክሮሱ በሚለያይ ፍጥነት በምትጓዝ ምድር ላይ ሲሰላ፤ እንደዚህ አይነቱ ነገሮች የማይቻሉ ይሆን እንደነበር ቀላልና ግልጽ ጉዳይ ነው፡፡››

197) አንዳንድ ሰዎች ለእንደዚህ አይነት ትልቅ ደረጃ ማታለል ምንም አመክኒዮ አይኖርም፤ እና ዝርግ ወይም ኳስ መሆኗ ምንም ለውጥ አያመጣም ብለው ይናገራሉ፡፡ እነዚህ ማሱኖች ምድራችንን እንቅስቃሴ ከሌለው ማዕከላዊ አጽናፈ ዓለም በማስወጣት፤ እኛን በአካልም በስነ ልቦናም ከታላቅ ጠቃሚ ስፍራ አስወግደው ወደ አንድ ሙሉበሙሉ አህዛብ የሆነ ግድየለሽ ፍጥረትነት ቀይረዉናል፡፡ ምድር የአጽናፈ ዓለሙ ማዕከላዊ ከሆነች ፈጣሪ፣ ፍጥረት የሚለው ሃሳብ እና ለሰው ልጅ የመኖሩ ምክንያት ግልጽና የሚመሳከር እጹብ ድንቅ ጉዳይ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ምድር ከቢሊየን ፕላኔቶች ውስጥ አንዷ ከሆነች እና በቢሊየን ጋላክሲዎች ውስጥ በቢሊየን ከዋክብቶች ዙሪያ የምትጓዝ ከሆነ፤ ፈጣሪ፣ ፍጥረት የሚለው ሃሳብና ለምድር እና የሰው ልጅ መኖር ልዩ ምክንያት መኖሩ፡ በትልቁ የሚያጠራጥር ሁኖ ይቀርባል፡፡ በስውር ወደ እነርሱ ሳይንሳዊ በቁስ አካል አማኝ ፀሐይ አምልኮ ውስጥ አስተምረው ከተውን በማንኛውም ከቁሱ ባሻገር ያለንን እምነታችንን እናጣለን ማለት ብቻ ሳይሆን፤ ከዚህም በከፋ በቁሳዊነት ፍጹም እምነትን እናገኛለን፤ ወጩን ብቻ የምናስብ ግዑዛን፣ ስልጣን ፈላጊዎች፣ እራስወዳዶች፣ ደስታን ፈላጊዎች እና ሸማቾች ብቻ እንሆናለን፡፡ ፈጣሪ ባይኖርና ሁሉም ሰው ድንገተኛ ቢሆን ኑሮ፤ ሁሉም የሚያስጨንቀው ጉዳይ ለእኔ ለእኔ ለእኔ ማለት ብቻ ይሆናል፡፡ የፈጣሪን እናት ማዶናን(ማለትም፡ የቅድስት ድንግል ማርያምን ስም ከጣሊያንኛው) ቀይረው በቁሳዊዉ ዓለም ውስጥ የምትኖር ቁሳዊ ሴት አስመስለዋል፤ የእነርሱ ሐብታምና ታላቅ ተጽዕኖ ያለው ኮርፖሬሽን ከሚያንጸባርቅ የፀሐይ አምልኮ አርማቸው ጋር ጣዎቶችን እንድናመልክ ይሸጥልናል፡፡ ቀስበቀስ ዓለምን አየቀየሩ እኛ ደግሞ የእነርሱን ‹‹ሳይንስ›› ዝም ብለን እያመንን፣ የእነርሱን ፖለቲከኞች እየመረጥን፣ ምርታቸውን እየገዛን፣ ዘፈናቸውን እያዳመጥን እና ፊልማቸውን እያየን በቁሳዊ መሰውያነት ላይ ነፍሳችንን እናሰቃያለን፡፡ ሞርስ ክላይን እንዳለው ‹‹የተንቀሳቃሿ ዓለም ቲወሪ ፀሐይን ከህዋ መሃል ላይ በማስቀመጥ የሰውን ልጅ አንድ የሆነ በቀዝቃዛው ሰማይ ላይ በሚንሳፈፍ ብናኝ ውስጥ ያለ ፍጥረት ሁኖ እንዲታይ አድርጎታል፤ የተወለደው በክብር እንዲኖር እና በሞቱም ላይ ገነትን እንዲወርስ ከመምሰል አርቆታል፡፡ የአምላክ አገልጋይ ፍጥረት እንዳይመስልም አድርጎታል፡፡››

198) አንዳንዶች ብዝሀኑን ለማታለል በትዉልድ ቅብብሎሽ ውስጥ ያለፈ ዓለማቀፋዊ ሴራ የሚለዉ የማይታመን እና ከእዉነት የራቀ ነዉ ይላሉ፡፡ ግን እነዚህ ሰዎች እራሳቸዉን ከእነርሱ ከባለቤቶቹ ከፍሪማሶናሪ ስራዎች እና ጽሕፈቶች ጋር ብቻ ማስተዋወቅ ነዉ የሚኖርባቸዉ፤ ለምሳሌ በ1798 ጆን ሮቢንሰን ‹‹ **Proofs of a Conspiracy Against All the Religions and Governments of Europe Carried Out in the Secret Meetings of the Freemasons, Illuminati and Reading Societies.**›› በሚለዉ መጽሐፉ ዉስጥ ይህንን ሲያጋልጥ፤ ታላቁ ባለ 33 ዲግሪ ማዕረግ አዛዥ አልበርት ፓይክ የማሱኖችን የመጨረሻ ዓለምን የመቆጣጠር ግብ በተመለከተ በጣም ከጅምሩ በርካታ ከሆኑ ደብዳቤዎች ጋር ይመጣ እንደነበር ነዉ፡፡ እንዲሁም የጺዮናዊዎቹ መጽሐፍ ‹‹ **Protocols of the Learned Elders of Zion**›› የሚለዉ፡ በመቀጠል የሚከናወነዉን እና እየተፈጸመ ያለዉን ትክክለኛ እቅዳቸዉን ሙሉበሙሉ የሚገልጽ ነዉ፡፡



199) ከ ‹‹Foundations of Many Generations›› በ ኢ.ኢስትሂ ‹‹አንዱ የሚሸከፈከፈዉ ኳስ ምድር ስፈታፈክ የሰፈዉ ነገር ቢኖር፤ ስስከፈዉ የዉሸት ዉሸት ጉልበት የሰዉን ልጅ የስዕምር ባፈያ የማድፈግ ኃይል እንዳሰዉ ያሳየ ነበር። እናም የስፈሱ የስሜት ህሞሶች የሚያቀርኩስትን ማስረጃ መልሶ ስማስተዋል እንዳደደፍር ሁኗል፤ በፈቱ የሚታየዉን ግልጹን እና የተሰመደዉን የፀሐደ እንቅስቃሴ እንዲቃወም፤ ፍጹም እፈሱን እንቅስቃሴ በሴሰበት ምድር ሳደ እንደቆመ ተሰምቶት ሳሰ፤ በሴሳ ሰዉ ጥቆማ በታሳቅ ፍጥነት ክብ እየተሸከረከረ እንደሆነ ስመቀበል ደዘጋጃል፤ ወፎች ሲበረና መፈት ሳደ ሲያርፍ ሲያደ፡ በእዉነት መፈቱ ከወፎቹ ፍጥነት በትልቅ ቁጥር እጥፍ እየተጓዘ እንደሆነ ስማመን ልኩን ከፍቷል፤ በመጨረሻም የስመሳን ሃሳብ ስመደገፍ፡ ፈጣፈዉ እዉነትን እንዳሰነገረዉ አድርጎ ስመቃወም ተዘጋጅቷል።››

200) በመጨረሻም ከዶክተር ሮባተም ‹‹እነዚህ የምናያቸዉ የኒዉተናዊ ፍልስፍናዎች ሃሳበ ፅኑነት የሌሳቸዉ ናቸዉ። ዉስጥ ዝርዝራቸዉ አግባብ የሆነዉ ምክንያታዊነት ተቃዉሞ ዉጤት ነዉ፤ ሁሱም ንድፌ ሃሳቡ ግምት ነዉ። በእርግጥም በመሳምት ሰደ መሳምት ከመሆን የዘስስ ነገር የሰዉም። ሆነተብሱ ማጠቃስያዎችም የሚሰጠዉ የተረጋገጡ ነገሮች ተብሱ ከሚታመነው ጋር አንድ እንዲሆን ተደርጎ ነዉ፤ እናም እዉነቶች ተብስዉ እንዲወሰዱ በማድረግ ስመጀመፈያዉ መሰረታዊ መሳምት ምክንያት አድርጎ ማቀረብ ነዉ፤ እንደዚህ አደነቱ የተዛባና የተዘበራረቀ የሀሰት ቃል ወደም እዴታ ተስፋፍቶ እና ተጠናክሮ ቲወደያዊዉ ስነፈስክ ሚዛናዊነት ያስውን የተቃዉሞ ጠያቂ በሚያያቸው የእነርሱ የማደመስል መጥፎ ጥንቅሳዎች ስርአቱን በጥሳቻ እንዲመስከተው አድርጓል። በጥብቅ ደዒን ስመፍታት እና ተጨማሪ ሲመጣ የሚችስዉን መዘዝ ስመቋቋም፤ ስርአቱን ስመገልበጥ በመሳው ዓስም የተንሰራፋውን ቲወሬ ስማፈራስና ስማዳን፤ ከመስራቾቹ ጋር የተያያዘው ያልተገባ አክብሮት ስመማረ፣ ተቀበደነት ስማግኘቱ፣ ስመጠበቁ እና ስመከበረ፡ ስማንጫጫም ምሳሴ ስሆኑበት ነገር ሁሱ ክብር እና ሞራል እንዲሰጥ አያስፈስግም ነበር። የእነርሱ ሀስተኛ ምክንያታዊነት ባጠቃሳዩ ያሳወቀዉን የሰዉ ዘር በስነፈስኩ ጉዳዩ ሳይ እንደፈስጉት መጠቀሚያ ማድረጋቸውና እንዲሁም የተከሳከሱስት እና ማሻሻያ ያደረጉስት እዉነታ የሌሰው ቲወሬ ግን ከማዘን ውጭ በምንም መልኩ ሙሱበሙሱ ነቅሰን እንድናስወገደው አደቻስንም።››

ስለ ዝርን ምድራችን ስተጨማሪ መረጃ፤ የኤሪክ ዱቤይን ‹‹ The Flat Earth Conspiracy›› መጽሐፍ ወይም በቅርቡ የሚወጣውን ‹‹የዝርን ምድር ሴራ›› የተሰኘ የትርጉም ስራ ያንብቡ። አድራሻውን ይጎብኙ፡ http://www.AtlanteanConspiracy.com

http://www.ifers.boards.net

ትርጉም ትንሳኤ ዘኢትዮጵያ

Ethio Flat Earth Truth

ይህን በመጫን ይቀላቀሉን http://www.t.me/ethioflat

tnsaezethiopia@gmail.com

ይህ መጽሐፍ በባለቤቱ ፍቃድ የተተረጎመ ነው።